# ገበታዋሪያ

## የንባብ መማሪያ።

ከደስታ ተክለ ወልድ

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

በቅዱስ አልዓዛር ማተሚያ ቤት - ድሬ ዳዋ።
፲፱፻፷፰ ዓመተ ምሕረት።

# ገበታዋሪያ የንባብ መማሪያ።

## ዐጭር ያማርኛ ግስና ርባታ ከነፊደሎቹ

### ገና ካልታተመው ከታላቁ ግስ ባጭር ቃል ተለቅሞ የወጣ።

ተረቶችና ታሪኮችም ግጥሞችም አንዳንድ።

ከደስታ ተክለ ወልድ ዘብሔረ ወግዳ

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

በቅዱስ አልዓዛር ማተሚያ ቤት - ድሬ ዳዋ።

፲፱፻፳፫ ዓመተ ምሕረት።

.

# ማውጫ


መቅድም። ........ 3

የግእዝና ያማርኛ ፊደል አንዳንዱ ኅርመት። ........ 5

ሰባት ሰባቱ ከግእዙና ካማርኛው ራብዕ ድርቦች ጋራ እነኰኊኲም ሳይቀሩ። ........ 5

ክፍል ፩። ........ 7

ምዕራፍ ፩። ........ 7

የኹለት ፊደል ግስና ቃል። ........ 7

ምዕራፍ ፪። ........ 10

የሦስት ፊደል ግስና ጥሬ ዘር። ........ 10

ምዕራፍ ፫። ........ 27

ያራት ፊደል ግስ (በደጊመ ቃል)። ........ 27

ምዕራፍ ፬። ........ 31

ክፍል ፪። ........ 32

ምዕራፍ ፭። ........ 32

(ኀላፊ አንቀጽና ትንቢት አንቀጽ) ........ 36

(ዐቢይ ርባታ) ........ 37

ክፍል ፫። ........ 45

ምዕራፍ ፮። ........ 45

ክፍል ፬። ........ 25

ምዕራፍ ፯። ........ 25

ምዕራፍ ፰ ........ 26

ክፍል ፭። ........ 27

ምዕራፍ ፱። ........ 27

እገበታ ባይቀርብ ልጅ ካዋቆች ጋራ፤ ይኽ ገበታዋሪያ ለልጆች ተሠራ። ዐዋቆች ቢጥሉት ገበታዋሪያን ልጆች ተሰብስበው ሲያነሡት አየን። ከገበታዋሪያ የሚበልጥ ሲሳይ ስንኳን በምድርና የለም በሰማይ። ገበታዋሪያትን የረገጠ ሰው፤ ሳይጠግብ ይኖራል ዘላለም ሲርበው። ይኽቺነ መጣፍ በኋላ የፊደሉን አገባብ ያረሙልኝና ርባታውን የጣፉልኝ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ናቸው።

# መቅድም።

ይኽቺን መጣፍ የጣፍኹበትና የፊደሉን አገባብ የታረመበትን ዋናው ምክንያት አራት ነው። ፩ኛው ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ የንግሊዝን ባንክ በገዙ ጊዜ እንግዴኽ ወዲኽ ባንኩ የናንተ ከኾነ ለባንክ ሥራና ለማንኛውም ለመንግሥታችኹ ጕዳይ ውልም ለመዋዋል ቢኾን ቋንቋችኹን ማደስና ማከናወን ፊደላችኹን ማረም ማዘጋጀት ያማርኛን ግስ ማውጣት የቀድሞዉን የልማድ ጥፈት መተው ሥራን ኹሉ በፊደላችኹና በቋንቋችኹ መጣፍና መሥራት ይገባችኋል እያሉ እንግሊዞቹ መከሩን ብሎ ካማካሪዎች አንዱ ስለ ነገረኝ ነው። ይኽነንም የሚመስል ነገር የድሬ ዳዋ ጕምሩ ጣፊ ላንዲት ግእዝ ካማርኛ የምታውቅ ጀርመናዊት ሴት ፈርንሳይ ቋንቋ ደረስኝ ጥፎ ቢሰጣት ጕምሩኩ የፈረንሳይ ነውን ሙሴ (Monsiur) ደዜም (Deuxieme) ኮማንዳ (Commandant) ለማለት ከዋየል በላይ የማይነበብ ትርፍ ጨምረኽ ፺ና ፲ፊደል ከምትጥፍ ይልቅ የናንተ ፊደል አይቀለጥፍምን የናንተ ፊደል የፈረንጅ የፈረንጅ ፊደል የናንተ ቢኾን መለስ ብላችኹ አታዩትም ነበር አለችው። ባስበ ተፈሪ ግን ካማርኛ በቀር ሌላ ቋንቋ እንዳይጣፍ መከልከሉን ልጅ ሰይፉ በቃላቸው ነግረዉኛል። ይኽም ሥራ የብልጉ የበጅሮድን ተክላዋሪያት መኾኑን አልጠራጠርም። ፪ኛው፤ ሦስት ያገራችን ልጆች በድሬ ዳዋ ያለው የፈረንሳዮች ዐኪም ሥራ እንዲሰጣቸው ወደ ቤቱ ቢመጡ ኹሉንም በጥፈት ከፈተናቸው በኋላ የፊደል አገባብ አያውቁምና የጥፈት ሥራ ሊሠሩ አይገባቸውም ብሎ ኹለቱን ልጆች መለሳቸው የሚሉ ወሬ ብሰማ ባገራችንም የግእዝንና ያማርኛን ፊደል አገባብ ሳያውቁ እንዳሳባቸው የሚጥፉ ሰዎች ከሥራ የሚከለከሉበት ጊዜ ምናልባት ሳይመጣ አይቀርምና፤ ጣፎችና ወጣቶች ኹሉ ወደ ፊት እንዲጠነቀቁ ብዬ ነው። ፫ኛው፤ ከዕለታት አንድ ቀን ወዳዲሳበባ ደብዳቤ ለመላክ ድሬ ዳዋ ባቡር መቆሚያ ገብቼ ሳለኹ ከጣፎቹ አንዱ በጣፈው ወረቀት አድራሻ ላይ (ይድረስ ለክቡር አቶ በማለት ፈንታ ይድረስ ለክቡር ዓቶ) ብሎ የጣፈውን አየኹና ምነው ወንድሜ በአልፋ አ ግእዝ የሚጣፈውን በዐይኑ ዐ ራብዕ ጣፍኸው ብዬ ብጠይቀው አልተወስነምና ምናለበት በማንኛውስ ብጥፈው ብሎ መለሰልኝ። ፬ኛው፤ በፈረንጅ ተማሪ ቤት የሚማሩ ልጆች ካንዳንዶቹ በቀር የግእዝን ትምርት አገባብ የሚያውቁ ስለ ኾኑ አስተማሮቻቸው ይኽ ቃል ባማርኛ ምን ይባላል ብለው ሲጠይቋቸው ስም የለውም እያሉ ይመልሱላቸዋል። ከነዚኽም አንዱ ተማሪ አባይን ያላየ ምንጭ ያመሰግናል እንዲሉ፥ ሴትንና ወንድን ለይቶ የሚያስረዳ አገባብ

(ዝርዝር) በግእዝ ቋንቋ አለ ወይ ብሎ ጠየቀኝ፤ እኔም ለጥያቄው መልስ ብሰጠው እንግዴኽ ወዲኽ ያስተማሮቼን ጥያቄ ኹሉ በግእዝ አለ ይኖር ይኾናል እላለኹ እንጂ ስም የለውም ብዬ አልናገርም አይለምደኝም አለኝ። (ያገርን ቋንቋ ላይማሩ የውጪ አገር ቋንቋ መማር እንዳይገባ በዚኽ ይታወቃል። ማን ፈረንጅ ነው ያገሩን ቋንቋ ሳይማር የባዕድ ቋንቋ የሚማር ምን ሕፃን ነው የናቱን ጡት ሳይጠባ እንጀራ የበላ። ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ባልጋ ወራሽነ ሳሉ ዐጤ ምኒልክ ተማሪ ቤት ገብተው ለተማሮቹ ኹሉ የምክር ቃል (ስብከት) ሲናገሩ ያገሩን ቋንቋ ያልተማረ ቤቱን በድቡሽት ላይ የሠራ ሰውን ይመስላል ብለዋል ለውቀቱ መሠረት የለውም ማለት ነው)።

የክፍልና የምዕራፍ ማስታወቂያ። ይኽች መጣፍ ባ፫ ክፍል ትከፈላለች። መዠመሪያው ያማርኛ ግስ ነው እሱም ባ፬ ምዕራፍ ይከፈላል። ፩ኛው ርባታ። ፪ኛው ተረትና ምሳሌ ታሪክም። ፬ኛው ግጥም፤ እሱም በ፪ ምዕራፍ ይከፈላል። ፫ኛው ዐደራ። በዚኽም ግስ ፪ ጥቅም ይገኝበታል። ያበገደን ተራ ማወቅ። የፊደልንና የቃልን አገባብ መጠንቀቅ። ከዚኽ አስቀድሞ የሚጥፈው ጥፈት ኹሉ ከተለመደው ካንዳንድ ቃል በቀር በእልፍ እና በሆይ ሀ በሳቱ ሰ ነው እንጂ በሐውት ሐና በኀርም ኀ በኹኺኻኼኽኾ በዐይኑ ዐና በሠዉት ሠ አይጣፍም ነበር። ዛሬ ግን በመዝገበ ፊደል ባ፲፮ኛው ገጽ እንደ ተነገረ ቃሉ እየተመረመረ እንዳይገቡ ኹኖ በነዚኽ ኹሉ ተጥፏል (ታትሟል)። በፀሐኅና በጸፀ ግስ በግእዝ ብዙ ሲኾን ባማርኛ ማነሱ ለአዐና ለጠጨ ስለ ተለወጠ ነው። ኹለት ፊደል ኹኖ መዠመሪያዉና መድረሻው ራብዕ የኾነ ግስ ኹሉ በግእዝ አፀና ሀሐኀ ያሉበት ነው። ይኸውም ብእሰ ገዐረ መሀለ መሐረ አኀዘ። ገብአ ሠርዐ በርሀ ጸብሐ በዝኀ ያለውን ባሰ ጋረ ማለ ማረ ያዘ። ገባ ሠራ በራ ጠባ በዛ ማለቱን ያሳያል። ሌሎችም እንደነዚኽ ተለዋዋጮች ወይም ተወራራሾች የኾኑ በና መ ገና ቀ ዘና ሰ ጠና ተ ናቸው። (ማስረጃ) በና መ ሲወራረሱ ዘንመ ዝናም=ዘነመ ዝናብ። ዘመን=ዘበን። ነምር=ነብር ቀማ ቀማኛ=ቀበኛ። ገና ቀ ሲወራረሱ ወገጠ=ወቀጠ። ዘገጠ=ዘቀጠ። ዘና ሰ ሲወራረሱ ምዝጋና=ምስጋና። ዞረ=ሾረ። ጠና ተ ሲወራረሱ ወተረ=ወጠረ ይላል። ሌላም ይኽን የመሰለ ብዙ አለ። በሺዋና በጐንደር በያውራጃው ኹሉ ላለው ዐማርኛም ብዙ ልዩነትና መለዋወጥ አለው። (ማስረጃ) ሺዎች ረጠበ ተረጠበ የሚሉትን ጐንደሮች ቀለተ ተቀለተ ይሉታል። ጐመዠ=ሰየ። ቅል ጥቂት=ቋንጅል ሽክና። ምጣድ አክንባሎ=ምገኀ ሞገድ። ቀሠም=ቀለም። ወገል=ከርፈስ። በሶ-ብላ=ዘቃ ቅቤ። ቀንበር=ወስኮ የመሰለው ኹሉ። የንጨትም ስም በያገሩ እንደዚኹ ነው። (ዐማርኛን ጠባብ ነው ያሉ ይስታሉ።

# የግእዝና ያማርኛ ፊደል አንዳንዱ ኀርመት።

## አ በ ገ ደ ሀ ወ ዘ ሐ ኀ ጠ የ ከ ለ መ ነ ሠ ዐ ፈ ጸ ፀ ቀ ረ ሰ ተ ጸ ፐ።

## ጐጀ ዠ ኈጨ ኰኸ ኘ ቈ ሸቸ ።

ያገራችን ፊደል ራሱን የቻለ ነው። አገራችንም እንደዚኹ በ፫ ክፍል ራሷን ያቻለች ናት በማዕድን፤ ባትክልት፤ በንስሳ። በውቀትም ራሷን የምትችልበት ጊዜ ይመጣ ይኾና። ፈላስፋው ሰሎሞን (በ ጊዜ ለኵሉ ለኹሉ ጊዜ አለው) ብሏልና። ልጆቿም ርስ በርሳቸው ካልተጣሉ በቀር በወንድነት ራሳቸውን የቻሉ ናቸው። ጠላታቸውንም ኹሉ ጊዜ ተስፋ የሚያደርገው ርስ በርሳቸው መጣላታቸውን ነው። የጥሉም መሠረት ብዙ ሲኾን መደበኛው ሃይማኖት ይባላል።

| ሰባት ሰባቱ ከግእዙና ካማርኛው ራብዕ ድርቦች ጋራ እነጐኈኰም ሳይቀሩ። | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተራ ቍጥሩ ስሙ። | (ግእዝ) | (ካዕብ) | (ሣልስ) | (ራብዕ) | » | (ኃምስ) | (ሳድስ) | (ሳብዕ) |
| ፩ አልፍ | አ | ኡ | ኢ | ኣ | | ኤ | እ | ኦ |
| ፪ ቤት | በ | ቡ | ቢ | ባ | ቧ | ቤ | ብ | ቦ |
| ፫ ገምል | ገ | ጉ | ጊ | ጋ | | ጌ | ግ | ጎ |
| » » | ጐ | » | ጒ | ጓ | | ጔ | ጕ | » |
| ፬ ድልት | ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዷ | ዴ | ድ | ዶ |
| » » | ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጇ | ጄ | ጅ | ጆ |
| ፭ ሆይ | ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | | ሄ | ህ | ሆ |
| ፮ ዋዌ | ወ | ዉ | ዊ | ዋ | | ዌ | ው | ዎ |
| ፯ ዛይ | ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዟ | ዜ | ዝ | ዞ |
| » » | ዥዕ | ዡ | ዢ | ዣ | ዧ | ዤ | ዥ | ዦ |
| ፰ ሐውት | ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | | ሔ | ሕ | ሖ |
| ፱ ኀርም | ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | | ኄ | ኅ | ኆ |
| » » | ኈ | » | ኊ | ኋ | | ኌ | ኍ | » |
| ፲ ጠይት | ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጧ | ጤ | ጥ | ጦ |
| ፲፩ የማን | ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጯ | ጬ | ጭ | ጮ |
| ፲፪ ካፍ | ከ | ኩ | ኪ | ካ | | ኬ | ክ | ኮ |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| » » | ኰ | » | ኲ | ኳ | ኴ | ኵ | | » |
| » » | ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ዃ | ኼ | ኽ | ኾ |
| ፲፫ ላዊ | ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሏ | ሌ | ል | ሎ |
| ፲፬ ማይ | መ | ሙ | ሚ | ማ | ሟ | ሜ | ም | ሞ |
| ፲፭ ነሐስ | ነ | ኑ | ኒ | ና | ኗ | ኔ | ን | ኖ |
| » » | ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኟ | ኜ | ኝ | ኞ |
| ፲፮ ሠውት | ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሧ | ሤ | ሥ | ሦ |
| ፲፯ ዐይን | ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | | ዔ | ዕ | ዖ |
| ፲፰ ፈፍ | ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፏ | ፌ | ፍ | ፎ |
| ፲፱ ጸደይ | ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጿ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ፳ ፀጸ | ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | | ፄ | ፅ | ፆ |
| ፳፩ ቆፍ | ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | | ቄ | ቅ | ቆ |
| » » | ቈ | » | ቊ | ቋ | | ቌ | ቍ | » |
| ፳፪ ርእሰ | ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሯ | ሬ | ር | ሮ |
| ፳፫ ሳት | ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሷ | ሴ | ስ | ሶ |
| » » | ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሿ | ሼ | ሽ | ሾ |
| ፳፬ ታው | ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቷ | ቴ | ት | ቶ |
| » » | ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቿ | ቼ | ች | ቾ |
| ፳፭ ጸይት | ጰ | ጱ | ጲ | ጳ | ጷ | ጴ | ጵ | ጶ |
| ፳፮ ፌ ፈ | ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፗ | ፔ | ፕ | ፖ |

## ቊጥር በፊደልና በአኃዝ።

| |
|---|
| አ በ ገ ደ ሀ ወ ዘ ሐ ጠ የ ከ ለ መ ነ ሠ ዐ ፈ ጸ ቀ ቈ እ። |
| ፩ ፪ ፫ ፬ ፭ ፮ ፯ ፰ ፱ ፲ ፳ ፴ ፵ ፶ ፷ ፸ ፹ ፺ ፻ ፲፻ ፼። |

# ክፍል ፩።

## ምዕራፍ ፩።

| የኹለት ፊደል ግስና ቃል። | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| (አ) | አዠ | (በ) | በላ | ጐባ | ገላ |
| አአ | አየ | ባባ | በቃ | ጐኋ | ገል |
| አኡ | አለ | በጋ | በራ | ኋኋ | ጐላ |
| አብ | አለ (ሀለወ) | በግ | በሳ | ጐዳ | ገማ |
| አባ | አለ (ብህለ) | በጎ | ባሰ | ጋዳ | ገና |
| አቦ | አል | በጀ | ባተ | ገዛ | ገና |
| አዶ | አቶ | በዛ | ባት። | ገጨ | ገሣ |
| አጃ | አቻ | በጣ | (ገ-ጐ) | ጋጠ | ገፋ |
| አዎ | እት። | ቦካ | ገባ | ጋየ | ገራ (፪) |
| ጐራ | ሆሆ | (ሐ) | ጦለ | ኹሉ | (መ) |
| ጐሽ | ሆይ። | ሕግ | ጮለ | ኳለ | ማገ |
| ጒሽ | (ወ | ሐና | ጠማ | ኯላ | ሟዠ |
| ጐሽ | ዋበ | ሐኔ | ጣመ | ኬለ | መጣ |
| ገታ | ዋቢ | ሐቅ | ጦመ | ኾነ | ማጠ |
| ጐቸ | ወጋ | ሐር | ጠና | ከፋ | ማጥ |
| ጋተ። | ወደ | (ኅ) | ጫነ | ከፋ | ሟጨ |
| (ደ) | ዋጀ | ኋላ ኯ | ጠፋ | ካፋ | መካ |
| ደባ | ውሃ | (ጠ-ጨ) | ጣፈ | ኰራ | መላ |
| ደጋ | ዋቄ | ጠባ | ጣፋ | ከሳ | ሞላ |
| ደጅ | ወዛ | (ጠበወ) | ጦፈ | ኰሳ | ማለ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ዳዳ | ወጣ | ጠባ | ጠቃ | ከሰ | መና |
| ድዳ | ዋጠ | (ጠብሐ) | ጠራ | ኳስ | መና |
| ዳዋ | ወካ | ጠባ | ጣረ | ኳሽ | መራ |
| ዳጠ | ዋለ | (ጸብሐ) | ጫረ | ኳተ። | መራ |
| ደላ | ዋኘ | ጠጋ | ጦረ | (ለ) | ማረ |
| ዶለ | ወሣ | ጠዳ | ጨሰ | ላበ | መሳ |
| ደማ | ወቃ | ጠጀ | ጣት | ለጋ | መሸ |
| ደና | ወራ(፪) | ጠጅ | ጫት | ለጋ | ማሰ |
| ዳነ | ወሬ | ጣደ | (የ) | ላገ | ሚሸ |
| ዳኘ | ወር | ጣዠ | የበ | ለዛ | መታ |
| ደፋ | ዋሰ | ጦዘ | ያዘ | ላጠ | ሞተ። |
| ደቃ | ዋሸ። | ጠጣ | ይኽ | ላጨ | (ነ) |
| ደራ(፫) | (ዘ-ዠ) | ጣጣ | ይፋ | ለየ | ነባ |
| ዳረ | ዘባ | ጣጣ | የት። | ለካ | ነጋ |
| ዶሮ | ዘጋ | ጦጣ | (ኰኰኸ) | ላከ | ነዳ |
| ዳሰ | ዛገ | ጫጨ | ካበ | ላላ | ናደ |
| ዳስ | ዣዠ | ጠዬ | ኮበ | ለማ | ነው |
| ዳት። | ዛለ | ጮኸ | ከዳ | ላመ | ነዛ |
| (ሀ) | ዘና | ጠላ | ካደ | ለፋ | ነጣ |
| ሂአ | ዛቀ | (ጸልአ) | ኼደ | ለቃ | ነጨ |
| ሄደ | ዘራ | ጠላ | ከካ | ላቀ | ናጠ |
| ሀሀ | ዞረ | (ጠለ) | ኰኳ | ላሰ | ናጫ |
| ሀሁ | ዛተ። | ጣለ | ከላ | ላት። | ነካ |
| ነሣ | (ፈ) | ቀጨ | ራስ | ሰራ | ተወ |
| ነፋ | ፋገ | ቄጨ | ርሱ | ሻረ | ተካ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| (ነፍሐ) | ፈጀ | ቋጨ | ረታ። | ሾረ | ቸከ |
| ነፋ | ፈጨ | ቈጫ | (ሰ-ሸ) | ሸሸ | ተላ |
| (ነፈየ) | ፈካ | ቈየ | ሰባ | ሰቸ | ቻለ |
| ነጸ ጣ | ፈላ | ቋያ | ሳበ | ሸተ | ቻመ |
| ነቃ | ፋመ | ቀላ | ሳባ | ሳተ። | ተኛ |
| ናቀ | ፋፋ | ቈላ | ሸባ | (ተ-ቸ) | ተፋ |
| ናረ | ፈቃ | ቀማ | ሳጋ | ተባ | ተራ |
| ኖረ | ፋቀ | ቃመ | ሳጋ | ቱባ | ቸረ |
| ናሰ | ፈራ | ቆመ | ሰው | ተጋ | ተቸ። |
| ነት | ፋረ | ቀና | ሺዋ | | |
| ናቸ። | ፈሳ | ቀቅ | ሰጠ | | |
| (ሠ) | ፈታ። | ቆቅ | ሰጥ | | |
| ሠባ | (ጸ) | ቀረ | ሸጠ | | |
| ሥብ | ጸጋ ጠ | ቈራ | ሻጠ | | |
| ሣባ | ጸዳ ጠ | ቃረ | ሰየ | | |
| ሠጋ | ጸጥ ሰ | ቈቻ | ሰካ | | |
| ሠዋ | ጾመ ጦ | ቃተ | ሰላ | | |
| ሣለ | ጸና ጠ | ቃተ። | ሳለ | | |
| ሠም | ጻፈ ጣ | (ረ) | (ሰሐለ) | | |
| ሠኔ | ጻረ ጣ | ረባ | ሳለ | | |
| ሠኘ | (ፀ) | ራበ | (ሰዐለ) | | |
| ሣሣ | ፀር ጠ | ረጋ | ሾለ | | |
| ሠራ። | (ቀ-ቈ) | ረዳ | ሰማ | | |
| (ዐ) | ቀባ | ራደ | ሸማ | | |
| ዐባ | ቀባ | ረጨ | ሳመ | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዐጣ | ቀጋ | ሮጠ | ሾመ |
| ዐጨ | ቈጋ | ረካ | ሰኞ |
| ዐጤ | ቀዳ | ራቀ | ሸነ |
| ዐማ | ቈዳ | ራራ | ሸኘ |
| ዓሣ | ቃዥ | ሮሮ | ሰፋ(፪) |
| ዐራ | ቀጣ | ረሳ | ሰፍሐ ሰፈየ |
| ዐሸ። | ቃጣ | ራሰ | ሾቀ |

# ምዕራፍ ፪።

| የሦስት ፊደል ግስና ጥሬ ዘር። | | |
|---|---|---|
| (አ) | አገደ | |
| አበበ | አገዳ | |
| አበባ | አጐለ | |
| እባብ | አገረ | |
| አበደ | አጋር | |
| እብድ | አግሬ | |
| አባያ | እግር | |
| አቦል | አገር | |
| አበቀ | አጐረ | |
| እብቅ | አደበ | |
| አበሰ | አደብ | |
| አበሳ | አደገ | |
| አበሻ | አደጋ | |
| አበተ | አዳጋ | |
| አብታ | እጅግ | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| አቤት | አዳም | | | | |
| አቤቱ | አድሞ | | | | |
| አቤቶ | አደስ | | | | |
| እበት | አህያ | | | | |
| አወከ | አፈለ | በደለ | በክት | ቦቀረ | ባተሌ |
| አዘዘ | አፈኬ | ባደነ | በለገ | በቀተ | ቡችላ |
| እሑድ | አፈፈ | በድን | በልግ | በረደ | በተነ |
| አየረ | አፈፋ | ቦደነ | ባለገ | በረዶ | በትር። |
| አየር | አሮጌ | ቡድን | ባለጌ | ብርድ | (ገ-ጐ) |
| አከለ | አረጀ | በደረ | ቢላዋ | በረዘ | ጐበበ |
| አካል | አረኸ | ብድር | በለዘ | ቦርጭ | ጐባባ |
| እኩል | አረኾ | ቦደሰ | ብልዝ | በረከ | ገበደ |
| እኩየ | አረነ | በዘነ | ብልጎ | ብራኳ | ገበዘ |
| እኽል | አረቂ | ቦዘነ | በለጠ | ብርክ | ገበዝ |
| አከረ | አረተ | ቦዘን | ብልጥ | ባረከ | ግብዝ |
| አከተ | አሸገ | ባዘቀ | ብልጫ | በረቀ | ጐበዘ |
| አለለ | አሰድ | ባዜቃ | በለጨ | ብራቅ | ጐበዝ |
| አለሌ | አሲድ | ባዝራ | በለጭ | ብርቅ | ጋበዘ |
| እልፍ | አሰጅ | ባዘተ | በለለ | ባረቀ | ግብዣ |
| አመመ | አሸዋ | ባዘቶ | ቦለለ | በረቋ | ገበጠ |
| እመም | እስከ | በጠጥ | ባለቀ | ቦረቀ | ገበጣ |
| አመነ | አሰረ | ባጠጠ | በለሰ | በረረ | ግብጣ |
| አሚን | አተለ | ቧጠጠ | በለሸ | በረሰ | ግብጦ |
| አማን | አተላ | ባጠለ | ብላሽ | በረታ | ጐበጠ |
| አሜን | አቴና | በጨቀ | በለተ | በረት | ጐባጣ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| አማረ | አተረ | ቦጨቀ | ብልት | ብረት | ግብጥ |
| አሟረ | አተር | በጠረ | ብላታ | ብርቱ | ገበየ |
| አሞራ | አተተ | ቧጨረ | ቧልት | በለከ | ገበያ |
| አመት | አቴቴ። | በጠሰ | በነነ | በሰለ | ገበሎ |
| አመቴ | (በ) | በየደ | ቦነነ | ብስል | ጐበኘ |
| አንቦ | በገነ | በየነ | ባነነ | በሰና | ጐበኛ |
| አንድ | በገና | ብይን | በቀለ | ብስና | ጐባን |
| እንደ | በገረ | ብክካ | በቀል | ብሳና | ገበረ |
| አነሰ | ብጉር | በከለ | በቅሎ | በሸቀ | ገበሬ |
| አኒሳ | ቢጋር | ባከነ | በቈሎ | በሰሰ | ገበር |
| አናት | ቧገተ | ባካና | በቅል | በተከ | ገባር |
| እናት | ቧገታ | ቡከን | ባቄላ | በተኻ | ጐበረ |
| አፈገ | በደለ | በከተ | ብቅል | ባተለ | ብስ |
| ጋበሰ | ገሃድ | ገመድ | ገነዘ | ግርድ | ገስረ |
| ገበታ | ገውዝ | ግምጃ | ጐነጠ | ጋረደ | ጐረሰ |
| ጓጐጠ | ገዎቻ | ጐመደ | ጐነጨ | ጋሬዳ | ገሰሰ |
| ጓጐለ | ገዘመ | ጐመድ | ጐንጭ | ጐረደ | ገሸሸ |
| ገመመ | ገዝም | ጐመዠ | ገነነ | ጐራዴ | ጋተለ |
| ጐጐመ | ገዠሞ | ገመጠ | ገናና | ገረዘ | ገተመ |
| ጋጋኖ | ገዘፈ | ገመለ | ገነኘ | ጐሬዛ | ገተም |
| ገገረ | ገዛፍ | ግመል | ጐነፈ | ገረጣ | ጐተነ |
| ጋገረ | ግዙፍ | ገመነ | ጐኘረ | ግራጫ | ጐተና |
| ጋጋራ | ገዘረ | ገመና | ገነታ | ግራጭ | ገተረ |
| ጓጐረ | ገዘተ | ጐመን | ገነት | ጐረጠ | ጐተራ |
| ገደበ | ገጠበ | ገመረ | ገሠጠ | ጐረጥ | ገተተ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ገደብ | ገጠጠ | ገመር | ጋፈጠ | ጐርጥ | ግትቻ |
| ጐደበ | ገጣጣ | ጊሚራ | ጐፈየ | ጋረጠ | ጐተተ |
| ገደደ | ገጠመ | ገሞራ | ጐፉያ | ጋሬጣ | ጐትቻ። |
| ገዳዳ | ገጠረ | ጐመረ | ገፈፈ | ገረመ | (ደ-ጀ) |
| ጓደደ | ገጠር | ጐሞር | ገፈፋ | ግሩም | ደበበ |
| ገደል | ገጨረ | ጐማሬ | ጋፈፈ | ግርማ | ድባብ |
| ገደል | ገየደ | ጐመራ | ጋፈፎ | ገረማ | ደቡብ |
| ገድል | ገለበ | ጐምር | ጐፋፋ | ጐረና | ደባይ |
| ጐደለ | ገለባ | ገመሰ | ገፈረ | ጐረሠ | ደበለ |
| ጐደሎ | ገለብ | ገመሳ | ገፈራ | ጐርሻ | ደባል |
| ገደመ | ጐለበ | ገሚስ | ጋፈረ | ጐርሦ | ደቦል |
| ገዳም | ጋለበ | ገመት | ጐገረ | ገረፈ | ደበሎ |
| ጋድም | ገለጠ | ግምት | ጐፈሬ | ጐረፈ | ድበላ |
| ጐድን | ገለለ | ጐምቱ | ጐገር | ጐርፍ | ደበነ |
| ጐድኝ | ገለሌ | ገነባ | ገፈተ | ገረረ | ጀቦነ |
| ገደፈ | ጐለለ | ግንብ | ገፈታ | ግራር | ጀበና |
| ጐደፈ | ገለማ | ገንዳ | ገፈት | ጐረሮ | ደበቀ |
| ጐድፍ | ጐለመ | ጐነደ | ግፍት | ገረሸ | ደበረ |
| ገደረ | ጐልማ | ጐናጼ | ጋፈተ | ግርሻ | ደብር |
| ጊደር | ጐለተ | ጐንዳ | ጐረበ | ጋሸበ | ዳበረ |
| ጊድራ | ጐልት | ጐንዶ | ገረደ | ገሰለ | ዶበረ |
| ጐድራ | ገመድ | ግንድ | ገረድ | ግስላ | ደበሰ |
| ደበሳ | ደኸየ | ደመና | ደረባ | ወበራ | ወደር |
| ዳበሳ | ደከከ | ደመቀ | ደርብ | ወብራ | ወደሰ |
| ዳበሳ | ደከካ | ደመረ | ደረገ | ወገብ | ውዳሴ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ደበተ | ደከመ | ደመራ | ዳረገ | ወገቦ | ወገዘ |
| ደጐባ | ደካማ | ድመት | ድርጎ | ወገገ | ወዘመ |
| ደገገ | ድካም | ደነበ | ደረጀ | ወገግ | ዋዜማ |
| ደጋጋ | ዳከመ | ደነባ | ደረጃ | ወገደ | ዋዥማ |
| ድግጣ | ደከነ | ደንብ | ደረዘ | ወግዳ | ውዥሞ |
| ደገለ | ደከረ | ደነዘ | ደርዝ | ውጋዴ | ወዘና |
| ደገላ | ደለበ | ደነዝ | ደረጠ | ወገዘ | ወዘፈ |
| ጀጐለ | ድልብ | ድንክ | ድራማ | ወገዝ | ዋዝቀ |
| ጀጐል | ጀልባ | ጀነነ | ደረቀ | ወገጠ | ወዘተ |
| ደገመ | ደላጎ | ደነፋ | ደረቅ | ወገል | ወዘት |
| ደግሞ | ዳልጋ | ደነቀ | ድርቄ | ወገን | ወጠጠ |
| ዳግም | ደለዘ | ድንቅ | ድርቅ | ወገፈ | ወጠጤ |
| ደጐመ | ዶለዝ | ዳነተ | ደረሰ | ወገረ | ወጠለ |
| ደገነ | ዳለጠ | ደፈጠ | ድርስ | ወገራ | ዋጠላ |
| ደጋን | ደለኸ | ደፈጨ | ደረተ | ወገሬ | ወጠነ |
| ደገፈ | ደለለ | ደፈነ | ድሪቶ | ወገሸ | ወጨፈ |
| ደገፋ | ደለል | ዳፈን | ደረት | ወጌሻ | ወጨፎ |
| ደገሰ | ደለመ | ደፈቀ | ደሰመ | ወደበ | ወጠቀ |
| ደጐሰ | ደለማ | ደፈረ | ደሰቀ | ወደብ | ወጠረ |
| ዳጐሰ | ደለቀ | ደፋር | ዳሰሰ | ወደደ | ወየበ |
| ዳጐሳ | ደለሰ | ደፈር | ደሴት | ወዳጅ | ወይባ |
| ዳገት | ዶለት | ደለቀ | ደሰተ | ወዳጃ | ወየነ |
| ደደብ | ዱለት | ደቀል | ደስታ | ወደለ | ወያኔ |
| ደደኾ | ጀለተ | ዲቃላ | ድስት። | ደወል | ወይራ |
| ደደቀ | ደመጠ | ደቀነ | (ሀ) | ውዲላ | ወከበ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ደደረ | ድምጥ | ዳቄነ | ሀኬት | ውዴላ | ወከከ |
| ይደር | ድምጫ | ደቀቀ | ህላዌ | ወደመ | ወከለ |
| ደወለ | ዳመጠ | ደቂቃ | ህንድ። | ወደቀ | ወኪል |
| ደወል | ዳመጦ | ደቃቃ | (ወ) | ወዳቃ | ወከፈ |
| ደወረ | ደመመ | ድቃቂ | ወበቀ | ውዳቂ | ወከፍ |
| ደዘለ | ደመነ | ደረበ | ወበቅ | ወደረ | ወለበ |
| ወላባ | ወረፈ | ወረት | ዝብዱ | ዝየራ | ዘንግ |
| ወለባ | ወቀዘ | ወረታ | ዘበጠ | ዘይት | ዘንድ |
| ወለገ | ውቃዞ | ወርች | ዘባጣ | ዘከረ | ዘንዶ |
| ዋልጋ | ወቀጠ | ወሰበ | ዘብጥ | ዝክር | ዘነነ |
| ወለጋ | ውቃጭ | ወሸባ | ዘበነ | ዘለለ | ዘናና |
| ወለደ | ወቀሠ | ወሰደ | ዘበን | ዝለላ | ዘነፈ |
| ወላድ | ወቀሣ | ዋስዳ | ዘበኛ | ዝላይ | ዝንፎ |
| ወለድ | ወቀረ | ውስጥ | ዛበረ | ዘለላ | ዘነቀ |
| ወለለ | ወረበ | ወሰከ | ዥበር | ዝላላ | ዝነቀ |
| ወለላ | ወረብ | ወሰክ | ዘበተ | ዘለፈ | ዝናር |
| ወለል | ውርባ | ወስኮ | ዘበት | ዘለፋ | ዘፈነ |
| ዋለለ | ወረጋ | ወሸከ | ዘገባ | ዘለቀ | ዘፈን |
| ወለመ | ወረደ | ወሸላ | ዝግባ | ዘለቃ | ዙፋን |
| ወላሞ | ወራዳ | ወሸላ | ዘገጀ | ዘሊቅ | ዘፈፈ |
| ወለነ | ወረዳ | ውሻል | ዝግጁ | ዝልቅ | ዘፈቀ |
| ውለን | ውርድ | ወሸመ | ዘገጠ | ዘለሰ | ዝፍት |
| ወለኔ | ውርድ | ውሽማ | ዘገየ | ዘመደ | ዘቀጠ |
| ወለቀ | ውርዴ | ወሰነ | ዛጐል | ዘመድ | ዛቄነ |
| ወላቃ | ውራጅ | ወሰን | ዘገመ | ዝምድ | ዝርባ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ወለሰ | ዋርዳ | ውሽን | ዘገነ | ዘመመ | ዘረጋ |
| ወሊስ | ወረዛ | ወሸቀ | ዝግን | ዝማሚ | ዘረጠ |
| ዋልሴ | ወረኃ | ወሰስ | ዠግና | ዝማም | ዘረጦ |
| ዋሜራ | ወረጨ | ወተበ | ዘጐነ | ዘመረ | ዝራጭ |
| ዋምራ | ውጭ | ወታቦ | ዘርገ | ዝማሬ | ዘርጭ |
| ወመቴ | ወርካ | ወተፈ | ዘወረ | ዠመረ | ዘረፈ |
| ወገነ | ወረኘ | ወተረ | ዛዘነ | ዥመራ | ዘራፍ |
| ወንድ | ወረፈ | ወትሮ | ዘጠኘ | ዘመተ | ዘረፋ |
| ወንዴ | ወረፋ | ወተር | ዘጠና | ዘመቻ | ዘርፍ |
| ወንጅ | ወረቀ | ወተት | ዘጠረ | ዝሞት | ዘረረ |
| ወንዝ | ወርቅ | ወተተ። | ዘይቤ | ዠመት | ዘረር |
| ዋንዛ | ወረረ | (ዘ-ዠ) | ዘይብ | ዥማት | ዥረት |
| ወነጠ | ወረራ | ዠበበ | ዘየደ | ዘነበ | ዥራት |
| ዋንጫ | ወረሰ | ዝባድ | ዘየነ | ዝናብ | ዣርት |
| ወሠራ | ዋርሳ | ዠበደ | ዘየረ | ዘነጋ | ዘበተ |
| ዛተሎ | ጨበጣ | ጠደቀ | ጨለፈ | ጠናዛ | ጭቅና |
| ዝተት። | ጨብጥ | ጠዲቅ | ጭልፋ | ጭንጫ | ጠቀራ |
| (ሐ) | ጭብጦ | ጥቅድ | ጠለቀ | ጭንጨ | ጠቈረ |
| ሕብር | ጠበል | ጠወረ | ጣልቃ | ጥንፍ | ጠቋራ |
| (ሐገገ) | ጠበቀ | ጨዋታ | ጨለቀ | ጠነቀ | ጠቋር |
| ሔዋን | ጠብቃ | ጨውቴ | ጭልቃ | ጠንቅ | ጥቈር |
| ሕዝብ | ጠበቀ | ጠዘለ | ጨላቃ | ጨነቀ | ጠቀሰ |
| ሐይቅ | ጥብቅ | ጠጠረ | ጠለሰ | ጭንቅ | ጥቅሻ |
| ሐኪም | ጥብቆ | ጥጥር | ጠለስ | ጫንቃ | ጥቅስ |
| ሐምሌ | ጠበረ | ጨጨረ | ጠመደ | ጠነሰ | ጣቈሰ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ሐመር | ጠበራ | ጠጠተ | ጥማድ | ጥንስ | ጣቄሳ |
| ሖሞር | ጨበረ | ጠጠት | ጠመዥ | ጨፈገ | ጠረበ |
| ሕንጻ | ጨበር | ጠይብ | ጠመመ | ጣፈጠ | ጠርብ |
| ሕንፃ | ጨበሬ | ጠየመ | ጠማማ | ጣፋጭ | ጨረባ |
| ሐረር | ጠበሰ | ጠይም | ጣመነ | ጥፍጥ | ጠረገ |
| ሒሳብ | ጠቦት | ጠየፈ | ጣመን | ጣፊያ | ጠረዘ |
| ሐሰት | ጥቦት | ጠየቀ | ጥሞና | ጨፈነ | ጥራዝ |
| ሐተታ። | ጠገገ | ጥያቄ | ጠመኔ | ጨፈቀ | ጠረም |
| (ኀ) | ጠገግ | ጠየረ | ጠመቀ | ጨፈቃ | ጥርኝ |
| ኀጥእ | ጨገገ | ጠያር | ጠመቀ | ጠፈር | ጨረፈ |
| ኀይል | ጠገን | ጥይት | ጨመቃ | ጠፈር | ጠረቀ |
| ኀሊና | ጥገን | ጨከከ | ጠመረ | ጥፍር | ጠረቃ |
| ኀመር | ጭጎኝ | ጨከነ | ጠሞረ | ጨፈረ | ጨረቀ |
| ኀራጅ | ጠገረ | ጭከና | ጭመራ | ጭፍራ | ጨረቋ |
| ኀርም። | ጨጐረ | ጠኸኘ | ጣመተ | ጨቀየ | ጨርቋ |
| (ጠ-ጨ) | ጨጓራ | ጠለዘ | ጨመተ | ጨቅላ | ጨርቅ |
| ጠበበ | ጨጓራ | ጨለጠ | ጭምት | መ | ጭራቅ |
| ጥበብ | ጭገር | ጠለለ | ጠነባ | ጥቅም | ጠረረ |
| ጠበበ | ጠገተ | ጠለመ | ጥንብ | ጠቄመ | ጠራራ |
| ጠባብ | ጥገት | ጨለመ | ጠነጋ | ጥቄማ | ጨረር |
| ጨቦደ | ጫገት | ጨለማ | ጥገት | ጨቄነ | ጠረሰ |
| ጨበጠ | ጠደፈ | ጠለፈ | ጠነዘ | ጭቄኝ | ጥርስ |
| ጨረሰ | ከጀለ | ከንቱ | ክራር | (ለ) | ልዝብ |
| ጭራሽ | ክጀላ | ካንቻ | ኰረተ | ለበበ | ላዘገ |
| ጨረተ | ከደነ | ከንች | ኰረት | ልባብ | ለዘዘ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ጭረት | ክዳን | ከሠደ | ኰርቻ | ለደበ | ለዛዛ |
| ጭርት | ካህን | ክሥዳ | ካርታ | ልብድ | ላዘነ |
| ጫረተ | ከወነ | ክሣድ | ከሰበ | ለበጠ | ለሐጭ |
| ጫረታ | ከውር | ከሡተ | ከሰለ | ለበጣ | ለጠበ |
| ጠሰቀ | ከየደ | ኩፋዳ | ከሰል | ለበመ | ለጠብ |
| ጣሰሰ። | ኪዳን | ከፈይ | ከሰመ | ለበቀ | ለጠጠ |
| (የ) | ካከመ | ከፈለ | ከሰም | ለበቅ | ለጠመ |
| የገቦ | ኰኰኔ | ክፍል | ካስማ | ለበሰ | ሊጦን |
| ይሁዳ | ከክራ | ኩፋሌ | ኰሽም | ልብስ | ለጠፈ |
| የዋህ | ከለበ | ከፈነ | ከሽነ | ሌበቻ | ለጠቀ |
| የሎስ | ከላባ | ከፈን | ከሽን | ለገገ | ለጠሰ |
| ይተጌ | ከልብ | ኩፍኝ | ከሰረ | ልጋግ | ላከከ |
| ይቶት። | ከላዋ | ከፈፈ | ከሰሰ | ለገደ | ለከመ |
| (ለኰኸ) | ከለለ (፪) | ኰፈፈ | ኰሰሰ | ለጐደ | ለከፈ |
| ከበበ | ከለላ | ኰፈሰ | ኰሳሳ | ለገጠ | ለኰፈ |
| ክበብ | ከለል | ከፈተ | ከተበ | ለግጥ | ለኰሰ |
| ከበደ | ከለፈ | ከረበ | ከተለ | ለጐጠ | ለከት |
| ከባድ | ኰለፈ | ከረቦ | ከተመ | ለገመ | ለኾቴ |
| ክበድ | ከሊፋ | ከርቤ | ከተማ | ልግም | ለመደ |
| ከበረ | ከለሰ | ኰራዝ | ኰቸመ | ለጐመ | ልማድ |
| ከቢራ | ኰላሸ | ከረጫ | ኳተነ | ልጓም | ለመጠ |
| ክብር | ከመረ | ኰረጠ | ከተፈ | ለገሰ | ለምጥ |
| ከበሮ | ኮሞር | ከረየ | ከተረ | ለጋስ | ለመጠ |
| ከበሰ | ከማቸ | ኪራይ | ከተራ | ለገሸ | ለመመ |
| ክባስ | ኩምት | ከረመ | ከቸረ | ለደፈ | ልማም |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ከበተ | ከነዳ | ክርን | ከቸሮ | ለደመ | ለመነ |
| ከብት | ክንድ | ከርሥ | ኰቸሮ | ለውዝ | ልመና |
| ኩበት | ኰነነ | ከረፋ | ከተተ | ለወጠ | ለፈደ |
| ኾደደ | ኵነኔ | ኰረፈ | ኰተት | ለውጥ | ለፈጠ |
| ኹዳድ | ከነፈ | ከረረ | ከቸቸ | ለወሰ | ልፋጭ |
| ኹዳዴ | ክንፍ | ከራራ | ከቻቻ። | ለዘበ | ለፈፈ |
| ልፋፍ | ማገጠ | መጥን | መናጢ | ምረቃ | ሜትር። |
| ለቈደ | ማጋጣ | መጨኔ | ሜንጦ | መረቃ | (ነ) |
| ላቅዳ | ማገጥ | መጠቀ | መነጨ | ምራቅ | ነበበ |
| ላቈጠ | መገለ | ሚጨረ | ምንጭ | ምርቅ | ንባብ |
| ለመቀ | መግል | ሚያው | መነነ | መረረ | ነበዘ |
| ለቀማ | መገን | መሳይ | ምናኔ | መራራ | ነቢይ |
| ለቀቀ | ማገረ | ሚከከ | መነን | መረተ | ናበለ |
| ላቀቀ | ማገር | መከነ | ሚነነ | ምርት | ነበረ |
| ለቀሰ | ሞገሰ | መካን | ሞናና | ሚረተ | ነብር |
| ለቅሶ | ሞገስ | መከረ | መነቅ | ሚርት | ነገበ |
| ለሰነ | ሞገተ | መካር | መንታ | መሰገ | ናጌብ |
| ልሳን | ሙግት | ምክር | መኒቻ | ምሳግ | ነገደ |
| ልሻን | መደበ | መከራ | መሠጠ | መሸገ | ንግድ |
| ለሰቀ | መደብ | መከራ | መሠጠ | መሸገ | ነጐደ |
| ላሸቀ | መዳብ | መከር | ምሥጥ | መስክ | ነጐዴ |
| ላሰሰ | መደደ | መከተ | ምቀኛ | መስክ | ነጐድ |
| ለተመ | መደዳ | መከታ | ማቀቀ | መሸከ | ነገለ |
| ልቴም | መደዴ | ሞከተ | መቀስ | መሰለ | ነገሌ |
| ላቲን | ምድጃ | ሙክት | መቄት | ምሳሌ | ነጐለ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ለተተ | ሟደደ | መለገ | መረገ | ምስል | ነገሠ |
| ለታታ። | ሟደድ | ማለገ | ሞረደ | ማስነ | ነጋሽ |
| (መ) | ምድር | ማላጋ | ሞረድ | መሲና | ንጉሥ |
| መገበ | ሞጀረ | ማለደ | መርዋ | ሙስና | ነገረ |
| ምግብ | መዘዘ | ማለዳ | መረዘ | ምስር | ነገር |
| ምገኅ | መዘዝ | መለጠ | መርዝ | ምስር | ነጐረ |
| ሞገገ | መዘነ | ሚለጠ | መረጠ | ሞሸረ | ንጕር |
| ሞጋጋ | ሚዛን | ሚላጣ | ምርጥ | ሙሽራ | ነገተ |
| ማገደ | መዘቀ | መለከ | ሙርጥ | ምሰሶ | ነጐተ |
| ማገዶ | ሞዠቀ | መለሰ | ማረከ | ሟሸሸ | ነደደ |
| ሞገደ | መጠጠ | መልስ | ምርኮ | መሸተ | ነዲድ |
| ሞገድ | መጠጥ | ምላሽ | መረነ | መሸታ | ንዳድ |
| ሞግድ | ሟጠጠ | መልቲ | ምራን | መተረ | ነዳይ |
| መገዘ | መጠነ | ማመዘ | መረን | መተሮ | ነደለ |
| መጋዝ | መጠን | መነጠ | መረቀ | ማተረ | ነደላ |
| ናደለ | ነከተ | ነቀሰ | ሥልሳ | ዐበለ | ዐደን |
| ነደፈ | ነካታ | ነቀሸ | ሠነገ | ዐባይ | ዐደን |
| ናወዘ | ነኰተ | ነቀተ | ሠነጋ | ዐበላ | ዐደፈ |
| ነወጠ | ንምራ | ናርጅ | ሠንጋ | ዐበረ | ዐደፈ |
| ነውጥ | ነነዌ | ነረተ | ሠንኀ | ዐቦሬ | ዐደረ |
| ነወረ | ነፈገ | ናረት | ሠነቀ | (ዐበረ) | ዐዳር |
| ነውር | ንፉግ | ነሰበ | ሥንቅ | ዐቧራ | ዕዳሪ |
| ናወተ | ነፈዘ | ነሲብ | ሥንቅ | ዐገዘ | ዕድር |
| ነዘዘ | ነፈዝ | ነሸጠ | ሣቀየ | ዐኀዛ | ዐደር |
| ናዘዘ | ናፈጠ | ነሰረ | ሥቃይ | ዐገለ | ዐደሬ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ኑዛዜ | ነፍጥ | ነስር | ሠረበ | ዕግል | ዐጀረ |
| ነዘለ | ንፍጥ | ንስር | ሢርባ | ዐጉል | ዐጅሬ |
| ነዚፋ | ናፈለ | ነሽረ | ሠረገ | ዐገመ | ዐደሰ |
| ነዘረ | ነፈል | ነተበ | ሢርጋ | ዐገሠ | ዐዲስ |
| ነዝር | ናፈቀ | ንትብ | ሠርዘ | ዐገተ | ዐወደ |
| ናዘረ | ንፍቅ | ነተፈ። | ሠረዝ | ዕጎቻ | ዐውድ |
| ናዜራ | ነፈረ | (ሠ) | ሠረጠ | ዐጎት | ዐወጀ |
| ነሐሴ | ንፍር | ሠበዘ | ሥርጥ | ዐጓት | ዐዋጅ |
| ነጠበ | ንፍሮ | ሠበዝ | ሠራጨ | ዐበጀ | ዐዋዜ |
| ነጥበ | ነፈሰ | ሠገገ | ሥረይ | ዐጀብ | ዐውሎ |
| ነጠጠ | ነፋስ | ሠጋጊ | ሥራይ | ዐደገ | ዐወቀ |
| ነጠለ | ነፍስ | ሠገረ | ሠርክ | ዐደዳ | ዐወረ |
| ነጠላ | ነፍት | ሠጋር | ሢራክ | (ዐደየ) | ዐወሰ |
| ነጠፈ (፪) | ነቀዘ | ሠጠጠ | ሠረቀ | ዐደይ | ዐዘበ |
| ነጠቀ | ነቀዝ | ሣጠራ | ሣረረ | ዐደለ | ዐዛባ |
| ነጠረ | ነቄጥ | ሠየመ | ሠተረ። | ዕድል | ዐዘለ |
| ንጥር | ነቀለ | ሡካር | (ዐ) | ዐደሌ | ዕዝል |
| ነጥር | ነቀላ | ሠለጠ | ዐበዛ | ዐዳል | ዐዘሎ |
| ነጠሰ | ነቀፈ | ሠላጤ | ዐበጠ | ዐጀለ | ዐዘን |
| ነከለ | ነቀፋ | ሣለቀ | ዕባጭ | ዐደመ | ዐዘን |
| ነከረ | ነቀረ | ሥላቅ | ዐበጠ | ዐድማ | ዐጠበ |
| ነኰረ | ንቃሪ | ሠለሰ | ዐብጤ | ዕድሜ | ዐጠድ |
| ነከሰ | ነቈረ | ሠላሳ | ዐበየ | ዐጀም | ዐጨደ |
| ንክሻ | ነቋራ | ሥላሴ | ዐብዩ | ዐደነ | ዐጨዳ |
| ዐጠጠ | ዐሉላ | ዐማች | ዐረጠ | (ፈ) | ፎከት |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ዐጠጥ | ዐለመ | ዐነጠ | ዐራጣ | ፈገገ | ፈለገ |
| ዐጣጥ | ዕልም | ዐኘከ | ዕሪያ | ፈገጠ | ፈለግ |
| ዐጥም | ዐለም | ዕንካ | ዐርኬ | ፋጐሎ | ፍለጋ |
| ዐጠነ | ዓለም | ዐነቀ | ዐረመ | ፈገመ | ፈለጠ |
| ዕጣን | ዓላማ | ዐሣማ | ዐረም | ፈጋራ | ፈሊጥ |
| ዐጠፈ | ዐለፈ | ዐሠሠ | ዐረፈ | ፋገረ | ፈለለ |
| ዐጠፋ | ዐለቀ | ዐሠር | ዐረፋ | ፏደደ | ፈለመ |
| ዐጥፍ | ዐመገ | ዐሥር | ዕራፊ | ፊደል | ፈለማ |
| ዐጠቀ | ዐማጋ | ዐፈነ | ዕርፍ | ፈደነ | ፋልማ |
| ዐጥቅ | ዐመድ | ዐፈና | ዐረፋ | ፋደት | ፈለቀ |
| ዐጨቀ | ዐመድ | ዐፈሠ | ዐረቀ | ፈወሰ | ፈለሰ |
| ዐጠረ | ዐሞድ | ዐፈሣ | ዕርቅ | ፈውስ | ፈላሻ |
| ዐጥር | ዐሟዳ | ዐፈረ | ዐረረ | ፈዘዘ | ፈነዳ |
| ዐጠረ | ዐምድ | ዐፋር | ዐራራ | ፈዛዛ | ፈንጅ |
| ዐጭር | ዐመጠ | ዐቀበ | ዕራሪ | ፈጠጠ | ፍናጅ |
| ዐይጥ | ዐመጥ | ዐቃቢ | ዐረር | ፈጣጣ | ፈንዜ |
| ዐየለ | ዐሞጭ | ዐቀደ | ዐረሰ | ፈጠጤ | ፈነጠ |
| ዐያሌ | ዐመል | ዐቅድ | ሰርሽ | ፈጠመ | ፌንጣ |
| ዐያል | ዐምሌ | ዐቅል | ዐረሰ | ፈጠም | ፈነጨ |
| ዐይን | ዐመመ | ዐቅን | ዐራስ | ፈጠነ | ፋነነ |
| ዐከበ | ዕመም | ዐቀፈ | ዐሰበ | ፈጣን | ፎነነ |
| ዐከከ | ዐምና | ዐቈረ | ዐስብ | ፎጠና | ፈነረ |
| ዕከክ | ዐመቀ | ዐረበ | ዐሰብ | ፎጠረ | ፈንታ |
| ዐከመ | ዐማራ | ዐረብ | ዐሽቦ | ፎጠረ | ፈጸመ |
| ዐኪም | ዐማሮ | ዐረቦ | ዐስበ | ፈየደ | ፈቀደ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ዐለበ (፫) | ዐመሰ | ዐርብ | ዐሳብ | ፋይዳ | ፈቃድ |
| ዐሊብ | ዐሙስ | ዐረገ | ዐሸለ | ፈየጠ | ፈቀቀ |
| ዐላባ | ዐምሳ | ዐረግ | ዐሸመ | ፍየል | ፎቃቃ |
| ዐልቦ | ዐመተ | ዐረደ | ዐሳር | ፈከከ | ፈቀረ |
| ዐለጠ | ዕመት | ዐራጅ | ዐሻሮ | ፈከረ | ፍቅር |
| ዐልጫ | ዐሞት | ዐራዳ | ዐሰት | ፎከረ | ፍርግ |
| ዐለለ | ዓመት | ዐረዘ | ዐተበ | ፉከራ | ፈረደ |
| ዐለላ | ዐማት | ዕሪዝ | ዐተመ። | ፎከተ | ፍርድ |
| ፈርጅ | ፈተተ። | ቅዳሜ | ቃጨለ | ቀለደ | ቅመም |
| ፍሪዳ | (ጸ) | ቄደረ | ቃጭል | ቀልድ | ቀመረ |
| ፈረጠ | ጸበበ (ጠ) | ቄደር | ቀጤማ | ቀላድ | ቀመር |
| ፈርጥ | ጸደይ | ቀደሰ | ቀጨማ | ቀለዘ | ቁማር |
| ፈረመ | ጸደቀ | ቅዳሴ | ቀጨሞ | ቄለዘ | ቀመሰ |
| ፊርማ | ጻድቅ | ቀውጢ | ቅጫም | ቀለጠ | ቅምሻ |
| ፈረቀ | ጽድቅ | ቀወሰ | ቀጠነ | ቀለጥ | ቀሚስ |
| ፈረቃ | ጸየፈ | ቀውስ | ቀጠና | ቀለጦ | ቀነዳ |
| ፈረሰ | ጸያፍ | ቀዎት | ቀጣና | ቄለጥ | ቀንድ |
| ፈርስ | ጸለየ | ቀዘበ | ቀጪኔ | ቄለጨ | ቀንዳ |
| ፍራሽ | ጸሎት | ቀዘባ | ቀጪን | ቄለጭ | ቀንጃ |
| ፍራሽ | ጽላት። | ቀዘዘ | ቀጠፈ | ቀለለ | ቅናጅ |
| ፈረስ | (ፀ) | ቅዛዛ | ቀጠፋ | ቀሊል | ቋንጃ |
| ፋሽገ | ፀሓይ | ቄዘመ | ቀጠረ | ቀላል | ቃንዛ |
| ፈሰከ | ፀነሰ (ጠ) | ቈዘማ | ቅጥር | ቄለለ | ቀናጣ |
| ፋሲካ | (ቀ-ቄ) | ቀዘነ | ቃጠረ | ቀለመ | ቄነጠ |
| ፋሽከ | ቄበበ | ቃዘነ | ቀጠሮ | ቀለም | ቄነጨ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ፋሽኮ | ቄባባ | ቀዘፈ | ቄጠረ | ቀላማ | ቄንጫ |
| ፍሽካ | ቃብዱ | ቄዘረ | ቄጥር | ቄለፈ | ቀኖና |
| ፈሶሌ | ቀበጠ | ቀጠበ | ቋጠረ | ቄልፍ | ቄነነ |
| ፈሰ | ቀበጠ | ቅጠባ | ቁጥር | ቀለሰ | ቀነፈ |
| ፈሳሽ | ቀበለ | ቄጠበ | ቋጨራ | ቀለሸ | ቀነረ |
| ፈሰሰ | ቀበሌ | ቄጠባ | ቄጠሰ | ቀለተ | ቀነሰ |
| ፈሰሴ | ቀበሎ | ቀጠጠ | ቄጢሶ | ቃልቻ | ቄነሰ |
| ፈተገ | ቅበላ | ቄጠጠ | ቀየደ | ቄመደ | ቄናስ |
| ፈተለ | ቀበና | ቄጣጥ | ቀየጠ | ቀመጠ | ቀነተ |
| ፈትል | ቀበረ | ቄጫጭ | ቀየመ | ቄመጠ | ቅናት |
| ፈቸለ | ቀብር | ቀጠለ | ቅያሜ | ቄመጥ | ቀሠጠ |
| ፈቸል | ቀበሮ | ቀጠላ | ቀየረ | ቄማጣ | ቀሠመ |
| ፈተነ | ቄበር | ቅጠል | ቀየሰ | ቄምጣ | ቀሠም |
| ፈተና | ቀደደ | ቅጥል | ቅያስ | ቋመጠ | ቀሠፈ |
| ፈተረ | ቀመደ | ቃጠለ | ቀለበ(፪) | ቀመለ | ቀሠረ |
| ፈተሸ | ቀድሞ | ቃጥላ | ቀለብ | ቅማል | ቀፈደ |
| ፍተሻ | ቅድም | ቃጠሎ | ቀልብ | ቀመመ | ፈቀድ |
| ቄፈነ | ቀረፋ | ረገበ | ረሞጫ | ሰጐደ | ሾከከ |
| ቄፈን | ቄረፈ | ርግብ | ራመመ | ሰገጠ | ሾካካ |
| ቀፈፈ(፫) | ቋርፍ | ረገደ | ረመሰ | ሰገጥ | ሰከለ |
| ቀፈረ | ቀረረ | ረገድ | ሮምታ | ሰጐጥ | ሰካላ |
| ቄፈረ | ቅራሪ | ረገዘ | ፈረደ | ሸጐጠ | ሳከላ |
| ቂፈራ | ቄረረ | ርጉዝ | ረፋድ | ሸጐጥ | ሸክላ |
| ቄፋሮ | ቄረሰ | ረገጠ | ረፈቀ | ሰገል | ሻክላ |
| ቀፈት | ቅርስ | ርግጫ | ረቀቀ | ሰገሌ | ሰኰመ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ቀቀለ | ቀረሸ | ርግጥ | ረቂቅ | ሰጐን | ሸከመ |
| ቀቀረ | ቄሸበ | ረገመ | ርሳስ። | ሸገነ | ሸክም |
| ቄቀር | ቄሰለ | ረገፈ | (ሰ-ሸ) | ሸገና | ሰከነ |
| ቀቀተ | ቄስል | ርጋፊ | ሰበብ | ሻገረ | ሰኰና |
| ቅቅት | ቀሰሰ | ርጋፎ | ሸበበ | ሻጐረ | ሽክና |
| ቋቅቻ | ቄሰሰ | ረድፍ | ሸበድ | ሻጐራ | ሸከፈ |
| ቀረበ | ቄሸሸ | ረዘመ | ሽብዳ | ሻገተ | ሰከረ |
| ቅርብ | ቄሻሻ | ረዥም | ሽባጥ | ሻጋታ | ስካር |
| ቄረበ | ቀስተ | ረጠበ | ሰበካ | ሰደበ | ስካር |
| ቄርባ | ቀስት | ርጥብ | ሰበካ | ስድብ | ሻከረ |
| ቄርዝ | ቋትል | ረጠጠ | ሰብል | ሰደደ | ሻካራ |
| ቀረጠ | ቄተመ | ረከበ | ሸበላ | ሰደድ | ሻኹራ |
| ቀረጥ | ቀተረ | ርካብ | ሰበን | ሰደፍ | ሰለበ |
| ቄረጠ | ቀትር | ረኸጥ | ሰበቀ | ሰዲቃ | ሰለበ |
| ቄራጥ | ቋቲሮ | ርኩም | ሰብቅ | ሰደረ | ሸለበ |
| ቄርዩ | ቀተራ | ረከሰ | ሰበረ | ሴደር | ሶለግ |
| ቄርኬ | ቃተተ | ርኩስ | ሸበረ | ሸውክ | ሸለገ |
| ቃረመ | ቄተቸ | ርካሽ | ሽብር | ሰወረ | ስልጆ |
| ቄረመ | ቄትቻ። | ርኩት | ሰበተ | ሰሐራ | ሹልዳ |
| ቀረና | (ረ) | ረኰተ | ስበት | ሰጠመ | ሰሊጥ |
| ቅራና | ረበበ | ረመደ | ሸበተ | ስጥር | ሽልጦ |
| ቄረነ | ረበደ | ርምጃ | ሽበት | ሰየመ | ሰለከ |
| ቄረን | ረባዳ | ርምድ | ሰገባ | ሰየፈ | ስልክ |
| ቄረኘ | ረብጣ | ረመጣ | ሸጐበ | ሰይፍ | ሾለከ |
| ቄራኛ | ረበከ | ረመጥ | ሰገደ | ሰከከ | ሰለለ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ቀረፈ | ረበተ | ርሚጦ | ሰገድ | ሲካካ | ሰለላ |
| ሰለለ | ሰሞን | ሰፈፍ | ሽርጥ | ተገነ | ተመገ |
| ሰላላ | ሸማኔ | ሸፈፈ | ሰረየ | ተገን | ተመመ |
| ሰላሌ | ሸመቀ | ሸፋፋ | ሸረከ | ችግኝ | ተመን |
| ሸለለ | ሰመረ | ሽፋፍ | ሸሪክ | ትግሬ | ተምር |
| ሽለላ | ሰመር | ሰፈረ | ሰርን | ቸገረ | ቱማታ |
| ሰለመ | ስሙር | ሰፈር | ሶረን | ችግር | ተምች |
| ሰላም | ሰማራ | ስፍራ | ሰርፍ | ችጋር | ተነነ |
| ሸለመ | ሸመተ | ስፍር | ሸረፈ | ተከዘ | ትንኝ |
| ሽልሜ | ሽመታ | ሸፈተ | ሽረፋ | ትካዜ | ቸነነ |
| ሰሌን | ሳንባ | ሽንታ | ሰረቀ | ተከዚ | ቸንች |
| ሰለፈ | ሰነባ | ሸፍት | ስርቅ | ተከለ | ቸፈገ |
| ሰልፍ | ሰነድ | ሽቅብ | ሰረረ | ተክል | ቸፈረ |
| ሸለፈ | ሰናዳ | ሸቀበ | ሸረረ | ቸከለ | ተረበ |
| ሰለቀ | ስንዴ | ሸቃባ | ሰሪቴ | ችካል | ተረብ |
| ሸለቆ | ሸንዳ | ሰቀዘ | ሸሸገ | ተኩላ | ተርብ |
| ሾለቅ | ሸነጠ | ሰቀጠ | ሴሰየ | ቸኩለ | ቶረበ |
| ሸለተ | ሽንጥ | ሰቃጢ | ሲሳይ | ችኩላ | ተረከ |
| ሰለታ | ሰንጢ | ሸቀጠ | ሰሰለ | ተከነ | ታሪክ |
| ስልት | ስናጭ | ሸቀጥ | ሴሰነ | ተኩነ | ተረፈ |
| ስልቻ | ስንኝ | ስቈታ | ሴሰን | ትኳን | ትራፊ |
| ሰለቸ | ሰነፈ | ሰቀለ | ሴሰኛ | ተከረ | ተረፍ |
| ስልቹ | ሰነፍ | ሰቀላ | ሾተለ | ተኰረ | ተረረ |
| ሸለተ | ሸነፈ | ሸቀን | ሾተል | ተኳር | ተራራ |
| ሸለታ | ሲናር | ሰቀቀ | ሳተነ | ተኰሰ | ቸረረ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ሰመግ | ስናር | ሸረበ | ሳተና | ተኰስ | ተረተ |
| ሰመኀ | ስንት | ሹራብ | ሳተፈ | ታከተ | ተረት |
| ሸመደ | ሸንት | ሹርባ | ሸተረ | ተልባ | ቸሰረ |
| ስምዛ | ስፌድ | ሾርባ | ሻተረ | ተለለ | ተተገ |
| ሰመጠ | ሻፈደ | ሰረገ | ሰታቴ | ተለላ | ታታረ |
| ሸመጥ | ሸፈጠ | ሰርግ | ሸተተ | ተላላ | ቸቸረ። |
| ሰማይ | ሸፍጥ | ሰርዶ | ሻተተ። | ተለመ | (ጸ) |
| ሸመመ | ሽፋል | ሰረጀ | (ተ-ቸ) | ታልማ | ጳጳስ። |
| ሸማማ | ሸፈነ | ሸረጠ | ተገበ | ትልም | (ፐ) |
| ሰመነ | ሰፈፈ | ሽርጥ | ተግብ | ቸለሰ | ፓሪስ። |

## ምዕራፍ ፫።

| ያራት ፊደል ግስ (በደጊመ ቃል)። | | | | |
|---|---|---|---|---|
| (አ) | ገውጋዋ | ገረገረ | ደነደነ | ዘምዘም |
| አፍአዊ። | ገዘገዘ | ገራገራ | ደንዳና | ዘነዘና |
| (በ) | ገዝጋዛ | ግርግር | ደንዳኔ | ዘፈዘፈ |
| በገበገ | ጐዘጐዘ | ጐረጐረ | ድንድን | ዘቀዘቀ |
| ደበደበ | ጕዝጓዝ | ጕርጓሮ | ደፈደፈ | ዥቀዥቀ |
| በዘበዘ | ገጠገጠ | ገሸገሸ | ድፍድፍ | ዘረዘረ |
| ብዝበዛ | ጐጠጐጠ | ገተገተ | ዶፈዶፈ | ዝርዝር |
| በጠበጠ | ገጨገጨ | ጐተጐተ | ዶፍዷፋ | ዝርዝር |
| ብጥበጣ | ገለገለ | ጕትጐታ | ደቀደቀ | ዠረዠረ |
| ቦጠቦጠ | ግልጋሎ | ገችጋች። | ደረደረ | ዘተዘተ። |
| ቦከቦከ | ገላገለ | (ደ-ጀ) | (ወ) | (ጠ-ጨ) |
| በለበለ | ግልግል | ደብደበ | ወዘወዘ | ጠበጠበ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ቦፈቦፈ | ግልግል | ድብደባ | ውዝዋዜ | ጥብጠባ |
| በቀበቀ | ግልግል | ድብደባ | ወጠወጠ | ጥብጣብ |
| ቦረቦጭ | ጐለጐለ | ድብዳብ | ወከወከ | ጨበጨበ |
| በረበረ | ጒልጓሎ | ደብዳቤ | ወለወለ | ጭብጨባ |
| በርበራ | ገመገመ | ደባደቦ | ወላወለ | ጠዘጠዘ |
| በርበሬ | ግምገማ | ጀብጀባ | ወነወነ | ጠለጠለ |
| በርበር | ገነገነ | ደገደገ | ወረወረ | ጠልጣላ |
| ብርበራ | ግንገና | ደግዳጋ | ውርወራ | ጦለጦለ |
| ብርብራ | ጐነጐነ | ድግድግ | ወሰወሰ | ጦጧላ |
| ቦረቦረ | ጒንጒን | ዶገዶገ | ወተወተ | ጨለጨለ |
| በሰበሰ | ገሠገሠ | ደዘደዘ | ውትወታ። | ጠመጠመ |
| በተበተ። | ግሥገሣ | ደከደከ | (ዘ-ዠ) | ጥምጥም |
| (ገ-ጐ) | ጐሠጐሠ | ደለደለ | ዘበዘበ | ጨመጨመ |
| ገበገበ | ገፈገፈ | ደልዳላ | ዝብዘባ | ጨምጫሞ |
| ገብጋባ | ጐፈጐፈ | ድልድል | ዘጠዘጠ | ጠፈጠፈ |
| ጐበጐበ | ጐፍጓፋ | ዶለዶለ | ዘጥዛጣ | ጠፍጣፋ |
| ገደገደ | ገረገበ | ዶልዷላ | ዠጠዠጠ | ጥፍጥፍ |
| ግድግዳ | ገረገመ | ዶልዷሌ | ዘከዘከ | ጠፈጠፍ |
| ጐደጐደ | ግርግም | ዶለዶመ | ዘለዘለ | ጨፈጨፈ |
| ጐድጓዳ | ጐረጐመ | ዶልዷማ | ዠለዠለ | ጨፈጨፍ |
| ጒድጓድ | ጐረጐማ | ደመደመ | ዘመዘመ | ጠቀጠቀ |
| ጠቃጠቆ | ኰሰኰሰ | መዘመዘ | ነቀነቀ | ቀዠቀዠ |
| ጨቀጨቀ | ኰሸኰሸ | ምዝምዝ | ነሰነሰ። | ቀዥቃዣ |
| ጭቅጭቅ | ኰሸኰሸ | መጠመጠ | (ሠ) | ቀጠቀጠ |
| ጠረጠረ | ከተከተ | ሚጥሚጣ | ሠረሠረ | ቀጥቃጣ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ጥርጥር | ክትክታ | ሞጠሞጠ | ሠረሠር | ቅጥቅጥ |
| ጥርጣሪ | ኰተኰተ። | ሞጥሟጣ | ሥርሠራ። | ቈጠቈጠ |
| ጠራጠር | (ለ) | መጨመጨ | (ፈ) | ቈጥቋጦ |
| ጨረጨረ | ለበለበ | መጭማጫ | ፈገፈገ | ቀጨቀጨ |
| ጨርጨር | ልብለባ | መከመከ | ፈደፈደ | ቀጨቀጭ |
| ጠሰጠሰ። | ለገለገ | መክማካ | ፍድፉጅ | ቈጨቈጨ |
| (ከ-ኰ) | ለግላጋ | መለመለ | ፈጠፈጠ | ቈጭቋጫ |
| ከበከበ | ለደለደ | ምልመላ | ፈጨፈጨ | ቀለቀለ |
| ኰበኰበ | ለድላዳ | መነመነ | ፈከፈከ | ቀለቀል |
| ኵብኵባ | ለውላዋ | መንማና | ፎከፎከ | ቀልቃላ |
| ከውካዋ | ለዘለዘ | መቀመቀ | ፈለፈለ | ቀለቀሎ |
| ከለከለ | ለጠለጠ | ሞቀሞቀ | ፍልፈፍ | ቀላቀለ |
| ኰለኰለ | ሎጥሏጣ | መቅመቆ | ፈነፈነ | ቅልቅል |
| ከመከመ | ለከለከ | መረመረ | ፈቀፈቀ | ቈለቈለ |
| ከምከም | ለመለመ | ምርምር | ፈረፈረ | ቈለቈል |
| ኰመኰመ | ልምላሜ | ምርመራ | ፈረፈር | ቈልቈል |
| ከነከነ | ለፈለፈ | መረመረ | ፍርፋሪ | ቈልቋል |
| ክንካኔ | ልፍለፋ | ሞረሞረ። | ፈሰፈሰ | ቀመቀመ |
| ከፈከፈ | ለቀለቀ | (ነ) | ፎሽፏሻ | ቀምቀሞ |
| ኰፈኰፈ | ልቅለቃ | ነበነበ | ፈተፈተ | ቀነቀነ |
| ከረከረ | ለሰለሰ | ነገነገ | ፍትፍት። | ቅንቅን |
| ክርክር | ልስልስ | ነዘነዘ | (ቀ) | ቈነቈነ |
| ክርክር | ለሸለሸ | ነዝናዛ | ቀበቀበ | ቈንቋና |
| ክርክር | ለተለተ | ንዝናዜ | ቅብቃብ | ቀፈቀፈ |
| ከርከሮ | ለትላታ። | ንዝንዝ | ቅብቅብ | ቈፈቈፈ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ኰረኰረ | (መ) | ነጠነጠ | ቈበቈበ | ቀረቀበ |
| ኵርኰራ | መገመገ | ነጨነጨ | ቀውቃዋ | ቀርቃባ |
| ከሰከሰ | መደመደ | ነጭናጫ | ቀዘቀዘ | ቀረቀረ |
| ከስከሶ | መደመድ | ነከነከ | ቀዝቃዛ | ቅርቃር |
| ከሸከሸ | ሞደሞደ | ነፈነፈ | ቅዝቃዜ | ቈረቈረ |
| ቈረቈር | ረመረመ | ሸጠሸጠ | ሰቀሰቀ | ተፈተፈ |
| ቈርቈሮ | ረፈረፈ | ሰከሰከ | ሰቅስቆ | ትፍትፍ |
| ቊርቊራ | ረቀረቀ | ሶከሶከ | ሸቀሸቀ | ቸፈቸፈ |
| ቀሰቀሰ | ረሰረሰ | ሸከሸከ | ሸረሸረ። | ችፍችፍ |
| ቅስቃሴ | ረተረተ። | ሰለሰለ | (ተ-ቸ) | ተረተረ |
| ቈሰቈሰ። | (ሰ-ሸ) | ሰልሳላ | ተበተበ | ተረተር |
| (ረ) | ለበሰበ | ሸልሸል። | ቸበቸበ | ቸረቸረ |
| ረበረበ | ሰበሰብ | ሶመሶመ | ቸብቸቦ | ችርቻሮ |
| ርብራብ | ስብሳብ | ሱምሶማ | ተገተገ | ተሰተሰ |
| ርብርብ | ሸበሸበ | ሸመሸመ | ተከተከ | ቸሰቸሰ። |
| ረገረገ | ሽብሸባ | ሽምሽም | ቸከቸከ | |
| ረግረግ | ሽብሽቦ | ሰነሰነ | ተለተለ | |
| ረዘረዘ | ሰገሰገ | ሸነሸነ | ተመተመ | |
| ርዝራዥ | ሸገሸገ | ሽንሽን | ቸመቸመ | |
| ረጠረጠ | ሸደሸደ | ሰፈሰፈ | ችምችም | |
| ረከረከ | ሸውሻዋ | ሰፍሳፋ | ተነተነ | |
| ርክርክ | ሰጠሰጠ | ሸፈሸፈ | ትንተና | |

(ፈተና)

ራሴን በራሴ

ከላንቆላጳላጠሰኹት ማን

ያንቆላጳላጥስልኛል።

## ምዕራፍ ፬።

የ፫ና ያ፬ ፊደል ግስ በሥሩ ልማድ ባዕድ በጫፉ ዝርዝር ምእላድ ሲገባበት ፬ና ፭ ፮ና ፯ና ፱ ፲ም ይኾናል። ይኸውም እንዲኸ ነው፡

ጠየቀ

ተጠየቀ።

መረመረ

ተመረመረ

አስመረመረ

ተመራመራቸው

አላስመረመረም

አስመርምሯቸዋል

አያስመረምራቸውም።

# ክፍል ፱።

## ምዕራፍ ፩።

ዐጭር የርባታ መቅድምና ዐዋጅ። (ተረት) ነገር ከሥሩ ውሃ ከጥሩ። ረቢሕ፤ ረቢሖት (ረብሐ ይረብሕ ይርባሕ) መርባት መብዛት። ርባሕ፤ ርባ ርባታ አረባብ አበዛዝ።

ርባታ በ፫ ዐይነት ክፍል የከፈላል በወንድና በሴት ባንድና በብዙ፥ በቅርብና በሩቅ፤ መደበኛው ወንድና ሴት ነው አንድና ብዙ ቅርብና ሩቅ ከዚያው ይገባሉ። በርባታም ውስጥ ፫ት ጊዜ አለ ያለፈና ያኹን የሚመጣ። ያማርኛ ርባታ መደቡ ፱ ብቻ ነው ፮ቱ ያንዳንድ ፫ቱ የብዙ። ፮ቱ የቅርብ ፫ቱ የሩቅ። የብዙዎቹ ወንዶችና ሴቶች አንቀጻቸውም ዝርዝራቸውም በጥፈትና ባነጋገር ፩ ቃል ኹኖ ኹለቱ ስላንድ ይቈጠራል እንደ ግእዙ ልዩነት የለውም። ያንቱታውም ዝርዝርና አንቀጽ እንደ አነና እንደ ንሕነ ወንድና ሴት ያስተባብራል።

በባሕርይ ስም ፈንታ የሚነገር ፱ኙ ያካል ስም ወይም ቅጽልና ዐጸፋ የርባታ መደብ ከነሥሩና ከነምንጩ። ርኢስ፤ ርኢሶት (ርእሰ ይርእስ ይርአስ) ራስ መኾን። ርእስ፤ ርስ ራስ የናላ ቅል። ባለቤት ጌታ ገዥ አዛዥ ራሱን የቻለ ለራሱ የበቃ ለብቻው የቆመ የተለየ እከሌ የሚባል ወይም ርሱው ራሱ እኔ ነኝ የሚል ነባቢ አካል። ባለቤት ሲባል ባለ ነፍስን፤ ቤት፥ ከራስ ጠጕር እስከግር ጥፍር ያለ ሥጋን በተገናኝ ፍጹም ሰውነት አካልን ቁመትን ነባቢነት ያሳያል። ርባታውና ዝርዝሩም ዕጥፍ ድርብ ኹኖ በስምነቱ ላይ አካልና አንቀጽ እያሳየ በውእቱ መንገድ ይሄዳል። የግስ መብቀያ ሥር መሠረቱ ባንድ በፍጹም በሩቅ ወንድ ስም ስለ ኾነ፥ ርባታውም በዚያው በሩቅ ወንድ በበቀለበት ዐምድ ይዠመራል። ይኸውም ልማድ፥ ርባታን በሩቅ ወንድ መዠመር የግእዝ ብቻ ነው፤ ሌላው ቋንቋ ግን በራሱ በቅርቡ እኔ በሚለው ይዠምራል።

አንዳንዶች።

(ሩቅ ወንድ)

**ርሱ እሱ ራሱ ቅሉ ባለቤቱ እንቶ ያ።**

(ሩቅ ሴት)

**ርሷ እሷ ራሷ ቅሏ ባለቤቷ (እንትኩ) ያች።**

(የቅርብ ወንድ)

**ርስኽ እስኽ ራስኽ ቅልኽ ባለቤትኽ አንተ።**

(ቅርብ ሴት)

## ርስሽ እስሽ ራስሽ ቅልሽ ባለቤትሽ አንቺ ቺ።

(ነባቢ ወነባቢት) ወንድና ሴት)

## ርሴ እሴ ራሴ ቅሌ ባለቤቴ እኔ፣ እኔው።

(ክቡርና ክብርት ወንድና ሴት)

## ርስዎ ኹ እስዎ ኹ፤ ራስዎ ኹ፤ ቅልዎ ኹ፤ ባለቤትዎ ኹ፤ አንቱ

(ብዙዎች ሩቆች ወንዶችና ሴቶች ወይም አንዳንዶች የሩቅ ወንድና ሴት በቅርብ ርስዎና አንቱ የሚባሉት)

## ርሳቸው እሳቸው ራሳቸው ቅላቸው ባለቤታቸው እኒያ እሊያ።

(ቅርቦች ወንዶችና ሴቶች)

## ርሳችኹ እሳችኹ ራሳችኹ ቅላችኹ ባለቤታችኹ እና(ላ) ንተ ተ።

(ነባቢያን ወነባብያት) ወንዶችም ሴቶችም)

## ርሳችን እሳችን ራሳችን ቅላችን ባለቤታችን እኛ።

ከነዚኹ ደግሞ ለመደብነት ተመርጠው የወጡ አንዳንድ የተለዩ ስሞች ወይም የመደበኛ ስም ምትኮች።

| | |
|---|---|
| ርሱ<br>ርሷ | ርሳቸው። |
| አንተ<br>አንቺ | እና(ላ) ንተ። |
| እኔ<br>ርስዎ | እኛ። |

(ሐተታ) እኔ እኛ ከሚለው በቀር ፺ቱ ስም ተጠሪ ወኪል ይባላል ቶሎ እንደ ማለት ነው። ከ፺ቱ ደግሞ ቅርብ ቅርቡ በተጠሪነት ላይ ሰሚ ወይም ሰሚና ተጠሪ ይባላል። እኔና እኛ ግን ለብቻው ጠሪ ተናጋሪ ይባላ ዋና እንደ ማለት ነው። ርስዎ ማለት ቅርብ ኹኖ ምንም ካንዳንዶች ጋር ቢቈጠር አንቀጹ የብዙና የሩቅ ነውና የቅርብ ሩቅ መስሎ ከርሳቸው ይገባል። ርሱና ርሷ ርሳቸው እኒኽ ፫ቱ ደግሞ የሩቅ ብቻ ኹነው አይቀሩም የቅርብ ሩቅም ይኾናሉ ጥቂት ፈቀቅ ብሎ በዙሪያ በኋላ በስተቀኝና በስተግራ ያለ፥ ዘወር ዘወር ብሎ ሊያዩት ሊሰሙትና ሊናገሩት ሊጠሩትና ሊጠቅሱት የሚቻል፥ በአንተ አንጻር ርሱ ይባላል። (ርሱ ራሱ በማለት ፈንታ እን እየጨመሩ እርሱ እራሱ ማለት

እርስት እሩብ እንደሚሉት ያለ ጸያፍ ነው። እሱ ማለት ግን ርእስ ካለው ከ፲ቱ ፊደላት ርን ውጦና ጐርዶ ነውና ርትዕ እንጂ ጸያፍ አይባልም)። አንተና አንች እናንተና ርስዎ እኒኽ ፬ቱ በግንባር በአንጻር ፊት ለፊት ያሉ፥ ባይን ተቀምለው በጣት ተጠንቈለው የሚታዩ የሚነገሩ ቅርቦች አጠገቦች ወይም የቅርብ ቅርቦች ይባላሉ። እኔና እኛም እነዚኽ ኹለቱ ቅርቦች ስለ ኾኑ አንተንና የአንች የናንተ አንጻር ናቸው። ዳግመኛም በነዚኽ በዘጠኙ ላይ በሥርና በጫፍ እየገቡ የቋንቋን ስልት የነገርን ብልት፥ የርባታውን ዐምድ መንገድና አካሄድ ለይተው ለያይተው የሚያሳዩ አገባቦችና ዝርዝሮች አሉ፤ ዝርዝሮቹ ኋላ ይመጣሉ አገባቦቹና ግቢያቸውም ከነስማቸው እሊኽ ናቸው።

| (አገባብ) | (ገቢ) | (ስም) |
|---|---|---|
| የ | የርሱ | ጠቃሽ። |
| ለ | ለርሱ | አቀባይ። |
| በ | በርሱ | ማድረጊያ። |
| ስለ | ስለ ርሱ | ምክንያት። |
| ከ (ተ) | ከርሱ | መነሻ። |
| ወደ | ወደ ርሱ | መገሥገሻ። |
| እ | ዘንድ } | እርሱ ዘንድ፤ እስከ ርሱ፤ መድረሻ |
| ን | ርሱ } | (የገቢር) ተሳቢ። |

(ሐተታ) መገሥገሻና መድረሻ አንድ ወገን ናቸው፤ ይተባበራሉ። ርሱ ዘንድ እስከ ርሱ በማለት ፈንታ እ ቀርቶ ከርሱ ዘንድ ከሱ ይባላል፤ ይኸውም እና ከ አንድ ወገን ስለ ኾኑ ነው (ማስረጃ) የተጠማ ከፈሳሽ፥ የተበደለ ከነጋሽ። እና ከኹለቱም ከእስከ ተከፍለው የመጡ የእስከ ምልክት ናቸውና እ በሺዋ ዐማርኛ መገሥገሻና መድረሻ መኾኑ ስለዚኽ ነው። መድረሻነቱ በቦታው ተነግሯል መገሥገሻ ሲኾን፤ እቤት ገባ እደጅ ወጣ። እ ማለት ስከን ጐርዶ ነው ከ ማለትም እስን ጐርዶ ነው በተገናኝ ኹሉም እስከ ማለት ነው። አንዳንድ ጊዜም እንደ ከ በ ይኾናል፤ እግቢም እውጪም ፈልጌ ዐጣኹት። ከ መነሻና በ ሲኾን አገባብነቱ ከእም ጋራ እንጂ ከእስከ አይስማማም።

ከደቂቅ ርባታ የወጣ የአካላዊ ስም ዝርዝርና ነባር አንቀጽ ከነዘማቹ። የዘማች ዝርዝር የሩቅ ኀላፊ፥ ግእዝና ራብዕ (ዐየለ በረታ)፤ ትንቢቱም የግእዙ፥ ሳድስ የራብዕ ራብዕ (ያያል ይበረታ) ያሰኛል የብዙዎቹ ግን ኹሉም ካዕብ ነው።

| | (አካላዊ ስም) | (ዝርዝር) | (ነባር አንቀጽ) | (ዘማች አንቀጽ) |
|---|---|---|---|---|
| ውእቱ | ርሱ | ው | ነው። | ገደለ። |
| | ርሷ | ት ች | ናት ነች። | ገደለች። |
| | አንተ | ኽ ክ | ነኽ። | ገደልኽ ክ። |
| | አንቺ ቺ | ሽ | ነሽ። | ገደልሽ። |
| | እኔ | ኝ | ነኝ። | ገደልኹ ኩ። |
| | ርስዎ (አንቱ) | ዎ ኹ | ነዎ (ነኹ) | ገደሉ (ልኹ) |
| | ርሳቸው | ቸው | ናቸው። | ገደሉ። |
| | እና (ላ)ንተ | ችኹ | ናችኹ። | ገደላችኹ። |
| | እኛ | ነ ን | ነነ ነን። | ገደልነ ን። |

ያማርኛ ግስ ምሉ ሲኾን በ፰ አዕማድ ጐደሎ ሲኾን ከ፰ በታች እስከ ፩ና እስከ ፪ ድረስ በጐደግሎነት ይረባል። ከ፰ቱ አዕማድ ዋነኞቹ ፭ ናቸው፤ ፫ቱ ግን ድርቦችና ተወራጆች ወይም ተቀጥሎች ይባላሉ ምስጢራቸውም ነገር ማጽናናት ማበርታት ነው። ስለዚኽም ለ፰ቱ አዕማድ ልማድ የሚባሉ ፬ ለከቶች አሏቸው፤ እሊኹም ራብዕ ስሯጽ እስ ተ አ ናቸው። የአዕማዱም ረድፍና ተራ በየስክተቱና በየስሙ ይኽ ነው። (ዘር ወይም ሥረ ነገር) ቀቢር፤ ቀቢሮት። መቅበር መቀባበር።

| | | |
|---|---|---|
| ፩ኛ፤ (ድርብ) | ቀበረ ቀባበረ | አድራጊ። |
| ፪ኛል፤ | አስቀበረ | አስደራጊ። |
| ፫ኛ፤ | ተቀበረ | ተደራጊ። |
| ፬ኛ፤ (ድርብ) | ተቃነረ ተቀባበረ | ተደራራጊ። |
| ፭ኛ፤ (ድርብ) | አቃበረ አቀባበረ | አደራራጊ። |

ተቀባበረ ማለት ድርብነቱ ለ፫ኛው ዐምድ ለተደራራጊውም ነው እንጂ ላ፬ኛው ብቻ አይዶለም፤ ይኸውም ተሰበረ ተሳባበረ ብሎ ተሰባበረ በማለት ይረዳል። የ፰ቱ አዕማድ ስምና ግብር ገቢር ተገቢሮ

ወይም ማድረግ መደረግ ተብሎ በ፱ ክፍል ይወሰናል። ፩ኛው ፪ኛው ዐምድ ድርቦቻቸውም ሳይቀሩ እነዚኽ ፪ቱ ፩ወገን ኾነው በገቢርነት ይጠራሉ። ፫ኛውና ፬ኛው ከነድርባቸው እኒኽ ፫ቱ ደግሞ በተገብሮነት ይጠራሉ። ዳግመኛም ተደራራጊ አንቀጽ አድራጊነትም አለውና ተቃበረ ማለት ባንድ ወገኑ ከነቀበረ ይስማማል። ፫ኛም ግሱ እንደ መጣና እንደ ሄደ ያለ ዐጕል አንቀጽ ሲኾን ስሙና ክፍሉ ከተደራራጊነት ይገባል። አንቀጻቸውም ኀላፊና ትንቢት ተብሎ በ፪ ዐይነት ይከፈላል ለ፪ቱ ደግሞ በ፪፪ ስልት አላቸው ፫ኛው አንቀጽ ትእዛዝም ከትንቢት ይገባል።

## (ኀላፊ አንቀጽና ትንቢት አንቀጽ)

| (ኀላፊ) | (ያኹንና ትንቢት) | (ትእዛዝ አንቀጽ) |
|---|---|---|
| ፩ኛ - ከፈለ | ፪ኛ - ይከፍል። | ፫ኛ - ይክፈል። |
| - ከፍሏል (ከፍሎ አል ነበር) | ይከፍላል | |

(ሐተታ) ከፍሏል ማለት ዘሩ ከከፈለና ከሀሎ ያውም ከቦዝ አንቀጽና ከኀላፊ አንቀጽ እንደ በቅሎ የተዴቀለ ቅልቅል ድብልቅ ስለ ኾነ ዘንድና ትእዛዝ የለውም። ከፈለ ግን መደበኛ አንቀጽ ነውና ኹለቱም አሉት፤ ትንቢቱ ዘንድ ሲወድቅበት ማሰሪያነቱ ይለቅና ርሱ በሌላ አንቀጽ ይሳባል። ዘንድ ከኀበ የወጣ የውል ቃልና የውል አገባብ ነው፤ ፍቺውም እንዲና ሊ ናቸው። ይከፍል ዘንድ ሲል እንዲከፍል ሊከፍል ያስኛል። በሌላ አንቀጽም ሲሳብ፤ ብድር ይከፍል ዘንድ አይወድም ወይም ፈቃዱ ይከፍል ዘንድ ነው ያሰኛል። በኀላፊ አንቀጽ ሲገባ ከሄደ ዘንድ ብሎ ስለ ሄደ ያሰኛል። በስም እየገባ ከርሱ ዘንድ ሲል ቅርብና አጠገብ ያሰኛል። በዘንድ ፈንታ ነበር ይኾናል፤ ሲገቡ ምኞትና ጠጠት ጥርጥር ያሳያል። ይከፍል ነበር ምኞት። ይከፍል ይኾና፤ ጥርጥር። ይከፍል ይኾን ሲል፤ ወይም ብቻውን ይከፍል ማለት ደፍቶ ሲናገሩት ጥያቄ ይኾናል። በቀረው ግን ድር ቢያብር አንበሳ ያስር ዥብ ሲወጉ ባህያ ይጠጉ፤ ሲገዙ ይገዙ ሴት ታውቅ በወንድ ያልቅ እያለ በየፊቱ ያስራል። ፫ኛው አንቀጽ ትእዛዝ መባሉ ከላይ ወደ ታች ሲነገር ነው ከታች ወደ ላይ ሲነገር ግን ልመናና ጸሎት ይባላል። ከፍሏል ማለትም ኀላፊ አንቀጽ ሲኾን፥ የትንቢቱ ሥር ይ ሲጨመርበት ተቀአይ የሌለው ዐጕል ትእዛዝ እየኾነ ባጓጕል መንገድ ይከፍሏል ያድሏል ያሰኛል። ምሥጢሩና ስልቱ ዐጕል ባይኾን ግን የከፍሏል ትንቢት ይባል ነበር።

ድርቡሾ አዕማድ ሲገሰሱ እንደ መደበኞች ዘንድና ትእዛዝ አላቸው

ትንቢታቸው ኹሉን ይደርባል።

| (ኀላፊ) | (ትንቢት) | (ዘንድ) | (ትእዛዝ) |
|---|---|---|---|
| ከፋፈለ | ይከፍላል | = | = |
| ከፋፍሏል | ይከፋልፍላል | | |

ግስ ኹሉ በ፱ መደብ ሲረባ ከፈለ ከፍሏል ከፍሎ ነበር እንዳልነው ኹሉ ኹለቱ ጽንዖች አይቀሩም። አኹን ለጊዜው ግን አልና ነበር አንድ ስለ ኾኑ ነበርን ትተን አልን ብቻ ይዘን እንኼዳለን ነበርም ጥቂት ልዩነት ስላለው ኋላ ከቦዝ አንቀጽ ጋራ ይነገራል። ርባታም ዐቢይና ደቂቅ ተብሎ በ፪ ስሞች ይጠራል ደቂቅ የተባለም የስምና የግብር የነባር አንቀጽ ርባታ ነው ያውም ከ፱ መደብ አይወጣም። ፊደል ኹሉ የዐና ሀሐኀ በፊቱ ሲኾኑ እነሱን ጐርዶ ራብዕ ይኾናል ይኸውም በትንቢት መነሻ በየና በተ ይታወቃል ከፍሏል ይከፈላልም ያስረዳል።

## (ዐቢይ ርባታ)

### ዐዋቂ ፤ዐዊቆት (ዖቅ የዐውቅ ይዑቅ) ፤ ማወቅ መረዳት።

| | (ኀላፊ) | (ትንቢት ዘንድ) | (ትእዛዝ) |
|---|---|---|---|
| (ርሱ) | ዐወቀ | ያውቅ | ይወቅ። |
| (ጽንዕ) | ዐውቋል | ያውቃል | |
| (ርሷ) | ዐወቀች | ታውቅ | ትወቅ። |
| | ዐውቃለች | ታውቃለች | |
| (አንተ) | ዐወቅኽ | ታውቅ | ዕውቅ። |
| | ዐውቀኻል | ታውቃለኽ | |
| (አንች) | ዐወቅሽ | ታውቂ | ዕወቂ። |
| | ዐውቀሻል | ታውቂያለሽ | |
| (እኔ) | ዐወቅኹ ኹ | ዐውቅ | ልወቅ። |
| | ዐውቂያለኹ | ዐውቃለኹ | |
| (አንቱ) | ዐወቅኹ | ታውቁ | ዕወቁ። |
| | ዐውቀ኿ል | ታውቃለኹ | |

| (ርስዎና ርሳቸው። ብዙዎቹም የሩቅ ወንዶችና ሴቶ) | | | |
|---|---|---|---|
| (ርሳቸው) | ዐወቁ | ያውቁ | ይወቁ። |
| | ዐውቀዋል | ያውቃሉ | |
| (እናንተ) | ዐውቃችኹ | ታውቁ | ዕወቁ። |
| | ዐውቃችኂል | ታውቃላችኹ | |
| (እኛ) | ዐወቅነ | እናውቅ | ዕንወቅ። |
| | ዐውቀናል | እናውቃለን | |

እስከዚኽ መደብ ይባላል ከዚኽ ቀጥሎ ዝርዝር ነው ከጽንዑ በቀር ራሱ ፳፩ ይኾናል። የለና የበ ዝርዝሮች ለትና በትም እንደ እልና እንደ ነበር ከዝርዝር ጋራ ይዘምታሉ ለት የበኀ በት የክፉ ነው። ይኸም ዐውቀው፥ ብሎ ዐወቀለት በት፤ ዐውቆለታል በታል። ያውቅበታል በት፤ ለታል በታል እያለ መሄዱን ያሳያል።

| (ዝርዝር ርባታ ርሱ የተባለው ሩቅ የተባለው ሩቅ ከርሱ እስከኛ ፱ኙን መደብ በተራ ሲያውቃቸው) | | | |
|---|---|---|---|
| (ርሱን) | ዐወቀው (ለት በት) | ያውቀው | ይወቀው። |
| | ዐውቆታል | ያውቀዋል | |
| (ርሷን) | ዐወቃት | ያውቃት | ይወቃት። |
| | ዐውቋታል | ያውቃታል | |
| (አንተን) | ዐወቅኽ ሽ | ያውቅኽ፤ ሽ | ይወቅኽ ሽ። |
| (- ችን) | ዐውቆኻል ሻል | ያውቅኻል ሻል | |
| (እኔን) | ዐወቀኝ | ያውቀኝ | ይወቀኝ። |
| | ዐውቆኛል | ያውቀኛል | |
| (አንቱን) | ዐወቀኹ፤ ዎ | ያውቅኹ፤ ዎ | ይወቅኹ ቆ። |
| (ርስዎን) | ዐወቆኂል፤ ዎታል | ያውቅኂል፤ ዎታል | |
| | ዐውቃቸው | ያውቃቸው | ይወቃቸው። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| (ርሳቸውን) | ዐወቋቸዋል | ያውቃቸዋል | |
| (እናንተን) | ዐወቃችኹ | ያውቃችኹ | ይወቃችኹ። |
| | ዐወቋችኋል | ያውቃችኋል | |
| (እኛን) | ዐወቀን ነ | ያውቀን | ይወቀን |
| | ዐውቆናል | ያውቀናል | |

| ርሷ የተባለች ሩ (ቋ) ቂቱ ከርሱ እስከኛ ፱ኙን ዘርዝራ ስታውቅ። | | |
|---|---|---|
| ዐወቀችው | ታውቀው | ትወቀው። |
| ዐውቃዋለች | ታውቀዋለች | |
| ዐወቀቻት | ታውቃት | ትወቃት። |
| ዐውቃታለች | ታውቃታለች | |
| ዐወቀችኽ፤ ሽ | ታውቅኽ፤ ሽ | ትወቅኽ ሽ። |
| ዐውቃኻ (ሻ) ለች | ታውቅኻ (ሻ) ለች | |
| ዐወቀችኝ | ታውቀኝ | ትወቃቸው። |
| ዐውቃቸዋለች | ታውቃቸዋለች | |
| ዐወቀቻችኹ | ታውቃችኹ | ትወታችኹ። |
| ዐውቃችኋለች | ታውቃችኋለች | |
| ዐወቀችን | ታውቀን | ትወቀን። |
| ዐውቃናለች | ታውቀናለች | |

| አንተ የተባለ ቅርቡ ፳ቱን መደብ ዘርዝሮ ሲያውቅ። | | |
|---|---|---|
| ዐወቅኸው ኻት | ታውቀው ቃት | ዕውቀወ (ቃት) |
| ዐውቅኸዋ (ኻታ) ል | ታውቀዋ (ቃታ) ለኽል | |
| ዐወቅኸኝ | ታውቀኝ | } ዕወቀኝ። |

| | | |
|---|---|---|
| ዐውቀኽኛል | ታውቀኛለኽ | |
| ዐወቅኻቸው | ታውቃቸው | } ዕወቃቸው። |
| ዐውቀኻቸዋል | ታውቃቸዋለኽ | |
| ዐወቅኽን | ታውቀን | } ዕወቀን። |
| ዐውቀቅኽናል | ታውቀናለኽ | |

| አንች የተባለ ቅር(ቧ) ቢቱ ፏቱን መደቦች ዘርዝራ ስታውቅ። | | |
|---|---|---|
| ዐወቅሽ ሻት | ታውቂው ያት | ዕወቂው ያት |
| ዐወቅሽዋ(ሻታ)ል | ታውቂዋ (ያታ) ለሽ | |
| ዐወቅሺኝ | ታውቂኝ | } ዕወቂኝ። |
| ዐውቀሽኛል | ታውቂኛለሽ | |
| ዐወቅሻቸው | ታውቂያቸው | } ዕወቂያቸው። |
| ዐወቀሻቸዋል | ታውቂያቸዋለሽ | |
| ዐወቅሽን | ታውቂን | } ዕወቂን። |
| ዐውቀሽናል | ታውቂናለሽ | |

| እኔ ባይ ዃቱን መደብ ዘርዝሮ ሲያውቅ። | | |
|---|---|---|
| ዐወቅኹት | ዐወቀው | } ልወቀው። |
| ዐውቄዋለኹ | ዐውቄዋለኹ | |
| ዐወቅዃት | በውቀት | } ልወቃት። |
| ዐውቄያታለኹ | ዐውቃታለኹ | |
| ዐወቅኹኽ፤ ሽ | ዐውቅኽ፤ ሽ | } ልወቅኽ ሽ። |
| ዐውቄኻ(ሻ) ለኹ | ዐውቅኻ(ሻ)ለኹ | |

| | | |
|---|---|---|
| ዐወቅኹኹ ዎ | ዐውቅኹ ዎ | } ልወቅኹ ዎ |
| ዐውቄኊ(ዎት) ለኹ | ዐውቅኊ(ዎት) ለኹ | |
| ዐወቅኊቸው | ዐውቃቸው | } ልወቃቸው። |
| ዐውቄያቸዋለኹ | ዐውቃቸዋለኹ | |
| ዐወቅኊችኹ | ዐውቃችኹ | } ልወቃችኹ። |
| ዐውቄያችኊለኹ | ዐውቃችኊለኹ | |

| አንቱ የተባሉት ቅርቡ ፷ቱን መደቦች ዘርዝረው ሲያውቁ። | | |
|---|---|---|
| ዐወቅኹ (ኊ)ት | ታውቁ(ቋ) ት | } ዕወቋት። |
| ዐወቅኹ (ኊ)ት | ታውቁ(ቋ) ታለኹ | |
| ዐወቅኹኝ | ታውቁኝ | } ዕወቁኝ፣ |
| ዐውቀኹኛል | ታውቁኛለኹ | |
| ዐወቅኊቸው | ታውቋቸው | } ዕወቋቸው። |
| ዐውቀኊቸዋል | ታውቋቸዋለኹ | |
| ዐውቀኹናል | ታውቁናለኹ | } ዕወቁን። |
| ዐውቀኹናል | ታውቁናለኹ | |

| ርስዎና ርሳቸው ብዙዎቹም ወንዶችና ሴቶች ሩቆቹ ፱ኙን ዘርዝረው ሲያውቁ። | | |
|---|---|---|
| ዐወቁ(ቋ)ት | ያውቁ(ቋ)ት | } ይወቁ (ቋ)ት። |
| ዐውቀወ(ዋ) ታል | ያውቁ(ቋ) ታል | |
| ዐወቁኽ፤ ሽ | ያውቁኽ፤ ሽ | } ይወቁኽ ሽ። |
| ዐውቀውኻ(ሻ)ል | ያውቁኻ(ሻ)ል | |

| | | |
|---|---|---|
| ዐወቁኝ | ያውቁኝ | } ይወቁኝ። |
| ዐውቀውኛል | ያውቁኛል | |
| ዐወቁኝ | ያውቁኝ | } ይወቁኹ። |
| ዐውቀውኊል | ያውቁኊል | |
| ዐወቋቸው | ያውቋቸው | } ይወቋቸው። |
| ዐውቀዋቸዋል | ያውቋቸዋል | |
| ዐወቋችኹ | ያውቋችኹ | } ይወቋችኹ። |
| ዐወቀዋችኊል | ያውቋችኊል | |
| ዐወቁን | ያውቁን | } ይወቁን |
| ዐውቀውናል | ያውቁናል | |

| እናንት የተባሉ ቅርቦቹ ፳ቱን መደብ ዘርዝረው ሲያውቁ። | | |
|---|---|---|
| ዐውቃችኹ(ኊ)ት | ታውቁ(ቋ)ት | } ዕወቁ(ቋ)ት። |
| ዐውቃችኹ(ኊ)ታል | ታውቁ(ቋ)ታላችኹ | |
| ዐወቃችኹኝ | ታውቁኝ | } ዕወቁኝ። |
| ዐውቃችኹኝ | ታውቁኛላችኹ | |
| ዐወቃችኊቸው | ታውቋቸው | } ዕወቋቸው። |
| ዐውቃችኊቸዋል | ታውቃቸዋላችኹ | |
| ዐወቃችኹን | ታውቁን | } ዕወቁን ፡ |
| ዐውቃችኹናል | ታውቁናላችኹ | |

| እኛ ባዮች ፲ቱ ፲ቱን መደቦች ዘርዝረው ሲያውቁ። | | |
|---|---|---|
| ዐውቀነው | እናውቀው | } እንወቀው። |
| ዐውቀነዋል | እናውቀዋለን | |
| ዐወቅናት | እናውቃት | } እንወቃት። |
| ዐውቀናታል | እናውቃታለን | |
| ዐወቅንኽ ሽ | እናውቅኽ ሽ | } እንወቅኽ ሽ። |
| ዐውቀንኻ(ሻ)ል | እናውቅኻ(ሻ)ለን | |
| ዐወቅንኹ ዎ | እናውቅኹ ዎ | } እንወቅኹ ዎ። |
| ዐውቀንኧ(ዎታ)ል | እናውቅኧ(ዎታ)ለን | |
| ዐወቅንኹ ዎ | እናውቅኹ ዎ | } እንወቅኹ ዎ። |
| ዐውቀንኧ(ዎታ)ል | እናውቅኧ(ዎታ)ለን | |
| ዐወቅናቸው | እናውቃቸው | } እንወቃቸው። |
| ዐውቀናቸዋል | እናውቃቸዋለን | |
| ዐወቅችኹ | እናውቃችኹ | } እንወቃችኹ። |
| ዐውቀናችኋል | እናውቃችኋለን | |

ከ፳ አዕማድ ፫ቱ ድርቦች ዐዋወቀና ተዋወቀ አስተዋወቀ ማለት ከዚኽ ካወቀ መደብ አይገቡም። የቀሩት አዕማድ ግን፤ አሳወቀና አስታወቀ ፩ወገን፤ ታወቀ ተዋወቀ፤ አስተዋወቅ እነዚኽ ፬ቱ በየፊታቸው ሲረቡ አርእስትና ቦዝ መስምና ቅጽል አላቸው የነገር ኹሉ ስምና ግብር ጥሬና ቅጽል ከማይመስለው አንቀጽ አይወጣም፤ ከሚመስለው እንጂ።

| | (አርእስት) | (ቦዝ አንቀጽ) | (መስምና ቅጽል) |
|---|---|---|---|
| ፩ኛ | ማወቅ | ዐውቆ | ዕዋቂ ያወቀ፤ (የሚያውቅ።) |
| ፪ኛ | ማሳ(ስታ)ወቅ፤ | አሳ(ስታ)ውቆ | አሳ(ስታ) ዋቂ (ያላወቀ የሚያስታውቅ።) |
| ፫ኛ | መታወቅ፤ | ታውቆ | ታዋቂ ዕውቁ፤ (የታወቀ የሚታወቅ።) |
| ፬ኛ | መተዋወቅ፤ | ተዋውቆ | ተዋዋቂ የተዋወቀ፤ የሚተዋወቅ። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፳ኛ | ማስተዋወቅ | አስተዋውቆ | አስተዋዋቂ፤ ያስተዋወቀ ያሚያስተዋውቅ |

ዕውቂያ፤ ዕውቀት ከማወቅና ከመታወቅ ከመተዋወቅ ይወጣሉ፤ ስምነታቸውም የሥራና ያሥራር ስም ነው። ሲዘረዘርም ዕውቂያው ዋ ዕውቀቱ ቷ፤ ዕውቂያክ ሽ ዕውቀትኽ ሽ ዕውቂያዬ ዕውቀቴ እያለ ፱ኙን መደቦች ይጠቅሳል ይኸውም ደቂቅ ርባታ ይባላል። ባዕድ አብዢ ወይም ማብዛ ዎች ነው ዕውቂያዎች ዕውቀቶች ዐዋቆች ዐዋቂዎች። ቶች ቆች ማለት ዎን ውጦና ጕርዶ ነው። ዐዋቂ ያወቀ ከኀላፊ የሚያውቅ በትንቢት ይወጣል የቀርቱንም ያራቱ አዕማድ ቅጽሎች አወጣጣቸው እንደዚኽ ነው ባንዱ የኹሉ ይታወቃል። ቦዝ አንቀጽ ደግሞ አልና ነበር ሲስቡት ወይም ሲዘምቱበት ኀላፊነቱ በ፪ ጽንዕ ይፈታል ጽንዕ ማለትም ጥናት ጥኑነት ጥንካሬ ማለት ነው። ባላፊ ጊዜና ባላፊ አንቀጽ ፫ ዐይነት ክፍል አለ ዐወቀ ያኹን የቅርብ የዛሬ የትላንት ጥቂት የቈየ። ዐውቋል የዋለ ያደረ የሰነበተ የዘገየ። ዐውቆይ ነበር ፈጽሞ ያለፈ የኖረ ወይም ያረጀ የቀረ። የትንቢቱም ጊዜ ክፍሉ እንደ ኀላፊው ነው ይኸውም ይከፍል፤ ይከፍላል፤ ይከፍል ነበር በማለት ባንቀጹ ሦስትነት ይታወቃል። ርባታው አሉታ ሲኾን ግን አል ባሉታ ሞክሼነት ይቀርና፥ ነበር ብቻ ይዘምታል በዘንድም ፈንታ እንዲና ሊ በራብዕነት ይገባሉ። አሉታው ም አል ም ነው አል እስ በቃል ኹሉ ሥር በመነሻ ም በኀላፊና በትንቢት ጫፍ ብቻ መድረሻ እየኾነ ይገባል። (ማስረጃ)

**ኢዐዊቅ (ኢያቀ፥ ኢየዐውቅ፤ ኢይዑቅ)** አለማወቅ።

| (ኀላፊ) | (ትንቢት) | (ዘንድ) | (ትእዛዝ) |
|---|---|---|---|
| አላወቀም (ነበር) | አያውቅም (ነበር) | እንዳ(ላ)ያውቅ | አይወቅ። |
| (ቅጽልና ስም) | | | |
| **አላዋቂ፥ ያላወውቀ የማያውቅ።** | | | |
| (ቦዝ አንቀጽ) | | | |
| **(ኢዐቂቆ፤ ቃ) ሳያውቅ፤ ሳታውቅ።** | | | |
| ግስን ኹሉ እንዲኽ እያልኽ አርባ። | | | |

# ክፍል ፫።

## ምዕራፍ ፮።

ተረትና ምሳሌ ታሪክም ይኸውም በባላገር የሚኖሩ አባትና እናት ሕፃናት አፋቸውን ከፈቱ በኋላ የሚያስተምሯቸው ነው።

(ተረት ተረት፥ የላም በረት)።

### (አ) - እውነት።

እውነትና ዕብለት ውሃና እሳት እነዚኽ አራቱ ዐብረው ዘመቱና ያገኙትን ኹሉ ማርከው ዘርፈው ይዘው ሲመለሱ መቼም አቶ ዕብለት ለተንኰል አያርፍምና ወደ ውሃ ቀርቦ አንተ እሳት ግደለውና (አጥፋውና)፤ ያገኘውን ኹሉ ለሦስት እንካፈላለን ብሎ መከረው። ሞኙ ውሃም ወደ ወሰዱት የሚሄድ ስለ ኾነ ነገሩ እውነት መስሎት እሳትን አንድ ጊዜ ቢረግጠው ሞተ (ጠፋ)። ከዚኽም በኋላ አካሄዱን አይተኽ ጭብጭጦውን ቀማው እንዲሉ ወደውነቱ ቀርቦ፥ እውነት ከብታችንን ይዘን ወደ ዳገት አለው። ውሃም አሻቅቦ መውጣት አይኾንለትምና፤ ራሱን ይዞ እየጮኸ ቈልቈል ሄደ (ወረደ) እውነትና ዕብለትም ከብቱን ኹሉ ነድተው ወዳገር ቤት ከገቡ በኋላ እንደ ገና አቶ ዕብለት እውነትን ከድቶ ኹሉ የኔ ነው አንተ ግን አሽከሬ ነኽ እንጂ ምንም የለኽ አለው። ስለዚኽም ተካሰው በዳኛ ፊት ቆሙ፥ ዳኛውም ሽማግሌ ይያችኹ አላቸው፤ ሽማግሎቹም ነገሩን ከመረመሩ በኋላ ታገሉና እውነት የጣለ እንደ ኾነ ዐብራችኹ ብሉ (ተካፈሉ)፤ ያልጣለ እንደ ኾነ ግን ይቅርበት አሉ። በታገሉም

ጊዜ እውነት ጣለ። ስለዚኽ እውነትና ዕብለት ባንድነት ይኖራሉ ይዘታውም የብለት ይበዛል የውነት ግን እጅግ ትንሽ ነው። እውነትን ተናገሮ እመሸበት ያድሯል። እውነትን ግዛት አትሽጣትም ፤(ምሳ፳፫ ፳፫) (፩ኛ ሥዕል)

አመቴ (የወንዝ አመቴ)። የወንዝ አመቴ በወንዝ የምትውል የጋጋኖ ዐይነት አሞራ ናት። ምግቧም ዓሣና ያይጥ ዓሣ ወይም እንቈራሪት ነው። የምትሠራውም ቤት ካንድ ጒበዝ ሸክም ይበልጣል፤ ስትሠራውም በባላ በልቾ ዛፍ ላይ በስተምዕራብ በኩል አፉን ወደ ምድር ታደርገዋለች፤ ውስጡንም በጭቃ ትመርገዋለች፤ በበት ትለስነዋለች። በክረምትም እንቈራሪት ልትበላ ኩሬ ወዳለበት ሂዳ ትውላለች፤ ያን ጊዜም ጭልፊት እቤቷ ትገባና ማታ በመጣች ጊዜ በውስጥ ኹና እየነከሰች ታባርራታለች። እሷም በዛፉ ላይ ዝናም ሲወርድባት ታድራለች (ከቶም የወንዝ አመቴ)። በማግስቱም እንደ ገና ሌላ ቤት መሥራት ትዠምራለች። እንደ ገዲ በበጋ ምግቧን ሰብስባ በክረምት በቤቷ ብትውል ቤቷን ባልተቀማች ነበር። ለላመትም ዐዲሱን ቤት ትቀማታለች።

## (በ) - ቡዳ፤ ወይም ጠይብ ወይም ባለጅ።

፩ ፈላሻ ወዳገራችን መጥቶ ከንጒሡ ጋራ ባለሚል ኾነ። ምክንያቱም አንጥረኛ ስለ ኾነ ወርቅና ብር እያፈሰሰ ዐልቦና ድኰት፥ አንባርና ቀለበት፥ ድሪና ማርዳ፥ ሙጣና ጣፉ ጫሜ፤ በያይነቱ ጌጥና ሽልማት ዘውድም ከመሥራቱ የተነሣ ነው። ያም ንጒሥ ቀጥቃጮችንና አንጥረኞችን ጠይብ የተባለንም ኹሉ እጅግ ወደዳቸው፥ ካለቃቸውም ጋራ ኹል ጊዜ ቈይታ ያደርግ ነበር፤ ካህናትን ግን ባይኑም ለማየት ጠላ። ካህናቱም በጠይቦቹ እጅግ ቀኑባቸው፤ እነሱንም ለማጥፋት ተማከሩ። ከካህናቱም አንዱ ደብተራ፤ ከሰው ክፉ ደብተራ ካውሬ ክፉ ዳሞትራ እንደሚሉ ወደ ወንዝ ሂዶ ጋኔን ጒተተ። ጋኔኑም ለምን ጠራኸኝ ቢለው እነዚኽን ጠይቦች ከቤተ መንግሥት የሚያሶጣ፥ እኛን የሚያስገባ፥ እነሱን የሚያስጠላ፥ እኛን የሚያሶድድ ብልኀት አድርግልኝ አለው። መቼም ለሰይጣን ተንኰል ቅርቡ ነውና ሂጄ የንጒሡን ልጅ አሳብድታለኹ ምን ኾንሽ ያሏትም እንደ ኾነ የጠይቦቹ አለቃ በላኝ እያለች ትለፈልፋለች። መድኀኒትኽስ ምንድን ነው ቢሏትም ያንተን ስም ጠርታ መድኀኒቴንና ምሴን ደብተራ እከሌ ያውቀዋል ትላለች። አንተንም በዚያ ጊዜ ይጠሩኻል የማንኛውም ዕንጨት ሥር ትቀጠቅጥና ይዘኽ መጥተኽ ታጥናታለኽ ያን ጊዜም እንደ ኻብ አው አሰኝቼ አተላ አስጠጥቼ አለቃታለኹ። ከዚኽም በኋላ ጠይቦቹ ኹሉ ለብቻቸው በዋሻ ይኖራሉ እንጂ እቤተ መንግሥት አይገቡም በከተማም አይቀመጡም (አይኖሩም)። እናንተ ግን ከነገሥታቱ ጋራ ባለሚሎች ትኾናላችኹ ብሎ ነገረው (መከረው) እንደ ነገረውም ኾነ። ከዚያ ወዲኽ ሲሠራ ይኖራል። ባረብኛ ጠይብ ማለት ማለፊያ ደግ ማለት ነው። ቡዳ ግን የዣፖንና የቺንን ሃይማኖት ያወጣ የህንድ ንጒሥ ልጅ ነው። ቡዳ እጅግ ብልኀ ስለ ነበረ ከባለቤት ያወቀ ቡዳ ነው ይባላል። ባማርኛ ጠይብ የተባለው በግእዝ ጠቢብ ይባላል፤ ብልኀ ፈላስፋ ማለት ነው። ይምሰል አይምሰል፥ የጠይብ እጁ ተከሰል። (፪ኛ ሥዕል)

**ቧልተኛ።** አንድ ቧልተኛ ሰው በጉን ሊሸጥ ወደ ገበያ ይዞ ሄደ። በገበያም ተቀምጦ ሳለ በግ ፈላጊ መጣና በዘንጉ የበጉን ዠርባ ነካ አድርጎ ባለበግ ቢለው አይሸጥም ለዘንግ አለ ምን ይላል፤ አንተ ቢል ባ ይላል ምን የሚያራ ነው በጠጥ፤ ረ የት ያደገ ነው እጋጥ፤ እንዲኽ እያለ ቢያላግጥበት ተናደደና ጐራዴውን ውልቅ አደረገ እሱም አየንልኽ ኹለት ጨው ያወጣልኻል አለው ይባላል። (፫ኛ ሥዕል)

**(ገ) - ገበሬ።**

ዐጤ ምኒልክ ከጐንደር ከተመለሱ በኋላ ለጊዜው ወታደር በባላገር ላይ ይመራ ነበርና፥ የጐንደር ወታደር ምሪት የተመራበት አንዱ የሸዋ ገበሬ በገዳው ዳር አንዱ የሸዋ ገበሬ በገዳው ዳር ያጠመደው ወጥመድ ድኵላ ቢይዝለት ወታደሩ የሰማ እንደ ኾነ ይቀማኛል ብሎ ፈራና ሚስቱን፥ እንትን ባልኹበት እንትን ገባበት እንትን አምጪልኝ እንትን እልበት አንቺም ነዪልኝ እንትን ትይልኝ ብሎ ድምጥ ቢያሰማ ወደንጨት የምትሄድ መስላ ገመድ ጠቅላ ቢላዋ ደብቃ ሄደች። ምታም ሥጋውን በርጥብ ሣር ጠቅለው ወደ ጐተራ ቤት አገቡት። እንተ በግእዝ ቋንቋ በቂ ይኾናልና ላኹኑም ዐማርኛ በቂ መኽኮኑ ነው (፬ኛ ሥዕል)

**ጐጕት።** ጐጕት ፊቷ በሩቁ ድመት የሚመስል አሞራ ናት። እሷም ዐይኗ ከፀሓይ ብርሃን ጋራ አይዋሐድምና ቀን በገደል ላይ ቈጭ ብላ ትውላለች። ሌሊትም ወዲያና ወዲኽ ስትል ዐይጥና ድመት ብታገኝ ትበላለች። ዳግመኛም የሌት ወፍ ቀን ብርሃን በሌለበት ቦታ በዋሻ ወይም በጣራ ውስጥ ሳባ በሌለባቸው በኹለቱ ክንፎቿ ቈልቈል ተዘቅዝቃ (ተንጠልጥላ ተሰቅላ) ትውልና ሌሊት ስትበር ታድራለች መብራትም ያየች እንደኾነ ለማጥፋት ትጣጣራለች። ፫ኛም በክንፎቿ ውስጥ ነጸብራቅ (ብልጭልጭታ) ያላት ስሟና መልኳ የማይታወቅ ሌሊት ስትበር ክንፏን ዕጥፍ ዘርጋ ስታደርግ በክንፎቿ ውስጥ ያለው ነጸብራቅ ብልጭ ድርግም ይላልና ባላገሮች የሰይጣን መብራት ነው ይላሉ፥ ከውጪም ሸሽተው ወደ ቤት ይገባሉ። ፬ኛም ስሟና መልኳ የማይታወቅ ሌሊት ስትበር የሚክንፏ ድምጥ እንደ ተተኰሰ ርሳስ የሚሰማ አንዲት አሞራ አለች እነዚኽ ከጨለማ በቀር ላይናቸው ብርሃን የማይስማማቸው ናቸው። እንደዚኽም ኹሉ በሥማቸው ናቸው። እንደዚኽም ኹሉ በሥጋዊና በመንፈሳዊ ነገር ካሰት በቀር እውነት የማይሰማማቸው ሰዎች ቈጥር የላቸውም እነሱም በጨለማ ድርንቈርና ይሄዳሉ (ይኖራሉ)። እነዚኽም ላይናቸው ብርሃን የማይስማማቸው ወፎች ቀን ቀን ባሜሪካ አገር ይደሩ፤ ሌሊት ሌሊት ግን ባገራችን ይዋሉ።

**(ደ) - ደም።**

አንድ ክፉ ሰው ጐራዴዉን ያለልክ ሳለና ስለቱን ለማየት በውሻው ዠርባ ላይ ሳብ ቢያደርገው ውሻው ከኹለት ክፍል ብሎ ሞተ። እሱም ለውሻው ጥቂት ሳያዝን እከደከድዬ ጐራዴዬን የውሻ ደም ነካብኝ ብሎ ጐራዴውን ሊያጥብ ወደ ወንዝ ወረደ፤ በወንዝም ተቀምጦ ሲያጥብ መንገደኞች ወንድማቸውን ሽፍታ ገድሎባቸው ጠፍቶ ነበርና፥ ያንን ሽፍታ ሲፈልጉ ደም የነካው ጐራዴ ሲያጥብ ቢያዩት ይኽ ነው ወንድማችንን የገደለው ብለው ደብድበው ገደሉት። ከዚኽ የተነሣ እግዜር የውሻውን ደም እንኳ አያስቀርም ይባላል ስለዚኽ ላራዊት መራራት ይገባልና። ሰው እንግዳ ቢኾን እግዜር ባላገር ነው። (፭ኛ ሥዕል)

**ድመት።** ድመት ካንበሳና ከነብር የተለየ የቤት አውሬ ነው። ምግቡም ዐይጥ ወይም ሥጋና ወተት ዳቦም ነው። ዐይጥ እየያዘ በልቶ ከጠገበ በኋላ የሚይዘውን ዐይጥ ሲርበው ሊበላ እየገደለ ይጥለዋል። ዳግመኛም እንዳይበላ በመጥገቡ እንዳይተው በመሠሠቱ ዐይጦቹን ላይ ገድል ኹለት ዐይናቸውን አጥፍቶ ወደ ሰማይ እያጓነ ይጫወትባቸዋል። በዱር በበረሓ ከሚኖሩ ከወንበዴና ከቀማኛ ከሽፍታና ከጋዱ ተለይቶ ቤት ሠርቶ የሚኖር ክፉ ባለጠጋ ድመትን ይመስላል። እሱ ያለደንብ የድኾችን ገንዘብ እየቀማ ሣጥኑን ከመላ በኋላ እነሱን ማሰር መግረፍ መቀማት መግረፍ አይተውምና በመጨረሻውም ከግዞቱ እንዳይወጡ ከባርነቱ እንዳያመልጡ ሰው አስቀድሞ ለድንቈርና ካልተሰጠ ለጠላቱ አይገዛምና የልብ ዐይን የተባለ ትምህርትና ዕውቀት ስለሌላቸው እንደ ፈቃዱ ሲያደርጋቸው (ሲጫወትባቸው) ይኖራል። (ምሳ፴ ፲፬)። ያይጥ ሞት፥ የድመት ሰርግ ነው። (፯ኛ ሥዕል)

**ደንቈሮዎች።** አንዲት ደንቈሮ ሴት ፍየሎቿ ቢጠፉባት ልጇን ዐዝላ ልትፈልጋቸው ሄደች። በመንገድም አንድ ደንቈሮ ገበሬ ሲያርስ አግኝታ ብትጠይቀው ምንም ዠሮው ባይሰማ ባለ ፍየል መኾኗን ያውቃልና ፍየሎቿ ያሉበትን በጁ አመለከታት። እሷም ወዳመለከታት ሂዳ ፍየሎቿን አግኝታ ስትመለስ አንዱን ወጠጤ እግሩን ናዳ ስለ ስበረው ብድር የመለሰች መስሏት ይኽን ወጠጤ ዐርደኽ ብላ አለችና ብትሰጠው ያልሰማ ዠሮ ከጎረ ቤት ያጣላል እንደሚሉ ፍየሌን የሰበርኸው አንተ ነኽ ማለቷ መሰለውና ሊመታት ፈለገ በዚኹም ምክንያት ወደ ዳኛ ሂደው ተቋቋሙ። ለዳኛውም እንዲኽ ብሎ አሳየ፤ እግዚሓር ያሳይዎ ክርስቶስ ያመልክትዎ ጌታዬ፤ ይኽች ሴት ፍየልቿ ጠፍተዉባት በሳያት ወጠጤዬን የሰበርኸው አንተ ነኽ ብላ ያዘችኝ። እሷን እግዚሓር ያሳይዎ፥ መልአኩ ያመልክትዎ፤ ይኽ ሰው ፍየሎቼ ያሉበትን ስላመለከተኝ አንድ ናዳ የሰበረው ወጠጤ ወስደኽ ብላ ብዬ ብሰጠው ሊመታኝ ተጋበዘብኝ አለችና አመለከተች። ዳኛውም ደንቈሮ ነበርና፤ ልጅ ማዘሏን አይቶ፥ አያችኹ አያችኹ ይኽ ልጅ ቈጥ እሱኑ ይመስላል በል ቀለቧን ስፈር ብሎ በየነበት ይባላል።

**(ወ) - ውሻ።** ውሻ ከዥብና ከተኵላ ከቀበሮም የተለየ የቤት አውሬ ነው። ምግቡም ሥጋና እንጀራ ነው። ባንድ ቤት ኹለት ውሾች ቢኖሩ አንዱ ሥጋ ያገኘ እንደ ኾነ ላንዱ አይሰጥምና ርስ በርሳቸው ይጣላሉ ይናከሳሉ። ጩኸታቸውንም ሰምቶ ሌላ ውሻ ከውጪ ይመጣል ሥጋዉንም ይወስደዋል። እንደዚኽም ኹሉ ርስ በርሳቸው የሚጣሉ ሰዎች እነሱን ይመስላኡ ነጻነታቸውንም ያሶስዳሉ።

**የውሻ ዕውቀት።** በተጕለት ማገ ዋሻ በሚባል አገር መምሬ ሀብትሽ ይመር የሚባሉ ቄስ ነበሩ። እሳቸውም ከሰው ጋር ተጣልተው ሲነጋገሩ ውሻቸው የባለጋራቸውን ባቱን ነከሰው። በወግዳም በደጃች ጋረደው ቤት የንግዳ ሰው ዕቃና በትር እያሸተተ ባፉ ወደ ውጪ አውጥቶ የሚጥል አንድ ውሻ ነበረ። ባለቤቱን ካልናቁ ውሻዉን አይመቱ። (፰ኛ ሥዕል)።

**(ዘ- ዠ)- ዥብ።** ዥብ በዱር የሚኖር የቀበበሮ የተኵላም ዐይነት አውሬ ነው። ምግቡም ሥጋ ነው። እሱም ጕልበተ ብርቱ ልበ ፈሪ ይባላል። ከጎይሉም ብዛት የተነሣ እማጥ የገባውን አህያ ባለቤቶቹ ማውጣት አቅቷቸው አድፍጠው ሲጠብቁት ከማጡ

ውስጥ በደንደሱ አውጥቶ በወረወረው ጊዜ አስጥለው ወሰዱት ይባላል። ዥብ ሆዳም ነው ማታ ከጕረው በወጣ ጊዜ ብክክዉንም እበቱንም ይበላል ስለዚኽ ዐሩ ነጭ ነው። ያረጀውንና የደከመውንም ዥብ ይጠራል። እንደ ምን ቢሉ ያለመጠን በልቶ ያመጣና ያስታውክለታ ጢት አላደርስ ብሎት (አፋጦት) በዋሻው አጠገብ ያስታወከውን ባገሬ አይቻለኹ። ቡችሎችንም ሲያሳድግ እንደዚኹ ነው። ውሾችም ለቡችሎቻቸው እንደዚኹ ያደርጋሉ (ያስታውካሉ)። እንደ ዥብ ጒልበት ብርቱ ኹኖ ልበ ፈሪ መኾን አይገባም። ዥብ ያህያ ጠላት ነውና አንድ ቀን ማታ አህያዋ እገደል አፋፍ ወልዳ ቢያገኝ ከደስታው ብዛት የተነሣ ጮቤ ሲዘል ገደል ገባ ይባላል። ዥብ አያውቁት አገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ ይላል። እንደዚኽም ኹሉ ክፉ ሰው ክፋቱን በማያቁበት አገር ይከብራል። (፱ኛ ሥዕል)

**ዘንዶ።** ዘንዶ የሰውና የንስሳ ያራዊት የፍጥረም ኹሉ ጠላት ነው። እነዚኽንም ይዞ ለመብላት አስቀድሞ በዛፍ ላይ ተጠምጥሞ ይቈይና በዛፉ ሥር የሚያልፉትን ኹሉ በዥራቱ እየያዘ ይልሳቸውዋል፥ ይውጣቸዋልም። እስም ነገሥታትና ከመኳንንት ተጠግተው ድኾችን የሚበድሉና ገንዘባቸውን የሚቀሙ ክፉዎች ሰዎችን ይመሰላል። ዳግመኛም በተረት ዘንዶ ከባሕር ላይ ተኝቶ ጤዛ ይልሳል ይባላል። ይኽም ተረት ባለጠጋ ምንም ሀብታም ቢኾን የድኾችን ገንዘብ መቀማት አለመተዉን ያስረዳል። ፫ኛም በኦሪት ዘፍጥረት እንደ ተጣፈ እባብን ልቡን አይቶ እግር ነሣው ይባላል። እግዜርም የባለጠጋን ክፋቱን አይቶ የሰበሰበዉን እንዳይበላ ያደርገዋል (መዝ፴፱ ፮። ፵፱ ፲) ዓሣ ጕርጓሪ ዘንዶ ያወጣል የሰው ፈላጊ የራሱን ያጣል። እባብ ግደል ከነበትሩ ገደል። (፲ኛ ሥዕል)

**ዝንጀሮ።** ዝንጀሮ እንደ ጦጣ የሰው ኹናቴ ያለው የዱር አውሬ ነው። በመልክም ኹለት ዐይነት ስለ ኾነ ነጭና ጥቈሬ ይባላል። ጥቈሬው ዝንጀሮ እጅግ ቀናተኛ በመኾኑ እንደ ክፉው ፈርዖን ተባት ሲወለድ ይገድላልና፥ ተባት የወለድች ዝንጀሮ ሙጫሊውን በሆዷ ዐዝላ (ለጥፋ) ነው የምትሄደው ስትሄድም ዳር ዳሩን ነው እንጂ ከጅሩ ወይም ከጨውቴውና ከጭላዳው መኻል ገብታ አትሄድም። ተባት ተባቱም ካደገ በኋላ እየተለየ ሰባት ሰባት ኹኖ ለብቻይ ይጭራል (ይሰማራል)። ስሙም ቦለዴ ይባላል። ከዚኽም በኋላ ስፍራ ሊመቸው የታዘለችውን እንስት ሙጫሊት ከናቷ ዠርባ ነጥቆ (ነጥሎ) ይወስድና እያዘለ አሳድጎ በጊዜዋ ያውቃታል (ይደርስባታል)። ነጥቆ መውሰዱንና ዐዝሎ ማሳደጉን ባገሬ አይቻለኹ። ከነዚያም ከሰባቱ ቦለዶች በየጊዜው ያሸነፈ ይወስዳታል ትንሹ ዝንጀሮ የትልቁን ጫማ ይለካልና። ወይም ኀይል ቢያገን የትልቁን ገመር (ያባቱን) ጅር ይቀማል። ጥቈሬው ዝጀሮ ከፈሪነቱ ብዛት የተነሣ በሰፈረበት ገደል ሥር ኹኖ ነብር ድምጡን ቢያሰማ ካይኑ ጭፋር እንባው እያቀረረ ከገደሉ እየተከባለለ ይወድቃል። ነጨው ዥንጀሮ ግን ነብርን አይፈራም ቀን ለቀንም ቢመጣበት አባሎ እየቈጠረ ይደበድበዋል። ስለዚኽ ነብር ነጭ ዝንጀሮ ቢያይ በደኑ ውስጥ ድምጡን አጥፍቶ ይውላል። የነጬም ዝንጀሮ ስም እንዳሞድ ይባላ። እንዳመድ ያለ ማለት ነው እንዳፍንጫ ዐሚዳው ጥቈሬ ዝንጀሮ ያለ ማለት ይኾናል። ይኽም እንዳሞድ የሰው የሚመስሉ ኹለት ሥራዎች አሉት። ፩ኛው ክረምት ገብቶ ሣር

ባደገ ጊዜ ጨዛ የምትጥስ አንዲት እንዳሞድ ያደርጋል እንጂ እንዳሞዱ ኹሉ ጨዛ እየጣሰ አይሄድም። ያችም ተመላልጣ ስትሞት ሌላዪቱን ይተካል። ስለዚኽ የተመላለጠች እንስተኛ እንዳሞድ ከጅሩ መኻል አትታጣም። ፪ኛም ማሽላ ይቀጥፍ ይቀጥፍና እንዳሞዱ ኹሉ ተሰብስቦ ባንድነት ይቀመጣል አንዲቷም እንዳሞድ በመኻላቸው ተቀምጣ አንዳንድ ራስ ማሽላ እያነሣች ትይዝላቸዋለች እነሱም እየዠነጠፉ (እየዠመገጉ) ይበላሉ። ከጥቈሬው ዝንጀሮ ይልቅ ለነጨው ዕውቀት አለው። ለነብር ጠላታችን እንደ ነጨው እንጂ እንደ ጥቈረው መኾን አይገባም። ነጨው በግና ፍየል እሬትና ቈልቋል ይበላል። ትንሽ ልጅም ቢያገኝ ገፍቶ ገደል ይሰዳል። ጥቈሬው ሙጫሊቷን ነጥቆ እንደ ወሰደ አባት እናቷ ሳይፈቅዱ ልጃገረድን ነጥቆ የወሰደ ሰው ዝንጀሮን ይመስላል። የዝንጀሮ ንጉሥ እስው ይከምር እሱው ያፈርስ። ከዝንጀሮ ቈንጥ ምን ይመራርጧል። (፲፩ ሥዕል)

(ጠ) - ጦጣ። ጦጣ እንደ ጕሬዛ ከዛፍ ወደ ዛፍ የምትዘል እኽልና የዛፍ ፍሬ የምትበላ የሰው ኹናቴ ያላት የዱር አውሬ ናት። ማደሪያዋ በገደልና በዛፍ ላይ ነው። በተረትም ካራዊት ኹሉ ይልቅ ብልጥ ናት ይሏታል፤ ተረቱም ይኽ ነው። ጦጣና ድመት ባንድ ቤት ሲኖሩ ባለቤቶቹ በሌሉበት ጊዜ ጦጣ ድመትን እንቅልፍ እንደ ያዛት አይታ ርጎዉን ጠጣችና የራሷን አበሳ በሰው አብሳ እንደሚሉ፥ የድመቷን አፍ ለይምሰል በርጎ ቀባችው ይባላል። ይኽም ነገር ሰው የሠራዉን ኀጢአት በሰው ለማመካኘቱ ምስሌ ነው። (ዘፍ፫ ፲፪-፲፫)። ጦጣን በብልጠት ተማሪ ብቻ በለጣት ይላሉ። አንድ ቀን ጦጣ ቀለሙን ብታፈርስበት ተማሪ ቢላዋ ሳለ ሳለና በደንደሱ ዐንገቱን ክርክር ክርክር አድርጎ ቢላዋዉን ጥሎት ሄደ እሷም እንደሱ አደርጋለኹ ብላ ዐንገቷን በስለት ዐርዳ ሞተች። ይኽም ተረት ዕወቀት ያላቸው ሰዎች ትምርትና ዕውቀት ለሌላቸው መሣሪያና የተንኰል ምክር እየሰጡ በልማዳቸውና በሃይማኖታቸው በገዛ እጃቸው ርስ በርሳቸው እንዲያጠፏቸው ምሳሌ ነው። ስለ ጦጣ አጥፊነትም ከጦጣ የዋለ ጕሬዛ እኽል በልቶ (ፈጅቶ) ገባ ይባላል። (፩ነገ ፲፫ ፲፱)። ሽማግሌ ኹኖ ሳለ የልጆችን ሥራ የሚሠራዉንም ሰው እከሌ የጦጣ ሽማግሌ ነው ይሉታል። ጦጣ ተይዛ ትዘፍን። ጦጣ ባለቤቷን ታሰጦ። (፲፪ኛ ሥዕል)

**ጠንቋይ።** በወግዳ በራስ ጐበና ከተማ አቅራቢያ አንድ ጠንቋይ (ጠንቅ ዋይ) ነበረ። ሚስቱም በየጊዜው ሰዉን ኹሉ ሲያታልል እያየች እጅግ ዐዘነች። ከዕለታትም አንድ ቀን የባሏ ባልንጀራ ሌላ ጠንቋይ ባሏን ሊጠይቅ ወደ ቤቷ መጣ ብሏ ግን ጋላ ዐማራውን ሊያታልል ወደ ሌላ አገር ሄዶ ነበርና፥ ለጊዜው በቤቱ አልተገኘም። ይኽም ጠንቋይ እኽል ውሃ አቅርባለት ከተጋበዘ በኋላ፥ ዕዲስ ልብስ ስትታጠናቅ ስታጠፋ ቢያያት ምነው እመት እከሊት ወዴት ትሄጃለሽ አላት እሷም ከዱ ዘመቻ ተመልሶ የሞተ አባቷን በሞተ ባ፲፰ ዓመቱ አባትሽ ታሟልና በነፍሱ ድረሺ የሚል ጠሪ መጥቶብኝ ወደ ሳላይሽ መሄዴ ነው አለችው። እሱም እስቲ ቈዩ መጣፍ ልይልሽ አለና መጣፉን ገለጥ አድርጎ አይቶ ረ ጕድ ረ ጕድ አለ እሷም ምን አዩ አለችው ከቤቱ በታች ትልቅ ዛፍ የለሞይ አላት አዎን አለ አለችው እንኪያስ ባውራ ተሲያት ውሃ ሊያጠጣ ከብቶቹን ይዞ ሲውርድ ከዛፉ ሥር ተነሥቶ ነበር ዘንድሮ ግን ሐራ ዘመኑ ሰባት ወጥቶለታልና አይዞሽ አይሞትም። ዕንቺ ግማሹን ከቅቤ ጋራ

ቅቢው ግማሹን ዕጠኚው ብሎ ኹለት የተቈጣጠረ ነገር ሰጣት። ከዚኽም በኋላ ተነሥቶ ወደሚያታልልበት ሄደ። ከሚያታልልበትም አገር ተመልሶ በመጣ ጊዜ በጎረ ቤት ቢጠይቅ ምንም ክፉ ነገር አልሰማንም አሉት እቤቷም ገብቶ አባትሽሳ እንደ ምን ኾነ ብሎ ጠየቃት። እሷም የሚታጠነዉን ዐጠንኹት የሚቀባውንም ቀባኹት (ለቀለቅኹት) ከዚኽ በኋላ በርስዎ ውቃቢ ዳነልኝ (በጎ ኾነልኝ) አለችና ጫማዉን ሳመችዉ። ጥፈትም ጥፎ ሰጥቷት ነበርና ዋጋዉን ኹለት ጨው አምጪ አላት አባቴ እንደ ኾነ ድኗል ጦ ፈት ምን ያደርግለታል ብላ ጥፈቱን መለሰችለት። ያንንም ጥፈት ይዞ ባጣራ ሚካኤል ደብተራ ገብረ ሰንበት የሚባሉ ዐይነ ስዉር ነበሩና ወደሳቸው ቤት ሄደ። ጥፈቱን ልጃቸው ተቀብሎ ሲያነበው ሰመው ረ በሚካኤል፥ ሰውዬው በሞተ ባ፲፰ ዓመቱ (አድጎኖ ለገብርከ ወልደ ጻድቅ) እያልኽ ትጥፋለኽን ያች ሴት አላግጣብኻለች እያሉ ላቁበት። እሱም ዐፍሮ ወዳገሩ ወደ ጐሽውሃ ተሻገረ። የጠንቋይም ዋና ሥራ ከታላቅ ማዕረግ ትደርሳለኽ ሹመት ሽልማት ታገኛለኽ ራስ ደጃዝማች ትባለለኽ እያለ ሰውን ኹሉ ሲያስገብርና ሲያከስር መኖር ነው። ሹመት ፈላጊም እሾማለኹ እያለ ስለ ጠንቋይ ሲገብር ይሞታል ከነፍሱም ከገንዘቡም ሳይኾን ይቀራል። (ጠንቋይ ለራሱ አያውቅም)።

**(የ) - *ያሬድ*።** ቅዱስ ያሬድ ዜማን የደረሰ ያገራችን ሊቅ ነው። በትውልድም ጌዴዎን ለሚባል ያኵስም ገበዝ የቱ ልጅ ነው ይባላል። እሱም እተማሪ ቤት ገብቶ ትምርት ሳይገባው ሰባት ዓመት ኖረ በሰባተኛውም ዓመት ከተማሪ ቤት ኰበለለና ጠፍቶ ሄደ በዋሻም ተቀመጠ። በዋሻውም አጠገብ ዛፍ ነበርና በዛፉ ሥር ቈጭ ብሎ ሳለ አንድ ትል ከዛፉ ላይ ወጣና እወገቡ ሲደርስ ወደቀ ዳግመኛም ወጣ ወደቀ እንዲኽ እያደረገ ስድስት ጊዜ ወድቆ በሰባተኛው ወጣና የዛፉን ፍሬ በላ። ቅዱስ ያሬድም ይኽን የትሉን ትጋት ባየ ጊዜ ወደ ተማሪ ቤቱ ተመልሶ መምሩን አጥፍቻለኹና ማረኝ አለው። ከዚኽም በኋላ መንፈስ ቅዱስ ገልጦለት ዜማን ደረሰ። ከዕለታትም አንድ ቀን ከቤተ ክሲያን ገብቶ ሲያዜም ዜማዉን ለመስማት ዐጤ ገብረ መስቀል በወገቡ ቆመ። ንጉሡም ሳያይ በሰንደቁ ዐንካሴ የቅዱስ ያሬድን ጫማ ወግቶት ኑሮ ሰንደቁን ቢነቅለው ደሙ ፈን አለ ንጉሡም ደነገጠ ለቅዱስ ያሬድ ግን ከዜማው ጣዕም የተነሣ ምንም አልተሰማውም። ጥቂትም እንኳ እንዳልተነካ ዜማዉን ያዜም ነበር እንጂ። ንጉሡም ያልኸውን እሰጥኻለኹና ንገረኝ የምፈልገው ነገር የለኝም ሂጄ ካን ተራራ (ቧሒት) ዘንድ እንድትመጥ ፍቀድልኝ አለው፥ ፈቀደለት በዚያውም ተራራ ዘንድ ተቀምጦ ሲያዜም ኖረና ዐረፈ (ሞተ ተለየ)። ተማሮች (ሕፃናት) ሆይ ትምርት ሳይገባን ብዙ ጊዜ ቈየን ብላችኹ አትዘኑ ተግታችኹ ሳትሰለቹ ተማሩ እንጂ። ፊደል ካልቈጠረ ባላገር በተማሪ ቤት የኖረና የተጐላላ እንዲሻል ዕወቁ አንድ ነገር ሳያውቅ አይቀርምና። (፲፫ኛ ሥዕል)

**(ከ) - *ክህነት*።** ከግራኝ ወዲኽ መንግሥት ወደ ጐንደር ስለ ሄደ ጳጳሱና መምራኑም የሚገኙት በጐንደር ከመኾኑ የተነሣ የክርስቲያን ትምርት ዛሬ የጋላ ቤት በሚባለው አገር ኹሉ ፈጽሞ ጠፋ። በጉራጌም አገር እያነሰና እየተቀነሰ ሄደ። ነገር ግን ጉራጌን ጋላ በዙሪያው ተሠርቶ ወደ ዜጋመልና ወዳንከበር ወደ ጐዣምና ወደ ጐንደር ወደ ሌላም ስፍራ ለትምርት እንዳይሄድ ምንም ቢከለክለውና

ቢያውከው እስካሰን እንጃቦ ድረስ ስመ ክርስትናዉንና ሀብተ ወልድናዉን አላጠፋም ነበር፤ ያላጠፋበትም ምክንያት ይኸ ነው። ከቤተ ክህነት ወገን የሚወለደው በኵር ኹሉ በሕግ ወይም በድንግልና እየኖረ ቄስ እከሌ ይባላል፥ ከማይረባ ነገር ኹሉ ይርቃል፤ ሕፃናትን ያጠምቃል። በዋሻ ውስጥ የተደበቀውንም ታቦት ያጥናል፤ ይቀድሳል ያቈርባል፤ ቀድሶም ስለ ቍርባን ክብር ታዝሎ ወይም በፈረስ ተቀምጦ ወደ ቤቱ ይገባል (ይመለሳል)። ሕዝቡም ኹሉ ቅዳሜ ማታ ተሰብስበው በቤተ ክሲያን ዐድረው እሑድ ቅዳሴ ውጪ ወደ የቤታቸው ይሄዳሉ። መገበሪያ የሚኾነውንም ስንዴ የሚዘራውና የሚያርመው የሚያጭደውና የሚወቃው ባለ ሕግ ነው፤ ከብትም እንዳይሸንበት በበትር ይወቃል። ስለዚኽ በጕራጌ መሢዕት በሺዋ ሳታት፥ በጐንደር ማሕሌት በጐዣም ጸሎት ይባላል። ያም ቄስ መሞታቸው በደረሰ ጊዜ ርጥብ ስልቻ ይነፋና አስሮ ያኖራል። እሱም ከሞተ በኋላ ሕዝቡ ተሰብስበው ወራሹን አቅርበው እግዜር የቄስ እከሌን ክህነት ያሳድርብኽ ይሉና ስልቻዉን ፈተው ትንፋሹን በራሱ ላይ ያፈሱበታል እሱም ቄስ ይኾናል። የሚያስተምር ጳጳስ ካለበት ስፍራ ይልቅ የጕራጌ ቤተ ክህነት እጅግ የተቀደሰ ነው። ቀድሞ ዘመንም በተጕለትና በወግዳ ቈላ ሚስቱ የሞተችበት ቄስ ባሏ የሞተባትን የቄስ ሚስት አግብቶ እንደ ገና ሲቀድስ ይኖር ነበር ይባላል። ይኸም የተደረገው በፍትሐ ነገሥት እንደ ተወሰነ ያ ቋንቋዉን የማያውቁትና ቋንቋቸውን የማያውቅ የግብጥ ጳጳስ ተገዝቶ በማይመጣበት ጊዜ ነው። ይኸነንም ጋብቻ የቆብ ተዝካር የለመዱ ሰዎች ይነቅፉት ይኾናል። ትልቁ ቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በጕራጌ አገር እንዳስተማሩ ገድላቸው ይመሰክራልና ይኸች እውነተኛዋ የጕራጌ አምልኮ የሳቸው ሳትኾን አትቀርም። ዐሰን እንጃቦ ያላሰማቸው አክሊልና ምሁር ናቸው። ጕራጌ ሲተርት አይትማሰል አይትጋባ ይላል።

ጳጳሱ የግብጥ ስለ ኾነ አገራችንን ቈጥር የሌለው ጕዳት አግኝቷል፤ ከጕዳቱም አንዱ ይኸ ነው። በሣህለ ሥላሴ ጊዜ ከወገዳ ፲፰ ሰዊች ጐንደር ሂደው ቅስና ተቀብለው ሲመለሱ ሽፍቶች ፈንግለው ሸጧቸው ካ፲፰ቱም ፫ቱ ፪ጊዜ ተሸጠው በ፫ኛው ያንኮበር ነጋዴ ቢገዛቸው አምልጠው አገራቸው በገቡ ጊዜ ከ፫ቱ ፩ኛው የኔ ዘር ተምሮ ቄስ የኾነ ርጉም ይኹን ብለው ስለ ረገሙ ጐሽውሃ በሚባል አገር ልጆቻቸው ፊደል ሳይቈጥሩ ይኖራሉ። ርስታቸውንም ከሌላ መቅደስ መጥቶ ሴቶች ልጆቻቸውን ያገባ ዐማች ሲበላው ይኖራል። (፲፬ኛ ሥዕል)

ማስረጃ ስሯጽ ግጥምና ታሪክ፤ በግብጦች ፈንታ ሠለስቱ ምእትን ስለሚነቅፉና ስለሚያሙ ስለ ፍትሐ ነገሥት አንባቦችና ትርጓሞች ስለ ሰሚዎችም። (ከኪዳነ ወልድ ክፍሌ)። **ስምዐኒ አንባቢ ወእንግርከ፥ ሰማዓኒ አስምዕ ለከ።**

ደስታ ተክለ ወልድ በሠራው ገበታ
ያቀረብኹትን ቃል ባርኮላችኹ ጌታ፤
ነገር ባቡን ወጥ እንዲበላላችኹ።
ጃንሆይ ይቁሙና ያሳልፉላችኹ።

ከታሪኩ በፊት ግጥሙን ስትቀምሱ፤
ወጡ ሰንፍጧችኹ እንዳታነጥሱ፤
በታሪኩም አለ ብዙ ሰናፍጭ፤
ዐይን የሚያስለቅስ እንብ የሚያመነጭ።

ሰፌድና ወንፊት እያለ በጃችን፤
ያልተነፋ ዶቄት ምነው ማቡቃታችን፤
እስከ መቼ ድረስ እንጠጣለን ጐሽ፤
አናጠራውሞይ በትርጓሜ ሻሽ።
ኮሶው ንባብ ብቻ ስላላሻረኝ፤
ቀጨሞ ጨምሬ ልደቈሰው ነኝ።
እንደ አሮን ልጆች የኦሪትን ጣቃ።
ለብሶ ተጐናጥፎ የወንጌሉ አለቃ፤
ፍትሐ ነገሥት አውጭው አባ ገብርኤል፤
ግብጦችን ሊያነሣ እናንተን ሊጥል፤
በሰማኒያ ሺሕ ብር አራት ጳጳስ፤
ገዝተው እንዳስመጡ ዐፄ ዮሐንስ፤
ጳጳስና ክህነት በጦቢያው መንግሥት፤
የንግድ ዕቃ ኹኖ እንዲሸጥለት፤
ራሱን በሌዊ እኛን በይሁዳ፤
መስሎ አነጻጽሮ ሱቁን ሲያሰናዳ፤
ባ፫ኛው አንቀጽ ቀለም ቀንዱን ተክሎ፤
ኢይሠየሙ ሲል ኢያጽጽስ ብሎ፤
ፈራሽ ሰው ሠራሽ ሕግ ስለ ጣፈባችኹ፤
ሠለስቱ ምእትን ለምን ታማላችኹ።
ካገር ልጆች በቀር ይኸነን ልቅና፤
ባዕድ የውጪ አገር ሰው ይሾም መች አሉና፤
ኢትዮጵያንስ ለይተው ከስልቅ፤
መቼ ተረዱና አሉታና ጽድቅ፤
በስልቅ ዐይነ ገመድ ቢሰፈር ቢለካ፤
ሦስት እጅ አይበልጥሞይ የናንተ ሰበካ።
ግብጥ ያፈለቀውን አሉታ ጠበል፤
ከሥሩ ከምንጩ ቅዱት በመንቀል።
ያባ ገብርኤል ፍርድ ዕጥፍ ድርብ ግፍ፤
ባ፩ ዐንገት ላይ ዕንቅርት ከዦሮ ደግፍ፤

ወይም ትንቦኾ ጠጭ ዛር ባለውዥሞ፤
ኢያጽጽስ የሚል መጠጫውን ሹሞ፤
የዛርም ትርጓሜ በዔቦር ልሳን፤
ፍሉጥ ብውድ ነኪር እምቤተ ክርስቲያን።
የኒቅያን ግዝት እንዳባይ ጠጥቶ፤
በጦቢያው ላይ ሲዋሽ አያፍርሞይ ከቶ፤
ይሰበር ይሰበር ወዲያ ይሰበር፤
ይኸ ከጦቢያው ዐንገት የጫነው ቀንበር።
የዘራውም ክርዳድ ገረማና ጌንጭ፤
ከስንዴው መካከል ይታረም ይነጭ።
ዐንገት መፈጠሩ ዙሮ ለማየት፤
ራስንም ችሎ ጐዦ ለመውጣት፤
ራሱን የማይችል ዐንገት እያለው፤
ምን ሰው ነው ምን ሰው ነው ረ ምን ሰው ነው፤
ራስ አለመቻል ባሕርዊ ሕግ፤
ለድዉይ ለሕፃን እስኪድን እስኪያድግ።

<><><><>

ሠለስቱ ምእትስ በኒቅያ ሸንጎ፤
የፈረዱልን ፍርድ ጤፍ እንጀራና ርጎ፤
በወንጌላውያን ባራቱ እንስሶች፤
በኪሩቤል አምሳል በግዜር ፈረሶች፤
ሊቃነ ጳጳሳት የወንጌል አፍላግ፤
ካራት እንዳይወጡ ስላቆሙት ሕግ፤
ምንም ለብቻችን እንዳንሾም በትረክ፤
ኢይሢሙ ብለው ቢጥፉብን ልክ፤
ለስልቅና ለኛ ለይተው ለፍርድ፤
አቁመውልናል ኹለት አዕማድ፤
እንደ ያቄምና እንደ በለዝ ያሉ፤
በወርድ በቁመት የተተካከሉ።
ፍርዳቸውም ይኸ ነው ለግብጥ የሚገባ፤

ሊቀ ጳጳስ መሾም ከኛው አንዱን አባ፤
የአንጾኪያው ሊቅ ከስልቅ አንዱን ሰው፤
ሊቀ ጳጳስ ብሎ እንደሚሾመው።
ከኛም አንዱን መሾም ባ፩ኛው ሰላማ፤
ዠምሮት ነበረ አትናቴዎስማ፤
አላገኘም እንጂ መሳይ ተከታይ፤
ዘምዶቹ ታስረው በፍቅረ ንዋይ።
እንዳትንፈራገጥ ላሚቱ አገራችን፤
ወድሮ ያልባት ዘንድ በጐፍላ ስማችን፤
ጳጳስ እሰጥ ብሎ ግብጽ ካሎደረ፤
ማነው እግር ተወርች ወንጌሉን ያሰረ።
ወንጌል ባገር ቋንቋ እንድትሰበክ፤
አገርም ባገር ልጅ እንድትባረክ፤
ከሧሚነት በቀር ተሹሞ መምጣት፤
ለግብጽ አልተሰጠም ከሠለስቱ ምእት።
የግብጽ ሰው ብቻ በዚያም በዚኽም፤
በኹለት አህጉር አለቃ አይኾንም፤
እንደ ስልቁ ጳጳስ ለኢትዮጲያውም፤
ሥልጣን አለውና ጳጳሳት ሊሾም።
ጳጳሳት የማይሾም ለየወረዳው፤
ሊቀ ጳጳስ ይባል አላሉም አበው።
ከስልቁ አሳንሰው የኢትዮጵያን፤
ስም ብቻ አልሰጡትም እንበለ ሥልጣን።
በስም ብቻ መክብር ሥራውን ሳይሠሩ፤
የግብጦች ዱለት ነው መቼ የማኅበሩ፤
በሀገራችንም ነብሪድና ዕጨጌ፤
የጳጳሳት ስም ነው መቼ የባለጌ፤
ከነጭ አባይ ወዲኽ ከማየ ግዮን፤
ከበለው ከስናር እስከ ውጋዴን፤
እስከ ወዲያ ማዶም እስካረብ የመን፤
እስከ ጀበል ሐበሽ እስከ ናግራን፤
እንድትዘረጋ ቤተ ክርስቲያን፤
ያስፈልጋልና መቶ ታምሳ አቡን።

<><><><>

ነጻነት ከሌላት ክህነት በሀገሯ፤
ፍጹም አይባልም የመንግሥት ክብሯ፤
በባዕድ ጳጳስ እጅ ተቀብቶ መሾም፤
ያሳዝናል እንጂ ደስ አያሰኝም፤
ደስታም ቢኖረው ድርሻው ከ፻ አንድ፤
ዘጠና ዘጠኙ ሂዶ ወደ ባዕድ።
ባዕድ ሐዋርያም ደስ ማሰኘቱ፤
አስተምሮ እስኪሾም በጥንተ ስብከቱ።
ለይቶ አለማወቅ ክብርና ኀሳር፤
ሲያስገዛን ይኖራ ጳጳስ እንደ ገብር።
ኢታምልኩ ባዕደ የተባለው ቃል፤
ስለ ጳጳሳትም ይተረጐማል፤
ርሱ ባለቤቱ በዳዊት በገና፤
አማልክት አንትሙ ብሏቸዋልና።
ከእስራኤል በቀር አሕዛብ እንኳ እብዱ፤
አያመልክም ነበር ያንዱን ጣዖት አንዱ።
ንጉሥ ሳይኖራቸው ሶርያና አርመን፤
መርጠው ይሾማሉ በትረክና አቡን፤
ከወገኑ መርጦ ጳጳስ የማይሾም
ከጦቢያችን በቀር ሌላ ሕዝብ የለም።

<><><><>

ግብጽ እንደ እስራኤል ሳይከተለን፤
የወሰድነውን ልብስ ከርሱ ተወስን፤
ለብሰንማ ቢኾን ዐጥፈን ደርበን፤
ስንኳን ካባይ ወዲኽ ግዛታችነን፤
እንደ ስልቅ ሰዎች ጳጳስ እየሾምን፤

እንሰብካት ነበረ ደቡብ አፍሪቃን።
ያባቶቻችነን ፈረስና ጓዝ፤
ባሕርም አላገደው እንኳን ፈሳሽ ወንዝ፤
ባለታሪኮችም ይመሰክራሉ፤
ያማራ ቄንጮች ሞዛምቢክ እንዳሉ።
በሰሜን አፍሪቃም ያቬ ዳዊት ጫማ፤
ሱዳንና ኖባን ሲረግጥ እንዳውድማ፤
የግብጽን ጕረሮ አባይን መዝጋት፤
በጣታቸው ነበር እንደ ቀለበት።
ዛሬም እንደ ዳዊት በጥንቱ ስለባ፤
ያፍሪቃን አህጉር ስናጭ ስናሰባ፤
አይበቃም ተብሎ አንድ ጃን ደረባ፤
በኀይለ ሥላሴ በቀዳማዊው፤
ቀዳማዊ ኹና የተዠመረው፤
መፈጸሙ አይቀርም ኋላ በጊዜው።
ዐምስቱን ጳጳሳት ሰዎች ኹሉ እንደኔ፤
መስለዋቸዋል በዋዜማ ቅኔ፤
ለሥነ በዓሉ ምንም ቢቸኰል፤
ዋዜማ ሳይቆም አይከብርም በዓል።
ነገር ሲበዛበት ልብ እንዳይዘነጋ፤
አራተኛው አንቀጽ በዚኩ ይዘጋ፤
አባ ገብርኤልም በያዘው ዐለንጋ፤
መገረፉ አይቀርም ጨርሶ ሲነጋ።
ባወጡት ዳኛና በያዙት በትር፤
መረታት መመታት እንዴት ያሳፍር።
ያባቶቹ መዝገብ ቋንቋና ትምርት፤
ዕልም ድርግም ብሎ እስኪጠፉበት፤
ሺሕ ሰባት መቶ ዓመት በንግድ ሲኖር፤
ያተረፈው የለም ከማጕደል በቀር።
በጠየቀው ጊዜ አቁሞ ከፊቱ፤
ምን ይመስል ይኾን ለባለመክሊቱ።
ሶርያማ ባይኖር ጵጵስና ሰጭ፤
ጭራሽ ደርቆ ነበር የክህነቱ ምንጭ፤
ከዚያው ከምንገዛው ካንዱ ጳጳስ ጕንጭ፤
ዳግመኛ እየገዛን እንዳንጐነጭ።
ዛሬም በየፊናው ተበታትኖ ሕዝቡ፤
፫፻ ሺሕ ነው ያለው በመዝገቡ፤
ለ፫፻ው ሺሕ ባሥራ ስምንት ክፍል፤
ዐሥራ ስምንት ጳጳስ ይሾምለታል።
ቆቅ ማለደ ጮኾ ወደ ርሱ አጠገብ፤
ያሎለዳቸውን እንዲሰበስብ፤
እኛንም ሰብስቦ መዝኖን ቢኾን
እናነሣ ነበር ሠወስት መቶ አቡን።

<><><><>

በግብጦች ሰንሰለት በወፍራም ስሉታ፤
የታሰረው ንባብ በጽድቅ እስኪፈታ፤
ከናባ ገብርኤል እየተሟገተ፤
በፍትሐ ነገሥት ውስጥ ዐይኑን ለከፈተ፤
የግዝት ማየ አይኅ የርግማን በረዶ
እንሆ ይታያል በግብጽ ላይ ወርዶ።

ወፈታሒሰ ውእቱ ሊቀ ካህናት፤ ወውእቱ ሊቀ ጳጳሳት፥ አው ኤጲስቆጶስ። ይኩን ድጉኑ ምስማዕ ወንጻሬ፤ ከመ ይፍልጥ ቃል ጽድቅ ወቃለ ሐሰት። ወይኩን ድጉኑ ልሳን ወዘየአምር ነገረ ልሳን እንተ ኢትትከሀል፥ ልሳነ ሰብእ ሢመቱ በዘይትናገሩ በበይናቲሆሙ (ፍ ነ ፺፫)። ወለኵሉ ዘዐለወ ዘንተ ሕገ ሲኖዶስ ያወግዞ። አሌ ሎቱ ለዘየዐሉ ዘንተ ሕገ፤

ወሲኖዶስ ያወግዞ (ፍ ነ ፬ ዘኒቅያ ፴፱ ና ፸፯)። ለዚኽ ቃል ማገዣ (ገላ፩ ፰ ፱። ፩ጢሞ ፯ ፯-፲፩። ሕዝ፳፱ ፯ ፯ ፲፫። ማቴ፯ ፲፫ ፲፯። ፲፫ ፯ ፰ ፱ ፲፬። ፲፰ ፯)።

(ታሪክ ቋንቋ ስለማወቅ)

በጐንደሮች መንግሥት ከላስታ ብዙ ዛቋኖች ጐንደር ወርደው በንባብ ከተፈተኑ በኋላ አምጃሩ ቅስና የሚሾሙትን ፪፪ ብር ጕቦ አምጡ ሰላስ ኹሉ እንዳቅማቸው ሲሰጡ አንዱ ብቻ ስለ ድኽነቱ የለኝም ቢል ለይቶ አስቀረው። ወንድሞቹ ቀስው ሲወጡ በደጅ ቈይቶ ፪ጣቶቹን በላ አስመስሎ ቀሰረና አባታችን እግዜር አምጃርዎ ለኔ ፪ ብር ካልሰጠኽ አትቀስም ብሎ ከለከለኝ፤ እንኳን ፪ ብር ፩ ብር የለኝም ፍጹም ድኻ ነኝ ሲል ሌባ ጣቱን ደግሞ ቀስሮ አሳየ። አቡኑ ምን ይላል ብሎ አምጃሩን ቢጠይቅ ሚስቶቹ ፪ ናቸው፥ ባንዲት ሴት መወሰን አልቻልምና በኹለቱም ቅስና ይስጡኝ ይላል አለው። ጳጳሱም ደንግጦ ፊቱን ይላል አለው። ጳጳሱም ደንግጦ ፊቱን አማተበና የማሪያም ጠላት እንደ ማለት ይኽን ያልመታ ብሎ ቁሞ አስደበደበው፤ ወዲያው ደግሞ በዚኽ ከተማ ያደርኽ እንደ ኾነ ውዮልኽ ተብሎ ከወድሞቹ ተነጥሎ ደሙንና እንባዉን እያዘራ ወዳገሩ ተመልሶ ሄደ ይባላል። ይኽም ታሪክ በውጪ አገር ቋንቋ ተጥፏል ሌላም ይኽን የመሰለ ዐብሮት የተጣፈ ብዙ ያቡኖችና የምንጃሮች ግፍ አለ። በመጨረሻውም ጸሐፊው የዚኽን ታሪክ ማሰሮ፥ ኢትዮጵያ በውስጧ በጋጧ ከሚወለደው ፈረስ በቅሎ ያውም ከጮሌውና ከሠጋሩ ከድንጕላው ይልቅ ሌላ ልዩ ዐይነት የውጪ አገር ኩበት ትወዳለች ብሎ በተረት መግላሊት ከድኖታል። ዛሬ ግን ባዲሱ ሥልጣኔ ቀፎነት በወጣቶቿ ንብነት ባውራዋ በኀይለ ሥላሴ መሪነት በግዜር አናባቢነት ያገር ልጅ የማር እጅ መኾኑን ዐውቃ መላስና መቅመስ ዠምራለች። ከሩቅ ዘመድም ዐብሮ የሚሞት የቅርብ ጎረ ቤት መብለጡንና መሻሉን አለጥርጥር ዐውቃለች።

ዓዲ ናተሉ ወንዌስክ ጽሒፈ ካልእ ታሪክ ዘርቱዐ ይሰብክ በእንተ ብዝኀ ዕበያ ወፍድፋዴ ክብራ ለኢትዮጵያ እሞን ወእምሔውቶን ለአህጉረ ገነት አፍራቅያ። ገነትሰ ምድረ ኵሽ አው ኢትዮጵያ ነቅዐ ማየ ግዮን ወኤፌሶን ዘይሰቅያ ትሰመይ ሰማየ እምትካት በልዕልናሃ እምአድባራት፤ ወበአጽብሖተ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር ፈጣሪሃ በከመ፤ ጽሑፍ። በፍልስጥዔም ያሉ የምሥራቆችን አብያተ ክርስቲያናት ርስት ከሚናገር ከሎንሶ ቢዮ ታሪክ በዐረብ ቋንቋ ጥፎና አሳትሞ ካኖረው ከኹለተኛው መጽሐፍ ወዳማርኛ የተቀዳ ፯ኛ ክፍል። ከጥንት ዠምሮ በቅድስት አገር በኢየሩሳሌም የነበረ የኢትዮጵያን ርስትና ቦታ ይናገራል ሎንሶ ቢዮም ፯ ቋንቋ የሚያውቅ የኢየሩሳሌም ባላባት ነው። ተርጓሚቹም ኹለት ናቸው መጣፉን ከኢየሩሳሌም ያመጣው ኪዳነ ወልድና ዐረቢ ወልደ ሥላሴ በሐረር ከተማ ፲፱፻፲፫ ዓመተ ምሕረት።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘወትር በኢየሩሳሌም ከሚኖሩ ክርስቲያኖች ጭምር ናቸው፤ በኹለተኛው ክፍል እንደ ተነገረ።

ቀድሞ ዘመን በቅድስት አገር ለሚኖሩ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከሌሎች ሕዝበ ክርስቲያን ይልቅ እጅግ ታላቅ ክብር ነበራቸው። ይኸውም ስለ ፫ ነገር ነው ፩ኛ፥ ቅድስቲቱ ቦታ በጃቸው ስለ ኾነች ፪ኛ፥ በያመት ባሉ ከሌላው ሕዝብ እነሱ የሚቀድሙባትና የሚሠለጥኑበት ሥራ ስለ ነበራቸው። ፫ኛ፥ በዚኹ በሚመጣው ክፍል እንደሚታይ መጠን ንጉሣቸው ለፈረንሲስካን መነኰሳት የዋለውና ያደረገው ብዙ ርዳታ ስለ ነበረው ነው። ከቀደሙ ትውልድ ቅድስቲቱን አገር ለመሳም የመጡ ሰዎች ኹሉ በጐዳናቸው ታሪክ ላይ ኢትዮጵያውያን ኢየሩሳሌም መኖራቸውን አብዝተው ይናገራሉ። ባ፲፫፻፴፪ ዓመት ፍልስጥዔምን ዙሮ ያየ አቡነ ባሩካር ዶመኒካኒው በኢየሩሳሌም ከሚኖሩ ሕዝብ ጋራ አንድነት ያላቸው ኢትዮጵያውያን ናቸው ብሎ ተናግሯል።

ዳግመኛም ባ፲፬፻፴፪ ዓመት ወደ ኢየሩሳሌም የመጣ በሪትራንዱን ዱላብሩኪይር በጎልጎታ ቤተ ክርስቲያን ካሉት ክርስቲያኖች ጋራ ዘወትር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ናቸው እሊኹም ከዮሐንስ ቀሲስ አገር የመጡ ብሎ ይናገራል። (ይኸውም ደብረ ሊባኖስ ይመስላል)። ከጃዋ (ሙሴ) ዱበሪፍም የፈረንሳዊ መልክተኛ በስንጥቡል ከተማ ነገር ጨራሽ የነበረው በሥራው መካከል ለመፈረጅ ወደ ምሥራቅ በመጣ ጊዜ፤ የአብርሃም መሠዊያና የመልከ ጼዴቅ መሧዕት ማቅረቢያ የነበረውን ዛሬ በሮሞች (ግሪኮች) እጅ ያለውን የኹለቱን ቤተ ክርስቲያን ቦታ ሲተረጕም እንዲኽ ይላል። ከዚያም ከወጣነ በኋላ ጨለማ ባለበት በብዙ ምድር ቤት ውስጥ ለውስጥ ዐልፈን በአብርሃም ስም ወደ ታወቀች ቤተ ክርስቲያን ወጣን። ይችውም የተሠራችው አብርሃም ልጁን ሊሠዋ ባሰበበት ቦታ ላይ ነው። መሬቱም ባማረ በተሸለመ በታናናሽ እብነ በረሽ የተጸፈጸፈ ነው በዚያም ላይ የቱርክ ምንጣፍ ተነጥፎበታል። መሬቱን የሚሳለም ሰው በመጣ ጊዜ ምንጣፉን ያነሡለታል። ከዚኽችም ቤተ ክርቲያን በስተኋላ ያለው ኢየሱስ ሕማም ሞት የተቀበለበት ደብረ ቀራንዮ ነው በመካከላቸው ከናስ ግንብ በቀር ሌላ የለም። ከዚያም የመልከ ጼዴቅ መሧዕት ቦታ ወደምትባ ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ያገባል ያችም ቤተ ክርስቲያን እጅግ የተጌጠች ናት በርሷም የሚያገለግሉ ኢትዮጵያውያን ናቸው። ከኹለቱ ቤተ ክርስቲያን ባንዲቱ ከነሱ ወገን የሚኾኑ ጥቋቄሮች መነኰሳይያት ነበሩበት ይላል። ዳግመኛም ይኸው ኸዋጃ ዱበሪፍ ጎልጎታን ስንሳለም የታነጠ የንጨት ደጃፍ ወዳላት ኢትዮጵያውያን ወደሚያገለግሏት ቤተ ክርስቲያን ገባን የመንበሩ ዐምድ በቈርበት የተለበጠ ነው ብሎ እስከዚኽ ተናግሯል። ፈረንሱአርኑድም የኸዋጃ ዱበሪፍ የመርከቡ አለቃ ባ፲፮፻፪ ዓመት ወደ ምሥራቅ የሄደበትን ታሪክ ሲጥፍ አብርሃም ልጁ ይስሐቅን ለመሠዋት ባሰበበት ቦታ ላይ ያማረች ቤተ ክርስቲያን ትገኛለች ይላል።

እንደዚኽም ኹሉ ባ፲፮፻፳፪ ዓመት ወደ ኢየሩሳሌም የመጣው ከቡሻዊው አቡነ በሲፈክዱብሩፈንስ የኢትዮጵያ ሰዎች በጎልጎታ መኖራቸውን ይናገራል። እነሱም በዚኹ ቦታ ላይ መስቀል በተተከለበት በቀራንዮ ቀስተ ደመና ሠርተዋል። በቀስተ ደመናውም ላይ ቤተ ክርቲያን አለች በኢትዮጵያ ጳጳስ እጅ ይላል። « ሶርያ ከግብጥ ተጣልቶ ቶማስ የሚባል ኢትዮጵያዊ ለሐበሻ ገዳም ኤጲስ ቆጶስ ሹሞ ነበርና ጳጳስ ያለው ርሱ ይመስላል»። ደግሞም ኸዋጃ ዱሪሻክ ባወጣው መጽሐፍ የሹማቸውን ታሪክ በተናገረበት በዛካሪስቲ ይታወቃል። ያም የኢትዮጵያ መኰንን መካናት ቅዱሳን ለመሳም ወደ ኢየሩሳሌም በመጣ ጊዜ ከኢትዮጵያ ገዳም ሰፈር። ዘወትር ከነሱ ብዙ ሕዝብ በዚኽ አገር ይገኙ

ነበረና ይላል። ሽዋጀ ዱቲፌኑም ባ፲፮፻፶፫ ዓመት ወደ ምሥራቅ በሄደበት መልእክቱ እንዲኹ ይላል። ደግሞም ወደ ጎልጎታ ቤተ ክርስቲያን ግቢ መጣን ከቀራንዮ በስተቀኝ በትንሽ ደጃፍ ገብተን ፴፱ ዕርከን ወጥተን ስንዞር በኢትዮጵያውያን እጅ ያሉ ፪ ቤተ ክርስቲያኖች አገኘን ብሎ ይናገራል። ይኸውም መጽሐፍ አውጭው እሱ ራሱ ይመሰክራል። በኢዮሳፍጥ ወንዝ ካለች ከድንግል መቃብር ቤተ ክርስቲያን በስተግራ ወገን ያማረች የውሃ ጕድጓድ አለች። በስተዠርባዋ ያለው የኢትዮጵያ መቅደስ ነው ብሎ ይናገራል። (ዛሬ ግን አርመንና ግብጥ ይዘውታል)። የፈረንሲስካን መነኰሳት ወኪልም እስጥንቡል ከተማ ላለው ለፈረንሳዊ ሹም መካናት ቅዱሳትን ለማሳሰብ በጽፈው መልእክት እንዲኽ ይላል። ለኢትዮጵያም ሰዎች በከተማው ገዳምና ቤተ ክርስቲያን አላቸው። ከጎልጎታም ደጃፍ ከመውጫው ላይ ቤተ ክርስቲያን ነበራቸው እሷም ዛሬ በሮም እጅ ናት ብሎ ይናገራል። «በዚኽ ታሪክ ውስጥ ሮም የሚለው ኹሉ ግሪክ ነው» ሮምና አርመን ግን በኢየሩሳሌም ያለ የሐበሾችን ይዞታ ለመቀማት ሲሚገቱ ነበሩና ርስታቸውን የተቀደሰና እይሚሳም ቦታቸውን ኹሉ ከጃቸው ወሰዱባቸው። ይኸውም የኢትዮጵያ ገዳም ሙሐንድስ በስከዋል ሱራፌ ባሳየኝ ፈረማኖች ይታወቃል። ከነዚኹም አንዲቱ በስላሞች ቈጥር ባ፲፻፸፰ ዓመት ዚልሕጃ በሚባል ባ፲፪ኛ ወራቸው ባ፲፯ ቀን የተጻፈች ናት። ቃሏም ይኽ ነው። በሲዩስ የሚባል የሮም በረከት (ሊቅ ጳጳስ) ባ፲፪ ከ፸፬ ዓመት ዚልቂዕዳ በሚባል ባ፲ኛ ወራቸው ባ፲ቀን በኢየሩሳሌም ያሉ የኢትዮጵያ ሕዝቦ ከዳኝነቱ በታች ይደሩ የሚል ትእዛዝ ከሥልጣን ተቀበለ ትላለች። እሱም ያን ጊዜ ከቃዲው የአርመንን ሕዝቦች በኢየሩሳሌም ያሉትን ሊያቀርብለት ፈለገ። የሐበሾችን ወቅፍና የሚሳም ቦታቸውን ቤተ ክርስቲያናቸውን በጎልጎታ ውስጥ ያለውን ከውጪም ያለውን በጃቸው የያዙትን ኹሉ በሥልጣን ትእዛዝ ለቀው ለርሱ ያስረከቡ ዘንድ። አገረ ገዥውም በዚያው ጊዜ ኹላቸውን የአርመኖችን ጳጳስ ወኪል ትርጁማናቸው የሚኾን የኽዘርን ልጅ ያዕቆብን አቀረበለት። ትእዛዙን ካነበበላቸው በኋላ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የነበረውን ኹሉ በጃችኹ ያለውን ለሮም አስረክቡ ብሎ አዘዛቸው። ወዲያው የመንግሥት ሹማምንቶች ወደ ጎልጎታ ሄዱ የሮሞች ትርጁማን አብራሂም በጎልጎታ ከሚኖረው ከሰርኪስ ከአርመኑና ከወገኖቹ በሹማምንቱ ፊት ተረከበ። ከግንዘቱ ላይ ቀንዲል የሚሰቀልበትን ቦታ ከመቃብሩ ውስጥ ፯ ቀንዲል የሚሰቀልበትን ቦታ ከመቃብሩም ውጪ ፪ ቀንዲል የሚሰቀልበትን ቦታ አንዱ በሰሜን አንዱ በደቡብ ፫ቱንም ጓዳዎች ለሐበሾች ብቻ የነበሩትን በቤተ ክርስቲያንኑ ደቡብ ያሉትን በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንነት የታወቁትን በውስጣቸውም ያሉትን የብርጭቆ እንዲሎች በሰሜንም ያሉትን ፪ ጓዳዎች እነሱን ተጠግቶ የታነጠውንና የተጌጠውን ዕንጨት በሰሜን በኩል ያለውን በምሥራቅም ያለውን መቅደስ የሐበሾች መኾኑ የታወቀውን የታነጠ ዕንጨት በስተደቡብ በአንጻሩ ያለውን በምሥራቅና በደቡብ መካከል ያለውንም መቅደስ መንበሩ በሚሳለሙት ዐምድ ላይ ያለውን በውስጡም ያሉትን የብርጭቆ ቀንዲሎች። ደጃፉ የታነጠ የተበሳሳ ዕንጨት የኾነውን ፊት ለፊት ያለውን ይኽ ኹሉ ከጎልጎታ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው። ኹሉንም ጨርሰው ወሰዱ። በጎልጎታ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለነበሩ ለኢትዮጵያውያን ሰዎች ከብር ቀንዲልና ከብር መስቀላቸው ከንዋየ ቅድሳታቸው ኹሉ ምንም አልቀረላቸው። ሐበሾች ፯ ቀንዲል ይሰቅሉበት በነበረው ቦታ ሮሞች ከራሳቸው ፳ የተበሳሳ የብር ቀንዲል ሰቀሉ። ፯ቱን ከመቃብሩ ውስጥ አንዱን ከግንዘቱ ላይ። በጎልጎታ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊው

መሹና ሶርያዊው ዮሴፍ እንዲኽ ብለው ጽፈዋል ይባላል። ከግንዘቱ ላይ ለሐበሾች የብር ቀንዲል ነበራቸው አርመኖች ወሰዱት የኢትዮጵያ ቦታ በጃቸው ነበረና። ሮሞች ደግሞ ካርመኖች የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን የታችኛይቱን በደቡብ በኩል ያለችውን ለጎልጎታ የምትጎራበተውን ወሰዱ። በጎልጎታ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወደ ርሷ የሚገቡትንም የኢትዮጵያን ገዳም ብከርሷም ጋራ ያለውን ቦታቸውንና ቤቶቻቸውን ከገዳሙም አጠገብ ከላይኛው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን ኹሉ ጨርሰው ወሰዱ። ለኢትዮጵያ ሰዎች በጎልጎታ እንዲኽ የተደላደለ ቦታና መዓርግ ነበራቸው። ብርሃን በሚወጣበት ቅዳሜ ከሚሰበሰቡት ኹሉ አስቀድሞ ወደ መቃብር የሚገባው የኢትዮጵያ ራኢስ ነው ለዚኹም እንሆ ፈረመናቸው። ዚልህጃ ፲፱ ቀን ፱፻፵፱ ዓመት ብርሃን ወደ ሚወጣበት ቦታ መዠመሪያ የሚገባ የኢትዮጵያ ራኢስ ነው። ፪ኛው የሮም በትረክ። ፫ኛው የአርመን ራኢስ። ፬ኛው የኰርጅ ራኢስ። ፭ኛው የሶርያ ራኢስ። ፮ኛው የግብጥ ራኢስ ነው ይላል። በሌላውም ሕጂ እንደዚኹ ይላል። ጀማደ እልአወል ፬ቀን ፱፻፰፫ ዓመት የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ራኢስ የተክለ ሃይማኖት ልጅ ዐብድ እልመሲሕና የሮሞች በትረክ ጀርማኖስ የአርመኖች ራኢስ የአብርሃም ልጅ እንድርያስ የኰርጅ ራኢስ የዳዊት ልጅ ዩአቄም የሶርያ ራኢስ የሐዲድ ልጅ ኡበይድ የግብጦች ራኢስ የዮሐንስ ልጅ ሚካኤል በቅድስት አገር በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ተብሎ አስቀድሞ እንደ ተነገረ እነዚኽ ኹሉ ከዛሬ ቀን ዠምረው ወደ ፊት እንደ ጥንት እንዳለፈው ዘመን አገር ሳይከፈት እንደ ነበረው ሥርዐታቸው ሊሡሩ ተስማሙ። ከዚያም በኋላ በያመት ባላቸው ቀን ብርሃን በሚወጣበት ጊዜ በጎልጎታ መቅደስ ውስጥ አንድነት ይሰበባሉ። ብርሃን ከሚወጣበት ቦታ መዠመሪያ የሚገባው የኢትዮጵያ ራኢስ (መምህር) ነው ከርሱም በኋላ የሮም በትረክ ነው ፫ኛው የአርመን ራኢስ ፬ኛው የኰርጅ ራኢስ ፭ኛው የሶርያ ራኢስ ፮ኛው የግብጥ ራኢስ ነው። ይኸም የጥንት ሥርዐታቸው ነው። እነሱም አኹን ከተናገርነው ቦታ አንድነት ጧፍ አቃጥለው ከዚያ ይወጣሉ። ደግሞም ብርሃን በሚወጣበት ቅዳሜ ከሚሰበሰቡት ዋነኛው የኢትዮጵያ ቄስ እንደ ኾነ ይገለጣል። ኡጂን ሩጂ በሚባል በ፪ኛው መጽሐፍ የምናነበው እንሆ ይኸ ነው። በትረኩና ጳጳሳቱ ቀሳውስቱና መነኰሳቱ አንድነት ተሰብስበው ልብሰ በዓላቸውን ይለብሳሉ ተመልሰው ወደ መቃብሩ ሲሄዱ አንድ ቄስ በፊት በፊታቸው ይሄዳል። እሱም ለዚኹ ላመት ባል ሥራ ብቻ ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትና ከዮሐንስ ቀሲስ የሚላክ ኢትዮጵያዊ ነው። ይኸም የተናገርነው ቄስ ነጭ ልብስ ይለብስና ዘይት የመላበት ያልተቃጠለ ፈትል ያለበት የብርጭቆ ቀንዲል በጁ ይዞ ወደ መቃብሩ ሲደርስ እስላሞች ይከፍቱለትና ወደ ውስጥ ይገባል ገብቶም ደጃፉን ይዘጋል። የሮም በትረክና የቀሩት ቀሳውስት ግን ከሕዝባቸው ጋራ በየጃቸው ጧፍ ይዘው ከውጪ ቆመው ይጠብቁታል። ይኸውም ቄስ ብርሃን ከወጣለት በኋላ የመቃብሩን ደጃፍ ይመታዋል የሚጠብቁት ሰዎች ለመሳለም ይገቡ ዘንድ። የሮም በትረክና የቀሩት ምጥራኖች በየጃቸው የያዙትን ጧፍ ከዚያ ቀንዲል አቃጥለው ወዲያው ፈጥነው ከመቃብሩ ይወጣሉ። የኢትዮጵያ ወዎች ብርሃን እያወጣ ርስታቸውን በጃቸው እንደ ያዙ እስካ ፲፮፻፺፬ ዓመት ድረስ ነበሩ። በትሪሙኒዩሲራፌኩ የሚባል ባለታሪክ እንዲኽ ይላል የምስር መንግሥት ኢየሩሳሌምን በያዘ ጊዜ ያባይን ዳር ድንበር የሚገዙ የኢትዮጵያ ሰዎች ውሃውን መመለስ ወደ ሌላ ማፍሰስ ከዚኽ የተነሣ ግብጥን እንድትራብና እንድትጠማ ማድረግ የሚቻላቸው ስለ ኾነ ከምስር ንጉሥ የሚገባቸውን ኹሉ አገኙ። ቅድስት

በዓላቸውን እንደ ወትሮ ያከብሩ ዠመር። ከዚያም በኋላ ብዙ ዘመን ሠልጥነውበት ኖሩ። ሌላውን መቀማት የማይችሉ ሮሞች ግን ሐበሾችን ጠላት አደረጓቸው። ይችን ተልእኳቸውን ቀምተው ለራሳቸው ሊያደርጉ ስለ ፈለጉ ታላቅ ሙግት አነሡባቸው ብዙ ገንዘብ እስኪያከስሯቸው ድረስ። በመጨረሻውም ዛሬ ዕርቅ አድርገው የሮም በትረክና ያርመን ጳጳስ ከኢትዮጵያ ቄስ ካንዱ ወይም ከኹለቱ ጋራ ኹነው በዓላቸውን ያከብራሉ። ሮምና አርመን ከሐበሻ ጋራ ከመቃብሩ ውስጥ ገብተው እንደ ጥንት ሥርዐታቸው ደጃፉን ዘግተው ብርሃን ያወጣሉ። ሐበሾች ከሮምና ካርመን ጋራ ኹነው ከመቃብሩ ውስጥ ገብተው ብርሃን ማውጣታቸው የቀረበትን ጊዜ ለይቼ አላወቅኹትም (ስሯጽ) ባ፲፰፻፺፰ ወይም ከዚያ በታችና ከዚያ በላይ ፱ኛው ሴክል ሲጨረስ በዚያ ግድም የቅዳሜ ሹር ለት ሮምና አርመን ብርሃን ስለ ማውጣት በቅድምና ነገር ተጣልተው በቱርክ ዳኝነት ሲሟገቱ መዝገብ ይታይልን አሉና መዝገቡ ቢታይ ቅድምናው የሐበሾች ኹኖ ተገኘ። ዳኛውም ቅድምናው የሐበሾች ከኾነ እነሱ ይፈልጉት እንጂ እናንት በሰው ገንዘብ ምን ያጣላችኋል ይልቅስ ሂድ እንደ ጥንታችኹ ብሎ ኹለቱንም አሳፈራቸው። ያበሾችም በየሩሳሌም መኖርና በዚያው እንደ ባላገር መኾናቸው ከጥንት ከዘመነ ብሉይ ዠምሮ ነው ምኵራባቸውም ለብቻው የተለየና የታወቀ ነበር ይባላል። የጎልጎታውም ቦታቸውና አገልግሎታቸው በዙሪያውና በውጪ ያለውም ገዳማቸውና የሚሳም ቤተ ክሲያናቸው ኹሉ በስማቸው የተጠራና ርስት የኾነላቸው በውዲያ ከእሌኒ ዘመን ከቈስጠንጢኖስ በወዲኽም ከአብርሀ አጽብሐ ዠምሮ ነው። በዚያም ከሚኖሩት ሐበሾች ብዙዎች ሕጋውያን ዓለማውያን ደብተሮች ጾመ ድጓ ቋሞች ናቸው እንጂ ኹላቸው መነኰሳት ብቻ አልነበሩም ምክንያቱም ቦታቸውና ርስታቸው ብዙ ስለ ኾነ ነው። ተስዐቱ ቅዱሳን ወዳበሻ የወጡትንም ምክንያት ይኽን ያበሾችን ክብርና ተልእኮ በጎልጎታ ውስጥ ስላዩ ነው ብለው የሚተርኩ አሉ። ገዳማቸውም ሊቃነ ጳጳሳት ከሚያዟቸውና ከሚሾሙባቸው ከሌሎች ገዳማት ተለይቶ ዴር ሥልጣን (ገዳመ ንጉሥ) መባሉ የሚያዝበትና የሚሾምበት አለቃውና ጠበቃው ባለሥልጣን ንጉሣቸው ስለ ኾነ ነው። ከዚኽ ይልቅ ደግሞ በቅድስት አገር ለሚኖሩት ኹሉ ክርስቲያኖች እስላሞች እንዳያጠቋቸው መመኪያቸውና መኵሪያቸው ማስፈራሪያቸው አይዟችኹ ባያቸው ስለ ኾነ አምኃውን ግማደ መስቀል እስከ መላክ ደርሰው ንጉሣቸው ያዩት ነበረና ስለ ክብሩና ስለ ግርማው ስለ ልዕልናው ነው። የሥልጣኑና የሥልጣንነቱም ምልክት በገዳሙ ውስጥ የናዜ ካሌብ ዘውድ በውጪም በገዳሙ ደጃፍ ታላቅ ወፍራም ሰንሰለት ነበረ ግብጦች ደግሞ ዴር ሥልጣን መባሉ በኛ በግብጦች ንጉሥ በምሥሩ ሥልጣን ነው እንጂ በሐበሻ ንጉሥ አይዶለም በለው አንደ ኒቅያው ቀኖና ለውጠው ገልብጠው ያወራሉ (ዮሐ፰ ፵፬)። ዘውዱና የብር ከበሮው በሮሞች እጅ አለ ይባላል የቀሩትን ንዋያትና መጻሕፍት ካቶሊካውያን ሳይቀሩ ኹሉ ተካፍለውታል። ይኸውም ሊታወቅ ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ የላኩት መጽሐፍ ነገሥት በሮማ አለ በዳሩ ጎኅታ ያሉትን ካህናት ብርሃን የሚወጣ በኛ እጅ ከኾነ እኛ እንበልጣለን ብላችኹ በዚኽ እንዳትመኩ ዐደራ ብሎ ከትቢት የሚያርቅ የሚያስጠነቅቅ በትሕትና ዝናር የሚያስታጥቅ የምዕዳን ቃል አለበት)። በዛሬው ዘመናችን ግን ለሐበሾች በተቀደሰው ቦታ ትንሽ እንኳ አገልግሎት የላቸውም ባመት ባልም ቀን ባንድ ኹነው የሚሠሩት ሥራ የላቸውም። ቀድሞ የኢትዮጵያ ሰዎች ለሐዋርያዊ መንበር ብዙ አገልግለዋል። የፈረንሲስካን መነኰሳት እስላሞች ባሳደዷቸው ጊዜ የተቀበሉትን መከራ ላ፩ኛው

ኡጂኒዩስ አስታውቁ። «በኤውሮፓ ቈጥር ካ፲፩፻፹፩ እስከ ፹፱ የነበረ ነው»። እሱም መከራቸውን ለማራቅ አንድ ጊዜ ኤውሮፖችን በገንዘብ ርዷቸው በማለት አንድ ጊዜም በምሥራቅ ያሉ ካቶሊኮችን ለዚኽ ለበጎ ሥራ ዕገዟቸው በማለት ብዙ ደከመ። በመጨረሻውም ለኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የምስርን ንጉሥ በግድ ያስታግሠው ዘንድ በቅድስት አገር ተግተው ለሚያገለግሉ ለፈረንሲስካን መነኵሳት የሚገባቸውን ከርሱ በፊት የነበሩት የሰጧቸውን ስጦታ እንዳይከለክላቸው ፈጽሞ እንዲታረቃቸው አድርግልኝ ብሎ ቈርጥ ቃል ላከ። የኢትዮጵያም ንጉሠ ነገሥት ሐዋርያዊውን መንበር በሚያስፈልገው ጥቅም ዅሉ ብዙ ርዳታ ረዳ። ለምስሩም ንጉሥ በኀይለ ቃል አስታወቀው። ለመነኰሳቱ የሚገባቸውን ካንተ በፊት የነበሩት የሰጧቸውን ነጻነታቸውን አላገባብ አሽከሮችኽ ያጠፉባችውን ክሳራ መልስላችው ይኽ ካልኾነ በብዙ ሰራዊት እመጣብኻለኹ ብሎ ላከበት። ሕዝበ ክርስቲያን ዅሉ ለመነኰሳቱ ብዙ ምጿት ላኩላቸው በዚኽም ምክንያት የሄደባቸውን ክሳራ መለሱ። ለኢትዮጵያውያን ቀድሞ ዘመን በጃቸው ከነበረው ቦታ ምንም አልቀረላቸው። የተቀደሰውንም ቦታ ለብቻቸውም የያዟቸውን ገዳማት የሚሳም ቦታቸውን ዅሉ ሮምና አርመን ወሰዱት። የተረፈውንም ግብጦች ጨረሱት። በዴር ሥልጣን መግቢያ ያሉትን ወደ ጎልጎታ የሚያሳልፉትን ፪ቱን ቤተ ክሲያኖችና ሐሳቦች ከውስጡ ያሉበትን ገዳም ያኛ ነው እያሉ ይሟገታሉ። ይኽችም ጠባቸው ሐሳቦች ከከተማ ውጪ ቦታ ገዝተው ቤተ ክሲያንና ገዳም ከሠሩ ዠምሮ እጅግ በረታች በመጨረሻው ግብጦች በሐበሾች ገዳም ውስጥ ያሉትን ዅለቱን ቤተ ክሲያኖች ዘግተው መክፈቻ ወሰዱ በዅለቱም የነሱን በረኛ አቁመው ወደ ጎልጎታ የሚያልፍ ሳሚ የሚሰጠውን መባ ለራሳቸው አደረጉ። ይኽችም ሙግት በመካከላቸው ስለ በረታች ለብዙ ክርክርና አቤቱታ ወደስጥንቡል አደረሰቻቸው። በዚኽ ምክንያት የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት (ዐፄ ምኒልክ) ወደ ሥልጣን ብዙ ብዙ መልክተኞች ያመላልስ ነበር። እስካኹን ድረስ ነገራቸው ገና አላለቀም። የሎንሶ ቢዮ ታሪክ እስከዚኽ ነው። (ማስታውቂያ)። አንድ ክፍል ቦታ የነበረው የጎልጎታ ምሥራቅ ዴር ሥልጣን ካራት ተከፍሏል ፩ኛውን ክፍል ዋነኛውን ገዳም ግብት ልሥራላችኹ ብሎ ተነኩል ገብቶ ወዲያው ቀምቶ ይዞታል። ፪ኛውን ክፍል ፈረንጆች በከራይ ገብተው ቀምተው ወስደውታል ግብጥም ባለርስትነት ስለሌለው ክራይ አምጡ ወይም ውጡ ብሎ በግድ መያዝ አልቻለም። ፫ኛውን ክፍል ግብጥ ውስጥ ለውስጥ ለመስኮቦች ሽጦት ቤተ ክሲያን ተሠርቶበታል ይኸውም ቦታ የጥንት ሐበሾች የመስቀል ደመራ ያደርጉበት የነበረው ነው። ፬ኛው ክፍል ዛሬ ሐበሾች ያሉበት ነው ይኸነኑም ከቤተ እግዚያሔሩ ላይ ያለውን ደርብ ቤታቸውን ቀምቶ ባለጋራ እንደ መኾኑ ርሱው ራሱ ግብጥ የቈራኛቶታል። በዚያም የሚኖረው የግብጥ ቄስ ያቦች ራኢስ እየተባለ የሐበሾች መቅደስ በነበረው በጌቴሴማኒ ይቀድሳል። አባ ማሆስም ከነብላታው የተዘጋውን ለማስከፈትና ለማስታረቅ በተላከ ጊዜ እስከ እስጥንሉልና እስከ መስኮብ ሂዶ የግብጦችን ነገር መሥርቶ ገድግዶ ልቡናቸውን አክብሮ የተላከበትን እምነቱን ክዶ ኢትዮጵያንም አዋርዶ ውለታዋን ዅሉ ገደል ሰዶ የጠቡን እሳት በማጥፋት ፈንታ ቈስቈሶና አንድዶ ደረቅ ዕንጨት ቃሉን ዠግዶ እንዳይጦልስና እንዳይጠፋ አድርጎት ተመልሷል። የርሱ ምስክርነት የሚጸድቅ መስሎት ኢትዮጵያ ከጥንት ዠምሮ ከግብጥ በታች የምትኖር የግብጥ ጥገኛ ናት እንጂ በዚኽ በቅዱስ ቦታ ርስትና ክፍል የላትም ብሎ በቅብጥ በዐረብ ጥፎና ዕትሞ በወዲያም በወዲኽ መንግሥት ሲለወጥ ያን ጊዜ አውጡት ምንም

ግብት ብኾን የማዕርግ ስሜ ሊቀ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ነውና የኋላ ኋላ በግድ ምስክር ይኾናል ብሎ ነገሩን ኹሉ በሰላ ድንጋይ ወርቅ ዐንጦ ቀርጦ ለብጦና አስጊጦ ለዘመዶቹ ሰጥቷቸው መጥቷል። ሐዋርያትም ሠለስቱ ምእትም ከባላገር በቀር ባዕድ የውጪ ሰው ጵጵስና አይሾም ማለታቸው በቤተ ክስያን ላይ እንዲኽ ሸፍቶ እንዳይኰራ እንዳይንጠራራ አድልዎና ግፍ እንዳይሠራ ለሕዝቡም እንጀራና አባት ምቀኛና ጠላት እሾኽ ዕንቅፋት እንዳይኾን ነበረ ኢትዮጵያ ግን እየሰማች ገና አልሰማችም።

ቀድሞም አራቱ አቡኖች በወጡ ጊዜ ማርቆስ ወዲያው በቶሎ ሞተና ማቴዎስ ደግቦ ቦሩ ሜዳ ላይ ታሞ ለሞት ቀርቦ ሳለ ከዛቋኞች ማኽል አንድ የግዜር መንፈስ የቃኘው ዳንኤላዊ መነኵሴ ዛሬ በሕልሜ ይኽ የታመመ አቡን መላውን የኢትዮጵያ ካህናት ባዋጅ በግዝት ባንዳይቅር ሰብስቦ ቁልቁላና እንቢልታ የሚያክል ረዣዥም ዋገምት በጁ ይዞ በያንዳንዱ ኹሉ በየካህኑ ዐንገት እየተከለ ደሙን ሲመጠው አይቻለኹና ደንጊያም ቢጭኑበት አይሞትም። ሌሎቹ ያልቁና ርሱ ብቻ ቀርቶ ኢትዮጵያን ምጥምጥ አድርጎ ይበላታል ዕድሜውና ሀብቱ ብዙ ነው ሥጋዊ ጌትነት ተሰጥቶታል የነፍሱን ግን እንጃ ወዳገሩም ይመላለሳል ብሎ እስከዚኽ ድረስ ተነግሮለት ነበር እንዳለውም ኹኖ አንድ እንኳ ሳይቀር ኹሉ ተፈጸመ (ዓሞ፫ ፯)። ከዚኽ የቀረ ዜና ገድሉን በዋዜማ ታሪክ ተመልከት።

(ብሥራታዊ ግጥም)
የዴር ሥልጣን ማኅበር ግብጥ የሚጠጣሽ፤
መራራ ሖምጣጣ መርዛም ስላልኾንሽ፤
ባባ ማቴዎስ ምክር እንዳይጨልጥሽ፤
ከመዦመሪያው ጋን ከጥንቱ ገችሽ፤
ታሪክ እያስቀዳ ሊያሳልፍልሽ፤
ተፈሪ መኰንን ሙሴ ኾነልሽ።
ማነኽ ባለሳምንት ብሎ ሲጠይቅ፤
ስላንቺ ወድቄ እኔም ልመረቅ።
ገና ሳይተይቀኝ ይኽ ዐዲሱ ሙሴ፤
ገድልሽን ለማንበብ ተስሏል ምላሴ፤
ኻያ ኹለት ዓመት ያየኹት ግፍ፤
ይገባኛልና መናገር መጣፍ።
አንባቦች ተርጓሞች ሰሚያዎችም ደግሞ፤
ፍትሐ ነገሥታችኹ ከታየ ፈጽሞ፤
ግብጦች በወሰዱት በሰንሰለታችኹ፤
ከዴር ሥልጣን ጋራ ይቈራኝ ልባችኹ።
ከደጃችኹ ይግባና ዐብሮ ይታሰር።

እስመ ረሳዕኩኪ ኢየሩሳሌም ለትርስዐኒ የማንየ፤ ወይጥጋዕ ልሳንየ በጕርዔየ ለእመ ኢተዘከርኩኪ፤ ወለእመ ኢበፃዕኩ ለኪ።

የኢትዮጵያ መንግሥት ዐልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ።

ይድረስ ከደብተራ ኪዳነ ወልድ እንደ ምን ሰንብተኻል፤ እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደኅና ነኝ። ከዐረቢ ወዳማርኛ ተተርጕሞ ይምጣልኝ ያልኹት መጽሐፍ ደርሶኛል። በውስጡም ፍሬ ነገር አይታጣበትም። እነደ ተመኘኹልኝ የእግዚአብሔር ፈቃዱ ኹኖ የኢየሩሳሌም ርስት በኛ ዘመን ከጃችን ቢገባ የኔም ዋና ምኞቴ ነው። ሕዝቅኤሉንም ተግተኽ ጨርሰኽ ዐሳቤን እንድትፈጽምልኝ ይኹን።

ጥር ፳፱ ቀን ፲፱፻፲፫ ዓመት። ዐዲስበባ።

<><><><><><><>

**(ሌ) - ሌባሻይ።** በግንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ጊዜ ሽፍታ እጅግ በዝቶ ነበር። ከሽፍቶቹም አንዱ ዋነኛው ንግዴ ይበሳል። ሣህለ ሥላሴም የንግዴ ነገር ስላስፈራቸው አትርሱኝ ሲሉ ወደ ገዳማቱ ገንዘብ ላኩ። ከመነኰሳቱም አንዱ መነኰሴ ሲያሳርጉ ንግዴም ዳር ዳሩን ያነጥንጥ ሣህለ ሥላሴም ካልጋው አይናወጥም ብለው አሳረጉ። ይኸነንም ያሉበት ምክንያት ንግዴም በበኩሉ እየዘረፈ የሚሰጣቸው ስለ ኾነ ነው። ንጉሡም የሽፍታና የሌባ ነገር ቢያስቸግራቸው ከባለሚሎቻቸው ጋራ መክረው የሌባሻይን ብልኀት አወጡ፤ ብልኀቱም እንዲኽ ነው። ባላገር ኹሉ በያገሩና በየመልከኛው፤ በየባላባቱና በየገጠሩ አገር የሚያውልና የሚጠብቅ ስሙን የጐልማሳ ጌታ እያለ አንዳንድ ሰው ይሾም ነበር። ሽማግሎችና አማካሪዎች መርማሪዎችም ይመረጣሉ። እነዚኽም ኹሉ ሌባዉንና ቀጣፊውን ሽፍታውንና ወንበዴዉን በውነት መርምረው ይይዙና ለጐልማሳ ጌታ ይሰጣሉ። (ወዮ ይኽች ብልኀት ምንኛ ድንቅ ናት!፤ አባት ልጁን አይመርምና)። ነገር ግን አንዳንድ ሌቦችና ቀጣፎች ካንዱ አገር ወዳንዱ አገር እየተዛወሩ ቀን ሲሄዱ ይውሉና ማታ መሽቶ ጨለምለም ሲል ሰርቀው ቀምተው ሌሊቱን ገሥግሠው ጧት በቤታቸው ይገኛሉ። ሌብነታቸው እየታወቀ ሲይዟቸው ዐሰት አልሰረቅንም፥ ርቱን እያሉ ያስቸግሩ ነበርና፤ የጐልማሳ ጌታ ከሽማግሎችና ካማካሪዎቹ ከመርማሪዎቹም ጋራ ኹኖ ለሌባሻዉ ሌባዉን ይጠቈመዋል፥ ሌባው የተያዘ እንደ ኾነ የተሰረቀው ዕቃ ይገኛል እሱም፤ ሌብነቱን ያምናል። ስለዚኽ ሌባሻይ ለጊዜው እውነተኛ መሰለ ስሙም የንጉሥ ቈና ተባለ። በኋለኛው ዘመን የነበረው ሌባሻይ ኹሉ ግን ገንዘቡ የጠፋበትን ሰው ጠላትኽ ማነው የምትጠረጥረውስ ማነው፤ እያለ ባልሰረቀው ሰው ቤት እያስተኛና ያልሰረቀውን እየያዘ ሰውን የሚጐዳና የሚያታልል መኾኑን ስላወቁ የኢትዮጵያ መንግሥት ዐልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን በንግሥት ነገሥታት ዘውዲቱ ጊዜ ይቅር ብለው አስቀሩት። አገራችንም ከታላቁ አደጋ ዳነች። በሌባሻይ ምክንያት ቤታቸውን የተወረሱና ትዳራቸውን ያጡ ብዙ ናቸው። ሌባሻይ ምን ቢኾን ከፈረንጅ ቤት አይገባም ነበር። ኹል ጊዜም በውሃ ይታጠባል፤ ይኽም ዋና ማታለያው ነው (፲፰ኛ ሥዕል)

**(ነ) - ነብር።** ነብር በዱር የሚኖር መልከ ዥንጕርጕር የድመት ወገን አውሬ ነው። እሱም ፍየሎችን ዐንገታቸውን እየጠቃ (እየወጋ) ይገድልና ደማቸውን ይጠጣል ሥጋቸውን ግን በመሬት ውስጥ ቀብሮ ያበሰብስና ሲርበው ይባላል። ደም ጠጥቶ ሳለ ሰው ሊገድለው ቢመጣ በፍጥነት አስታውኮ ወደ ሰውዬው ይገሠግሣል፥ ባያስታውክ ግን ይሸሻል ደሙ ይከብደዋልና የተገኘ እንደኾነ መሞቻው ያን ጊዜ ነው። ነብር ልበ ሙሉ ደፋር ነውና ሳይዝ አይሞትም። እግዜር ዥብን ጕልበታም አድርጎ ፈጠና ልበ ፈሪ አደርገው ነብርን ግን ጕልበተ ትንሽ አድርጎ ፈጥሮ ልበ ደፋር አደረገው ይባላል። ባላገሮች በጐባጣ ግራፍ ቅርንጫፍ ላይ አንዲት ኰሳሳ የፍየል ግልገል አስረው ስማርድ የሚባል ወጥመድ ከግልገሏ በታች ከዛፉ ላይ ያጠምዱና ነብሩን ኹሉ እየያዙ ይገድሉታል። ነብር ያይን ዕመም ይጠናበታልና፥ ሰዎች ዐይኔን ዐይኔን ያሉ እንደ ኾነ ካለበት ስፍራ ሸሽቶ

ይሄዳል ቅንጭብም ይፈራል። (ተረት) አንድ ቀን አያ ነብሮ ዐይኑን ታሞ ቢተኛ እንኰዬ ጦጢት ልትጠይቀው ሂዳ በቤቱ (በዋሻው) ቈጭ ብላ ስታነጋግረው ሊበላት ዐስቦ እእ አንጠራራኝ አለና እጁን ወደሷ ሲዘረጋ እኔንም ሰው ጠራኝ ብላ ሄደች (አመለጠች)። ለወዳጆቻቸው ክፉ የሚያደርጉ ሰዎች ብዙ ናቸው። (፪ኛ ተረት)፤ ከዕለታት አንድ ቀን እንኰዬ ጦጢት በቤቷ ተቀምጣ ሳለች አያ ነብሮ ድንገት ከተፍ አለና አስደነገጣት እሷም ሥጋ ልጋብዝኽ ወይ አለችው ዕሺ ምን ከፋኝ አላት ፈጥናም ወደ ግምጃ ሄደችና አሎሎ አግላ በሞራ ጠቅላ ሰጠችው እሱም ያንን ዋጠና ተፈነቸረ (ሞተ)። (ተረፈ ዳን ፲፪ ፳፯)። ሬሳውንም ከቤቷ የሚያወጣላት አጥታ ተቸግራ ሳለች፥ አያ ኸቦ ወደ ቤቷ መጦ ገንሆይ ጦጢት እባክሽ ሥጋ ስጪኝ አላት እሷም ኸራትኽን ልስፋውና አለችው ዕሺ ስላለ አንድ ዐጥንት ሰጠችው። ከዚኽም በኋላ ፊቱን መልሶ ዐጥንቱን ሲቈረጣጥምና ሲያጕመጕም ከነብሩ ዝራት ጋራ ልትሰፋው በወስፌ ጠቅ ብታደርገው ተዪ ዐመምሽኝ አላት አምጣ ዐጥንቴን አለችው። ዝም ብሎ ዐጥንቱን ሲቈረጣጥም ዳግመኛ ጠቅ አደረገችው ተዪ ዐመምሽኝ አላት አምጣ ዐጥንቴን አለችው። እንዲኽ እያደረገች የኸቡን ኸራት ከነብሩ ጭራት ጋራ ሰፍታ ስትጨርስ፥ ሰማኽ ወይ አያ ኸቦ አያ ነብሮን ትፈራዋለኽን አለችው ከቁም ነገርም (ከመ ጤፍም) አልቈጥረውም አላት። አንድ ነገር ሸፍናው ነበርና ገለጥ አድርጋ ይኸ ምንድነው ብትለው ደንገጠና በኸራቱ ጐትቶ ከቤቷ ይዞላት ወጣ ሲሸሽም ወዲያው ገደል ገባ። ይኸም ተረት ዕውቀት የሌላቸው ሰዎች ዕውቀት ካላቸው ሰዎች ጋራ ሳይመረምሩ ለጥቅማቸው ብለው በመጨረሻው ጕዳት የሚያመጣባቸውን ውል እንዳይዋዋሉ ይስጠንቅቃቸዋል። እንቅልፍ ታበዢ ከነብር ትፋዘዢ። የነብር ኸራት አይዙም ከያዝሙ አይለቁም። (፲፯ኛ ሥዕል)

**(ዐ) - ዐይጥ።** ዐይጥ በቤትና በዱር የሚኖር ትንሽ አውሬ ነው። እሱም ጐተራዉን ኹሉ በጥርሱ ቀዶ ይገባና እኽል ይበላል። የከስከሶ ጐታ ካልኾነ በቀር የሚያግደው የለም ይኸውም ዕንጨቱ የሚመር ስለ ኾነ ነው። በክረምትም እኽል ተዘርቶ ቡቃያው ባደገ ጊዜ ቡቃያዉን በጥርሱ እየቈረጠ ይጥለዋል፤ ስሙም ቈራጭ ይባላል። ባላገሮችም ድ(ደ)ፍጥ በሚባል በደንጊያ ወጥመድ አንድ እሳት የተለበለበ የስንዴ ዛላ ቀጪን በኾንች የናጫ ገመድ ከማስፈንጠሪያ ጋራ ያጠምዱና ዐይጡን ኹሉ ይፈጁታል (ይገድሉታል)። ዐይጥ ኹለት ዐይነት ነው ኹለተኛው አፈ ሹል ነው ስሙም ዐይጠ መጐጥ ይባላል። ዐይጥ የተነፈሰበት ፈትል ይበጣጠሳል። (፲፰ኛ ሥዕል)

(ያይጥ ፍራት።) አንድ ቀን አቶ ዐይጦ በስምሪት ዋለና ማታ ሲገባ ሚስቱን ልጆቼን እንደ ምን ዋሉ ብሎ ቢጠይቅ አቶ ድመት መጥቶ አንዷን ወሰደ አለችው። እሱም ተናደደና ይኸ ድብርቅ ዐይን፥ እኔ ልጆቼን ከቈጥ እባጥ እያልኹ አሳደግኹና ለሱ መገበር ኾነን፤ ቈይ ብቻ ግድ የለም እያለ በቤቱ ሲንጐራደድ ድመት በሰበሰብ (ግንፌጥ) ኹኖ ስድቡን ሰምቶ ነበርና ሚያው እያለ መጥቶ ምን አልኽ ቢለው አንዷን ደግሞ በጨመርሽለት አልኹ እንጂ ሌላ ምንም አላልኹ ብሎ መለሰለት። (ያይጥ ኵራት)። ከዕለታት አንድ ቀን ዐይጥና ዘንዶ ተጣሉ። ዐይጥም ዘንዶን ለመግደል መዣሪያ (መሰቅሰቂት) ታጥቆ መጣና ከዘንዶ ጋራ ተጋጠመ። ዘንዶዉም አፉን ከፍቶ ዐይጡን ዋጠ ስልቀጥ አደረገው፤ ዐይጡም በመሰቅሰቂቱ ሆዱን ቀዶት ወጣ። ኹለተኛውም ቢውጠው እንደ ገና ቀዶት

(ሽርክቶት) ከሆዱ ወጣና ያዘው እቤቱ መግባቱን ትቶ ወረጋዉን (ባዶ እጁን) በካብ ላይ ቈጭ እያለ ይዉል ዠመር። ሚስቱም ጭልፊት ትመታዋለች (ትወስድዎታለች) እባክዎ እቤት ይግቡ ብላ ብትመክረው (ብትለምነው) እንኳን ጭልፊትና ዘንዶ ገድያለኹ እያለ ይመካል ኾነ። ድንገትም ሳይስበው ረ ጭልፊት ዠሮ ግንዱን ብላ ይዛው ስትሄድ፥ ወደ ሚስቱ ረ ዱላዬን አቀብዪኝ እያለ ጮኸ። ሚስቱም የጒመኑን ነወይ ያገዳዉን ብላ መለሰችለት። ጭልፊቷም እየቦጨቀች በልታ ጨረሰችው። አንድ መሣሪያ እንኳ ሳይኖረው ጭልፊትን መናቁ እጅግ ያስደንቃል ያስገርማል። ካይጥ ቤት ብቅል። (፲፰ኛ ሥዕል)።

**ዕንጨቶች።** ከዕለታት አንድ ቀን ዕንጨቶች ኹሉ ጠላታቸውን ለማጥፋት ምክር ሊመክሩ ተሰበሰቡ። በመኻከላቸውም አንዱ ተነሥቶ ጠላታችንን ለማጥፋት አንችልም ብሎ ተናገረ። ኹሉም ባንድ ቃል ስለ ምን አሉት። ጠላታችን (መጥረቢያ) ብቻውን መጥቶ ባልጐዳንም ነበር ነገር ግን ከውጣችን አንዳንድ ጠማማ ውስጣወቅ ይወጣና እየሄደ ከሱ ጋራ ይስማማል (ይዋደዳል)፤ ምሥጢራችነንም ይነግረዋል። እኛንም ለማጥፋት እጅ ለጅ ተያይዘው ይመጣሉ። አንዳንድ ጊዜም ልብስ ቅርፊታችንን ይገፋሉ ዐንገት ቅርንጫፋችንን ይቈርጣሉ ብልት ቅጥያችንንም ይሰልባሉ ብሎ መለሰላቸው። ይኽ ተረት ባንጥያኮስ ጊዜ በእስራኤል ላይ ተፈጽሟል። ባገራችንም ባጤ ቴዎድሮስ ጊዜ ተደርጓል። (ሉቃ፲፪ ፶፪-፶፬)

**(ፊ) - ፈላስፉ።** በቀድሞ ዘመን የሰውን መልክ አይቶ ያደረገውንና ገና የሚያደርገውን የሚያውቅ ፈላስፋ ነበርና ውበቷ ከልክ ያለፈ ይኽ ቀረሽ እያለ ሲሠራት የዋለ መዠመሪያ ሙሉ እመቤት ኹለተኛ አቻም የለሽ የተባለች ልጃገረድ እየከሳችና እየመነመነች፥ ቅሥሟ እያነሰና እየቀነሰ እየኰሰሰ ስለ ሄደ አባቷ ወደ ፈላስፋው ይዟት መጣ። ፈላስፋውም ጒዳቷ ደኅና ምግብ ካለመመገብና ደኅና መጋቢ ከምጣት የተነሣ መኾኑን ላወቀ ገልጦ ቢናገር የሚሰማው የለምና ላባቷ ሰማኸይ ወንድሜ በልጅኽ አስቀድሞ ጠቋርና ደም ቀለቡ ዐድረዉባት ነበር ኹለተኛም ብር ዐለንጋ የሚባል ዛር ዐድሮባታል። አኹንም ወሰን ገፊ ተጨምሮባታል ሀብቷም እንዳይቀና ዐይነ ጥላና የድፍነትም ተደርጎበታል ለብር ዐለንጋ ዶግማ ፍየል ነጭ ዶሮም በየጊዜው እያረድኽ የኮርማዉንና የበጉን የዶሮዉንም ደም ቅባት ብሎ የቀንድ እጀታ ቢላዋ ሰጠው። ሥጋዉንም ኹሉ ከሷ በቀር ለማንም እንዳታቀምስ ላይነ ጥላዉና ለድፍነቱም በነጩ ፍየል ቈዳ ክታብ አድርግላት አለው። እንደ ነገረው አደረገ፥ ልጅቷም ዳነችለት ሰውነቷም እየዳበረ ሄደ። ከዚኽም በፊት አንድ ሌላ ሰው ብዙ ገንዘብ ይዞ ወደ ፈላስፋው ቤት መጣ እንዲቀበለውም ለመነው። ፈላስፋውም ገንዘብ ስቀበል ፍልስፍናዬ ይጠፋብኛልና አልቀበልም የምትጠይቀኝም ነገር እንዳለ ያለዋጋ (በብላሽ) እነግርኻለኹ አለው። እሱም መሞቻዬ ምን ጊዜ ነው የምሞተውስ በምድን ብሎ ጠየቀው። ፈላስፋውም ሰውዬው ውርዴ መኾኑንና ቈስል እንዲጠናበት ስላወቀ፥ ዳግመኛም የሚኖርበት ስፍራ እሾኽ እንደ በዛበት ስለ ተረዳ በዚኽ ዓመት በዚኽ ወር በዚኽ ዕለት ድንገት እሾኽ ወግቶ ይገድልኻል አለው። ያም ሰው ያለ ገንዘቡን እየበላ ሱሪዉን ሳይታጠቅ ባልጋ ላይ ተኝቶ መዋልን ዐሰበ፤ እናሰበውም አደረገ።

ከዕለታትም አንድ ቀን ልጆቹን ከመንጋው መኻከል የበግ ሙክት መርጠው እንዲያመጡ አዘዛቸው ባመጡም ጊዜ መሥባቱንና አለመሥባቱን ለማወቅ ዐልጋው ላይ እንደ ተቀመጠ ወዲኽ አምጡ አለና የበጉን ሽንጥ ሲዳብስ በጠጕሩ ውስጥ የኰሸሽላ እሾኽ ኑሮ ጣቱን ጠቅ ቢያደርገው ደንግጦ ወዲያው ሞተ። ሥራ ሳይሠራ ባልጋ ላይ መዋሉ ሳያድነው ቀረ ተሸፋፍኖ ቢተኙ ገልጦ የሚወጋ ጌታ አለና፡ (፲፱ኛ ሥዕል)

ፍርድ። ራስ እምሩ በደጃዝማችነታቸው ሐረርጌን ሲገዙ አንዱ ሰው ኹለቱን ሰዎች በጕድጓዳ ስፍራ ደብድባችኹ ገንዘቤን ቀምታችኹኛል ብሎ ከሰሳቸው እነሱም ዐሰት አንተን ደብድበን ገንዘብኽን መቀማት የለብንም ርታን አሉት። ራስ እምሩም ምስክር አለኽይ ቢሉት የለኝም አላቸው። በል እሰጥ ብለኽ ተወራረድና ገንዘብኽን የቀሙብትን ምድር ምስክር ቈጠራት አሉ። እሱም እንዳዘዙት ተወራርዶ ምድሪቷን ከቈጠረ በኋላ አመሳካሪ ዳኛ ጨምረው አንዱን አስቀርተው ከኹለተኛው ባለጋራ ጋራ ምድሪቷን ዕወቂልኝ እንዲል ላኩት። ከዚኽም በኋላ ጥቂት ቈይተው በሳቸው ዘንድ ያለዉን ሰው በል አንተ እነዚያ ሰዎች እቀማችኹበት ቦታ ይኽን ጊዜ አይደርሱምን ብሎ ቢጠይቁት አይደርሱም ብሎ መለሰላቸው። ራስም ሰው ልከው እነዚያ በቶሎ እንዲመለሱ አደረጉ። ከተመለሱም በኋላ ሊመሳከር የሄደዉን ቀማኛ ባልንጀራኽ እውነቱን አውጥቷልና፥ አንተም እውነቱን አውጣ አሉት እሱም አዎን ደብድበን ገንዘቡን ቀምተነዋል ብሎ አመነ፥ ኹለቱም ተቀጡ። ራስ እምሩ እንዲኽ አድርገው ብልኅና እውነተኛ ስለ ኾኑ በፍርድ ነገር እጅግ የተወደዱና የተመሰገኑ ናቸው።

**(ጸ) - ጽንዕት።** ሐሳበ ጽንዕት ወጽንጽንት (ሐሳበ ጸኒዕ ወጸንጽኖ)። ባ፲፪ቱ ወር ውስጥ ዕንጨት ተቈርጦ የሚነቅዝበት የማይነቅዝበት ቀን ቈጥር።

፩ኛ መስከረም እስካ ፲፰ ጽንዕት ከዚኽ በኋላ ጽንጽንት።

፪ኛ ጥቅምት እስከ ፳፫ ጽንዕት ከዚኽ በኋላ ጽንጽንት።

፫ኛ ኅዳር እስከ ፱ ጽንዕት ከዚኽ በኋላ ጽንጽንት።

፬ኛ፥ ታኅሣሥ እስከ ፳፫ ጽንዕት ከዚኽ በኋላ ጽንጽንት።

፭ኛ፥ ጥር እስካ ፲፯ ጽንዕት ከዚኽ በኋላ ጽንጽንት።

፮ኛ፥ የካቲት እስካ ፰ ጽንዕት ከዚኽ በኋላ ጽንጽንት።

፯ኛ፥ መጋቢት እስካ ፰ ጽንዕት ከዚኽ በኋላ ጽንጽንት።

፰ኛ ሚያዝያ እስካ ፲፩ ጽንዕት ከዚኽ በኋላ ጽንጽንት።

፱ኛ፥ ግንቦት ጽንጽንት።

፲ኛ፥ ሠኔ እስከ ፳፬ ጽንዕት ከዚኽ በኋላ ጽንጽንት።

፲፩ኛ፥ ሐምሌ እስካ ፲፯ ጽንዕት ከዚኽ በኋላ ጽንጽንት።

፲፪ኛ ነሐሴ እስከ ፳፫ ጽንዕት፤ ከዚኽ በኋላ ጽንጽንት።

» ጳጕሜ እስከ ፫ ጽንዕት ከዚኽ በኋላ ጽንጽንት። ይኽ ቃል ባሮጌ መጣፍ ዳር እየተጣፈ ይገኛል የተሳሳተም ቢኖር የሚያውቅ ሊያርመው ይችላል።

(ቀ) - ቀበሮ። (የቀበሮ ፍርድ)። እባብ በክረምት ውሃ ሞልቶበት ዳር ዳሩን ሲንቀዋለል አንድ ሰው መጣ እባቡም ሰውዮ እባክኽ አሻግረኝ ብሎ ለመነው። ይም ሰው አሻግረኝ ብሎ ለመነው። ይም ሰው እጅ የለኽ እግር የለኽ ምንኽን ይገዬ ነው የማሻግርኽ አለው። እባቡም ፈቃድኽስ ከኾነ ራስኽ ላይ ጠምጥመኝ ቢለው ጠምጥሞ አሻገረው። ካሻገረውም በኋላ በል ውረድልኝ ቢለው እንቢ አሎርድም አለ። ወደ ዳኞች (አራዊትም) ኹሉ ሂዶ ቢከሰው ዳኞቹ (አራዊቶቹ) በገዛ እጅኽ እባብ ራስኽ ላይ ጠምጥመኽ እያሉ ፈረዱበት። በመጨረሻውም በቀበሮ ዳኝነት ከሰው ቀበሮዋም እባብን እምድር ወርደኽ በግራ ቁመኽ ሥራት ለብሰክ ተነጋገር አለችው እሱም ተተረተረና ዱብ አለ። ከዚኽም በኋላ ቀበሮዋን ሰውዬው እህ አላት እሷም ሰው በትር ይዞ ቁሞ እባብ እምድር ተጋድሞ ብትለው ራስ ራሱን ብሎ ቀጥቅቶ ገደለው። ችሎም ሲመለስ ብድሯን ለመክፈል ማታ በግ አመጣልሻለኹና፥ ቤትሽን አሳዪኝ አላት እሷም አስከትላው ሂዳ ቤቷን አይቶ ተመለሰ። ማታም ውሻዉን አስከትሎ ሂዶ ከበር አፏ ቁሞ እንኰይ ቀበሩት ብቅ በዪ አላት በግ ይዞልኝ መጥቶ ይኾናል አለችና ብቅ ብትል ያዝ ኩቲ ብሎ ውሻዉን ለቀቀባት እሷም ሰው ሰው ሰው ለሰው ሞት አነውሰው እያለች ወደ ቤቷ ጥልቅ አለች። ሽማግሌ ሲመርቅ ከወዳጅ ጠላት ያድንኽ የሚለው እንደዚኽ ያለውን ነው። ይኽ ሰው ክፋትን የተማረ ከባብ ነው። (ዘፍ፫ ፩-፭) (፳ኛ ሥዕል)

**ቂል ባሪያ።** በጎይለ መለኮት ጊዜ አንዱ የወግዳ ሰው ክፉ ሥራ ስለ ሠራ ቤቱ ሲወረስና ከብቱ ሲቈጠር ባሪያዉን በጐተራ ውስጥ ደበቀው። ሹሞቹም ከብት ከገባ በኋላ መጥተው ቤቱን ሲይዙና ከብቱን ሲቈጥሩ ያ ባሪያ በከብቱ መኻከል እያቀናጀ የጕልማዉን የሚያስበት አንድ በሬ ነበረውና ራሱን ከጐተራው ውስጥ ብቅ (ዘለግ) አድርጎ ይመለከት ዠመር፤ ሹሙም ከብቱን ኹሉ እየቈጠረ ከሱ በሬ አጠገብ ሲደርስ አየና «ተው አያ እሱ የኔ በሬ ነው» ብሎ ቢጮኽ አንተም እዚኽ ኑረኻልን ብሎ ከጐተራው ውስጥ ጐተተና አውጥቶ ወሰደው። በለፈለፉ ባፍ ይጠፉ። (፳፩ኛ ሥዕል)

**ቆቅ።** ቆቅና ዶሮ እጅግ ይዋደዱ ነበር ከፍቅራቸውም ብዛት የተነሣ ማኅበር ሊወጡ ነገሩን ቈረጡ። መዠመሪያውም ማኅበር በቆቅ ደረሰ ማኅበሩም በኅዳር ወር ውስጥ ስለ ኾነ ዶሮ ቀጠርቶ ወደ ቆቅ ቤት (ወዳረኽ) ወጣ። ለድግሱም የስንዴዉና የገብሱ የባቄላውና ያተሩ የማሽላዉም እሸት ተሰናድቶ (ጕምርቶ) ነበርና እንደፈቀዳቸው ሲጋበዙ (ሲተከትኩና ሲጠረጥሩ) ዋሉ በመሸም ጊዜ እጅግ በለሰለሰ ገርሣ ውስጥ ተኝተው ዐደሩ። በማግሥቱም ምሳቸውን በጧት ተጋበዙና ዶሮ ወደ ቤቱ ሄደ። ከዚኽም በኋላ የዶሮ ማኅበር ቢደርስ ቆቅ ተጠራ ዶሮም በሚኖርበት ዐጥር ግቢ ውስጥ ባንድ ፊት የስንደዉና የገብሱ ፍትግ ባንድ ፊት የባቄላዉና ያተሩ የሽንብራዉም ክክ ተሰናድቶ (ተሰጥቶ) ቢያይ ለማኅበሩ የተሰናዳ መሰለውና ቆቅን ደስ አለው። ነገር ግን ሊበሉ ወደ ገበታው (ወደ ስጡ) ዳር በቀረቡ ጊዜ የእኽሉ ባልና ቤት

ዕሽ አለችና ቅምዝምዝ በታቅመዘምዝ የዶሮን ክንፉን የቆቅን እግሩን መታቻቸው እነሱም ሸሽተው ወደ ጐድፍ ሄዱ ካሙኚት በቀር ሌላ ምንም አላገኙም። በዚያውም ላይ ጣይ መታቸውና ሳይጠግቡ እያለከለኩ ወደ ጥላ ገቡ። በመሸም ጊዜ ሆዳቸው ጥቂት እንኳ ቡርቡጭ ሳይል ወደ ቈጥ ላይ ወጥተው ተኙ (ሰፈሩ)። ከዚኸም በዃላ እሳት ነደደና ጭሱ ዐይናቸውን ሲላቸው አመሹ እሳቱ ተዳፍኖ ጪሱም ቢጠፋ በቈጡ ላይ ቅንቅን ነበርና እስከኩለ ሌሊት እንቅልፍ ሳያሸልባቸው ቀረ። እኩለ ሌሊትም በኾነ ጊዜ ዶሮ ክንፎቹን አንዘፈዘፈና ኩኩሉ ብሎ ጮኸ። ቆቅም እጅግ ስለ ገረመው በዚኹም ዐዳርኽ ግብር አለብኽ አለው ይባላል። እንዳይነጋ የለምና ሌሊቱም በነጋ ጊዜ ቆቅ እከከከከ አለና በሮ ወደ ቤቱ ሄደ። ዶሮ የመከረኛው ድኻ ምሳሌ ነው። ዶሮ እንደዚኽ ባለ አኗኗር ይኖርና በመጨረሻው ይታረዳል፡ ድኻም በብዙ ችግር ኑሮ ይሞታል። ቆቅን ከኽል ምክንያት የተነሣ ወጥመድ ይይዘዋል። ሰነፎችንም ጠላታቸው በገንዘብ እያባበለ እጅ ያደርጋቸዋል። ዶሮ ክንፎቹን ስለ ምን ያንዘፈዝፋል የሚውቅ የለም። ባላገሮች ግን የመላእክትን ክንፍ ድምጥ እየሰማ ነው ይላሉ (ሕዝ፩ ፳፬)። ዶሮ ዕንቈላላቸውን ቀፍቅፋ (ፈልፍላ) ያሳደገቻቸው የቆቅ ገላግልቶች (ጫጩቶች)፤ ክንፋቸው ሲጠና ቱር እያሉ ወደ ዱር ይሄዳሉ። ትምርትንም የተማረ ሰው ከችግርና ከጨካኞች ቀንበር ይድናል ይወጣል ያመልጣልም። ነገር ግን በገልገልነታቸው ክንፋቸውን ቢሰብሯቸው መብረር አይችሉም። ትምርትንም ያጣ ሰው ከድንቈርናና ከባርነት ከግብዝነትና ከመቀማት ከመታለልና ከመሞኘት ከችግርና ከድኽነት አይድንም። ሰዶ ማሳደድ ቢሻኽ ዶሮኽን ለቆቅ ለውጥ። (፳፪ኛ ሥዕል)

**(ሰ) - ሴት።** የሴት ዐይነቷና ስሟ አራት ነው ይባላል። መዠመሪያዋ ጣዝሙት ኹለተኛዋ ንቡት ሦስተኛዋ ተርቡት አራተኛዋ ዝንቡት ናት። ጣዝማ ማሯ እጅግ ጣፋጭ ነው ዋጋዉም የከበረ፥ የሚገኘውም በጨዋ ቤት ነው ለቈስልና ለሳል ለባጭም ይበጃል (መድኅኒት ይኾናል)። የጣዝማ ማር በኹሉ ስፍራ አይገኝም። ጣዝማ ሰው አትና(ነ)ደ(ድ)ፍም። (ጣዝሙት) ባለሟያ ሴት የጋገረችው እንጀራ የጠመቀችው ጠላ እጅግ ይጠፍጣል የሠራችው ወጥ እጅ ያስመጥጣል ለሰውነትም ጤና ይኾናል። የፈተለችው ድርና ማግ እዩኝ እዩኝ ይላልና ሸማዉን ባደባባይ ማንም እየጐተተ ያየዋል። እሷም የምትገኘው ለባለዕድል ነው። ባሏንም አንድ ቀን እንኳ አስቀይማው አታውቅም ከሞት በቀር ከባሏ የሚለያት የለም። የሴት ንግሥት ይሉኻል ይኽች ናት። ጣዝሙትን ሰሎሞን በምሳሌው ምዕ ፴፩ ከቍጥር ፲ እስከ ፴፩ ሲያመሰግናት ስማ (እይ)። ንብ የንማትቀሥመው ዕንጨት የለም ወደ ቀፎዋም ስተባ ቀሥሟን በጇና በግሯ ይዛ ትገባለች ምን ቦና ቢኾን ከቀፎዋ (ካርኬናው አጠገብ) ያውራ እራት አይታጣም። ደመናም ባየች ጊዜ ማሯን ከዳ ታደርገዋለች ቀፎዋን ትታ ወደ ሌላ ቀፎ አትገባም ቀሠማም ባታገኝ በዱር ታድራለች፤ የሰው ወዝ ሳይቀር ትቀሥማለች። አንድ ጊዜ ሰውን ከነደፈች ኹለተኛ አትና(ነ)ደ(ድ)ፍም መርዟ ይወድቃልና። ሥራቷም እጅግ የሚያምር በመኾኑ እግዜር ንብን አይተኽ ተገዛ ብሏል ይላሉ የሰው ሥራት ግን በየጊዜው ሲበላሽ ይኖራል። የማይና(ነ)ደ(ድ) ፈውም ንብ ድንጕል ይባላል ውሃም ይቀዳል። (ንቡት) የማታውቀው ሞያ የለም ወደ ገበያም ወጥታ የሚያስፈልጋትን ገዝታ ትመለሳለች እንጂ የማይፈለግ ነገር ይዛ አትመጣም።

ምንም ችግር ቢኾን ቤቷ አይጐድልም ከቅል እቀንድ እያለች የባሏን ጐን ትጠብቃለች። የሴቱን ሚያ ኹሉ ታጠናለች። በሷንም በሚገባ አንድ ጊዜ ትቈጣዋለች እንጂ፤ በማይገባ ዘወትር አትጨቀጭቀውም። በደኅና ቀን ትለግሳለች በክፉ ቀን ግን ትቈጥባለች። ባሏን ትታ ሌላ ባል አታገባም። ወፍጮ የሚፈጨና ውሃ የሚቀዱ ገረዶች ትቀጥራለች። (ስትናገርም ካፏ ማር ይዘንባል ተከንፈሯ ጠጅ ወይዘሮ ንቡት የትጋት ወዳጅ)። የሴት ዕምስትያ ይሉኻል ይኽች ናት። ሰሎሞንም አስተዋይ ሴት ለባሏ ዘውድ ናት። ብልኀተኛ ሴት ቤቷን ትሠራለች ያላት ንቡት ነው (ምሳ፲፪ ፬። ፲፬ ፩። ተርብ እንደ ማር ዐይነት ያለ ታበጃለች ነገር ግን በውስጡ ምንም አይገኝበትም። በቤቷም ውስጥ በያይነቱ ትል ይገኛል። በመና(ን)ደፍም ከንብ እጅግ ትከፋለች፤ መርዟ ከሷ አይለይምና። የተርብ እንጀራ የባላ ውሻ ክፉ ይኾናል፤ እሷ እንዴት ትከፋ። (ተርቡት) እንደ ሴቶቹ ትጋግራለች ትጠምቃለች ነገር ግን ለድግሷ ጣዕም የለውም። በሷ ምነው እንጀራው ቂጣ ኾነ ወጡስ ምነው ዐልጫ ኾነ ቢላትም ብትበላ ብላ ባትበላ ተወው ትለዋለች ቢመታትም መልሳ ትመታዋለች ይኾናል። ቡኻቃዋንም አታጥበውም ዐመዱንም አትጠርገው ቤቷንም አታጠዳው ዕቃዋንም አትከድነው። ስለዚኽ በድግሷና በመሰናዶዋ ኹሉ ጕድፍ ይገኝበታል (ይገባበታል)። አንድ ቀን ተርቡት ከባሏ ተጣላችና ሽማግሎች ታረቂ ቢሏት አሻፈረኝ አለች ምክንያቱንም ቢጠይቋቸው በመኗችን አባ ጨጓሬ ቢገባበት ጭቅጭቅ ዝንብ ቢገባ ጭቅጭቅ አልችልም ይፍታኝ አለቻቸው። አሳዳጊ የበደላት ይሉኻል ይኽች ናት። ሰሎሞን በምሳሌው ከጠበኛ ሴት ጋራ ባንድ ቤት ከመቀመጥ በማገር አጠገብ መቀመጥ ይሻላል። ከጠበኛና ከቌጡ ሴት ጋራ ከመቀመጥ በምድረ በዳ መቀመጥ ይሻላል ያሉት ተርቡትን ነው። (ምሳ፳፪ ፱ና ፲፱)። ዝንብ ቈስልንና መግልን ደምንና ዕድፍን ኹሉ የምትቀሥም ናት ያረፈችበትም ነገር ለሰው ዐይን ያጸይፋል ያንዱን ቈስል ቀሥማ ላንዱ ታጋባለች በቈላም በተሰበረ ጊዜ አገዳው ውስጥ ገብታ ታልቃለች። (ዝንቡት) ያገኘችውን ወንድ ኹሉ የምትተኛ አመንዝራ ሴት ናት። ገንዘብም ከሰጣት ይኽ ጌታ ነው ይኽ ድኻ ነው ይኽ ጨዋ ነው ይኽ ባለጌ ነው ይኽ ቈንጆ ነው ይኽ መጥፎ ነው አትልም። ገንዘብም ብታገኝ የማይረባ ነገር ትገዛለች (ታበላሸዋለች)። ያንዱንም በሽታ ወዳንዱ እያስተላለፈች በጨብጥና በቂጥኝ በብዙ ዐይነት ዕመም ሰዉን ኹሉ ትፈጀዋለች (ትጨርሰዋለች)። ወረቷም ባለቀ ጊዜ የትም ወድቃ ትቀራለች። ባልም ብታገባ ቤት ከማበላሸት በቀር ሌላ ሥራ የላትም። የሴት ረኽጥ ይሉኻል ይኽቺ ናት። ወዳጅኽን ይዘኽ ና ቢሉት ውሻዉንና ቈርበቱን ጠላትኽን ይዘኽ ና ቢሉት ሚስቱን ይዞ የሄደው ሰው የንዝቡት ባል ነው። ዝንቡትን ሰሎሞን በምሳሌው ፯ ፩-፳፯ የሚላትን ስማ (እይ)

**(ተ) - ቴዎድሮስ።** በዘመናችን ያጤ ቴዎድሮስ ጭከናቸውና ክፋታቸው ይነገራል እንጂ ዕውቀታቸውና እውነተኛ ፍርዳቸው እጅግ አይነገርም አይወራም፤ አይወሣም። ነገር ግን ወልደ ሚካኤል የሚባል ደብተራ በተንኰሉ አእምሯቸውን ሳይለውጠውና ሳያጠፋው እጅግ የሚያስደንቅ ፍርድ ይፈርዱ ነበር፤ ፍርዱም ይኽ ነው። የይፋት አውራጃ ካህናት በገዛ እጁ ከውሃ ገብቶ የሞተዉን ሰው ተዝካር ስለ በሱ የክፉ ተዝካሩ ያቅራል እንዲሉ ተከሰሱና ጐንደር ሄዱ እንጉሡ አደባባይም ቀረቡ። ዐጤ ቴዎድሮስም ነገሩን በሰሙ ጊዜ ባብዬ ሣህለ ሥላሴ አገር የደግ እረኛ ስሙ ማን ይባላል ብለው ሺዎችን ቢጠይቁ ስሙር የከፋውሳ ቢሉ

ማጋጣ ይባላል አሏቸው። ስሙር እረኛ ከብቶቹን ሲያግድ የሰው ዝሪት እንዳያጠፋ የሰው ማሳ እንዳይረግጡ ተጠንቀቅ ሲጠብቅ ይውላል ከብቶቹንም ማለፊያ ግጦሽና ለቀም ወዳለበት ይወስዳቸዋል። በዚያዉም ላይ ለማምሻ ዕንጨት ይሰብራል ለመብራትም የክትክታና የፋየለፈጅ ግጥግጥ ይገጠግጣል ማታም ከብቶቹን ነድቶ ከቤቱ ይገባ የለሞይ ቢሉ አዎን ጃንሆይ እውነት ነው አሏቸው። ማጋጣ እረኛም እንዳርቶ ገባና እንደ ወሮ በላ ከዝላይና ከጨዋታ በቀር ከብቶቹን አንድ ጊዜም መለስ ብሎ አያያቸውምና የሰው ዝሪት ሲበሉ የሰው ማሳ ሲያበላሹ ይውላሉ በመጨረሻውም ተበታትነው ይጠፋሉ። እሱም አንዱን ላይዘው የትም ጠፍቶ ያድራል ከኒኸ ከኹለቱ አማላጅ የሚፈልገው ማንኛው ነው ቢሉ ማጋጣው አሏቸው። ኸዚያዲያማ መጣፍ «ወለጻድቃንስ እምግባሮሙ ትሜሕሮሙ ወትዔስዮሙ በከመ ጽድቆሙ። እስመ ለነ ለኀጥኣን ለእመ መሐርከነ ውእተ ኣሚረ ትሰመይ መሓሬ» ይል የለምን የንስሓ ቦታስ የሚባለው ለኀጥኣን ነው እንጂ ለጻድቃን ነውን ጌታስ «ኢመጻእኩ እጸውዕ ጻድቃነ አላ ኀጥኣነ ለንስሓ» ብሎ የለምን። ስሙረ እረኛ አማላጅ ካልፈለገ እነዚኸ ካህናት ኀጢአት የለባቸውም ብለው በየጕላቸው። (ኹለተኛው ፍርድ) አንድ ጊዜ ዐጤ ቴዎድሮስ ዘመቻ ሲሄዱ ባንድ አገር ሰፍረው ሰነበቱ ወታደሩም በባላገር ላይ ተመራ። ከወታደሮቹም አንዱ ባንዲት ድኻ ሴት ቤት ተመርቶ ነበርና ዕቅፍ ዶሮዋን ከጫጩቶቿ ነጥሎ ዐርዶ በላባት። በማግሥቱም ንጉሡ በከብት ተቀምጠው ጕዞ ሲዠምሩ ያች ድኻ ሴት ፲፪ ጫጩቶች በወንፊት ይዛ ጃንሆይ እግዚሓር ያሳይዎ ክርስቶስ ያመልክትዎ እኔ ባሪያዎ ሴትኛ ዕዳሪ ድኻ ስለ ኾንኹ አንዲት ዶሮ ነበረችና እሷኑ እያረባኹ ያመት ልብሴንና የለት ጕርሴን ችላኝ ትኖር ነበር ነገር ግን ትላትና አንዱ ወታደር ዐርዶ በላብኝ አለችኝ ጮኸች። እሳቸውም የኔ አሽከር እንኳን ዶሮና በሬስ ዐርዶ ቢበላ ምናለበት ብለው በቶሎ አስጠሩት እሱም በመታ ጊዜ ዛሬም ዐርደኸ ብትበላ ግድ የለም ብቻ እውነቱን ንገረኝ ቢሉት ማድረጉን አመነ። ቈማጣ ቈመጥማጣ ኸዚያዲያማ እነዚኸ ጫጩቶች እናታቸው ሙታባቸው ታ(ዐ)ቅፎ የሚያሳድጋቸው የለምና ያሳዝናሉ ብርድና ችጋርም ይገድላቸዋል። ንሣማ እናታቸው ዘንድ ደብላቸው እናታቸው ት(ታ)ቀፋቸው አሉና በከብት ተቀምጠው እንደ ቆሙ ፲፪ ጫጩቶች አሏጡት። ለድኻዋም ገንዘብ ሰጧት። ሌላም የሰሎሞንን ፍርድ የሚመስል ብዙ ፍርድ አላቸው። የሠሩት ኀጢአት ኹሉ ኢትዮጵያን አንድ በማድረጋቸው ይሰረይላቸዋል ለደብተራ ወልደ ሚካኤል ይብላኝለት እንጂ። ሲፎክሩም ዘራፍ መይሳአው ካሳ ያበሻ ልጅ የየሩሳሌም ውሽማ። መይሳው ካሳ ባጭር ታጣቂ ዘመድ ከዘመድ አደባላቂ ይሉ ነበር ይባላል። እጅግ የሚያስፈሩ ፷(፮) ባሎች ነበሯትና ከነዚያ አስጥለው ስለ ወሰዷት ባንድም አንድነት ረጋ ለጠላቷም አንድ ኹና እንትመከት ስላደረጓት ላበሻ በውነት ባሏ ናቸው። ቱርክን ወግቼ ኢየሩሳሌም አገሬን አስለቅቃለኹ ስላሉ ታጠቅ ብሎ ፈረስ ካሳ ብሎ ስም ዐርባርብ ይሸበራል ኢየሩሳሌም። እኔም ጌታ አይዶለኹ አንተም ሎሌ የየሩሳሌም ሰው ካልጫነ በርበሬ ይባል ነበር። ባገራችን እንዳጤ ቴዎድሮስ ዝናው የደስ ደስ ያለው ንጉሥ ከሳቸው በፊት አልነገሠም። ጳጳሳቸውንም የውጪ አገር ሰዎች የጠላቶቻቸው ሰላይና መሪ መኾኑን ስላወቁ አስረው ገደሉት።

ከንግሊዝ አገር የሚመጣውን ደብዳቤ በማሰሮ መሸፈኛ ውስት እያደረገ ለታሰሩት እንግሊዞች ያቀብል ነበርና። አበሻንና ግብጥን እስከ ዛሬ ድረስ ያፋቀረ ይኸ ይኾናል። ዕንጨት ሳይቈረጥ ቤት አይሠራምና የኢትዮጵያን ያንድነት ቤቷን ሲሠሩ ብዙ ዕንጨት ዐንገት ቈረጡ ብዙ ደም ውሃ አፈሰሱ። እንዳይገባብን ዝናብ ጠላት አለመያዛቸው ክፍክፋት። የነጻነት ክዳን ጕልላት በገዛ እጃቸው መሞት። አገራችን ብዙ የብረት ቀንበር ተሸክማ ነበርና ያንን ኹሉ የሰሩላት ዐጤ ቴዎድሮስ ናቸው። ይኸውም ብላቴን ጌታ ኅሩይ በጣፉት በሕይወት ታሪክ ይታወቃል።

## ቅኔ (ዋዜማ)።

መድኅኔ ዓለም ቴዎድሮስ፤

በፈቃደ ርእሱ ዘሞተ ወተመጠወ ኵነኔ፤

ለእለ ተዘርዉ በብዙኅ ኵርጓኔ፤

አባግዐ በቀል ወቂም መሳፍንተ ኅሊፍ ምጣኔ፤

ወዳግመ ወሰነ ውሳኔ።

(፳፫ኛ ሥዕል)

# ክፍል ፬።

## ምዕራፍ ፯።

በጦር ተማሪ ቤት ባደባይ ወንዝ የሚዘመር የወግዳ ግጥም ይኽ ነው።

አባራሪው ጐበዝ የነብር ለምድ ለብሶ፤
በደም የተነከራ ጐራዴውን በቀኙ፥ ጣምራ
ጦሩን በግራው ይዞ ባርበኞች መኻከል ቁሞ፤
እንዲኽ ይላል።

መሸሽ መሸሽ መሸሽ የለመደ፤
በመጫኛም ቢያስሩት ሄደ እየጐመደ።
ስመላ ዥረት ያለሽ ዕዳሪ፤
መች ትቀሪያለሽ ሳትሞከሪ።
ስመላ ዥረት ያለሽ አሞራ፤
ሥጋዉን በልተሽ ለምዱን ዐደራ።
ስመላ ዥረት ካቡ ስምንት፤
ያንን ላይዘለው ሚስት ዐጩለት።
ስመላ ዥረት ያልተወላዳ፤
ሚስት አይጩለት አህያ ይንዳ።
ወይ ግደልላት፥ ወይ ሙትላት፤
የፈሪ ወዳጅ አታስተኛ።
የፈሪ ወዳጅ ታስታውቃለች፤
አፋፍ ላይ ቁማ ታመነታለች።
የጐበዝ ወዳታስታውቃለች፤
እመኻል ገብታ በለው ትላለች።
ይወለድና ቂጠ ሰፋፊ፤
ያባቱን ምድር ወሰን ገፋፊ።
ይወለድና ቂጠ ሰፋፊ፤
ከናቱ ጋራ ጐመን ዘራፊ።
ይወለድና ኮባ መሳላይ
ለጋለሞታ ይኾናል ሲሳይ።

ውረድ እንውረድ ተባባሉና፤
አስደበደቡት አፋፍ ቆሙና።
የወግዳ ጐበዝ ስሙ ደንቄሬ፤
ይደበድባል ቁሞ እንደ በሬ።
ወዴት ሄዱና አባት በሮቹ፤
ፈሩናጠፉት ወይፋፍኖቹ።
ይጥኛ ሣሩ መምሬ ማምሻ፤
ወዲኽ በዳዊት ወዲኽ በጋሻ።
በላይነኽ ቶራ እሱ ባልነበር፤
ሰው እንደ በሬ ይታረድ ነበር።
ከጫማ ወንዝ ዠምሮ እስከ ደንጊያ ክምር ድረስ በራስ ጐበና መሪነት ድፍን የጋላን ቤት ኹሉ የከፈትች ይኽች ትውልድ ናት። ያገሪቱም የፈረስ ስሚ በራስ ጐበና ቋንቋ መራና ይባላል ጦር ማለት ነው። (ሠንጋ ምት)
እነራስ ጐበና ባቀኑት አገር፤
ቀኛዝማች ግራዝማች ይባሉ ዠመር።
ጐበና አባ ጥጉ ሆድኽን ይባሰው፤
ወትሮም ልማድኽ ነው እያቀናኽ ለሰው።
ያመ ሠላሳ ለት ጐበና ባይጠና፤
ይካፈሉን ነበር እነቱፋ ሙና።
መች አገለገለ ጐበና መልግም፤
የንጉሥ አገር ታሞ እየዞረ ሲያግም።
የሚሰጡት ቢያጡ ከድፍን አበሻ፤
ለራጉኤል ሰጡት የጐበና ጋሻ።
ጐበና ጐበዝ ጐበና ጐበና ራስ ጐበና።

# ምዕራፍ ፰

## የተማሪ ቤት ግጥም።

ተማሪ በሞተ በሰባት ዓመቱ፤
ተምሮ ይመጣል ትላለች እናቱ።
ተማሪ ሊጥፍ ቀስተኒቻ ይሻል፤
መቃብር ዐጕል ነው ቀለም ያበላሻል።
አፈር መልሱ እንጂ ደንጊያ ለምናችኹ፤
የቀልም ቀንድ ነው፤ ትሰብሩታላችኹ።
በተማረ ድኻ ባጣፈው ግንዘት፤
ድረስ ድረስ አሉት ግባተ መሬት።
አብ እሳት ወልድ እሳት መንፈስ ቅዱስ እሳት፤
ቄስ እንዴት ይሞታል ጕሣን ሲቀድሳት።
አገሩ ድብረ ብራን ታቦቱ ሥላሴ፤
ዳዊቱን ጨርሶ ገብቷል እቅዳሴ።
ዳዊቱም ይላላ ይጌይስ ታምኖ፤
ባልንጀራ ሲሞት ይሄዲል መንኖ።
ዳዊቱም ይላላ አኮኑ አኮኑ፤
ስው በሰው ነገር ምነው መኰነኑ።

# ክፍል ፭።

## ምዕራፍ ፱።

***ዐደራ።*** *ከዚኽ ቀጥላችኹ የውጪ አገር ቋንቋ ለመማር እንደምትተጉ የግእዝንም ቋንቋ ለመማር እንድትወዱ ዐደራ እላችኋለኹ። ስለ ምን ብትሉ በውጪ አገር ቋንቋ የተማራችኹትን ጥበብና ዕውቀት የግእዝ ቋንቋ ካላወቃችኹ ወዳማርኛ በቀጥታ መተርጐም አትችሉምና።*

***አንክሮ።*** *ግእዝ ቋንቋ ላወቀው ሰው ዋይ ርቀቱ ምስጢር የሚያናግረው። ዋይ ቅኔው ከደስታ ኹሉ የሚበልጠው። ዋይ ዜማው ሙዚቃ የማይፈልገው። ዋይ ቅዳሴው ዋይ መዋሥዕቱ ዋይ ዝማሬው ልብ የሚመሥጠው።*

***ምስክር።*** *ትምርት ተምራችኹ ስትጨርሱ የምትቀበሉት ምስክር ይኽ ነው። ፩ኛ አረቄ አለመጠጣት ያረቄ መጠጥ ኻያ ሰው ሲገድል አይቻለኹና። አናንተም ብዙ ሲገድል አይታችኋል (ታያላችኹ)። አእምሮ የተባለውንም ያን ትልቁን ሰው ይገድለዋል። ፪ኛ ስጃራን መጥላት ስጃራ በነፍስ ባይኰንን በገንዘብ ምክንያት በሥጋ ይኰንናልና። ፫ኛ ያገራችኹን ፊደልና ቋንቋ ሳትማሩ የውጪ አገር ቋንቋ አለመማር። ፬ኛ ስላገራችኹ ዐሳባችኹን ካለፉት ሰዎች እንደ ብላታ ገብረ እግዚሓር እንደ ነጋድራስ ገብረሒት ማድረግና እንሱ የጣፉትን መጣፍ ዘወትር ማንበብ ነው። እነዚኽ ኹለት ነቢያት ብናደርገው ጥቅም ባናደርገው ጕዳት የሚኾንብንን ወደ ፊትም ባገራችን ላይ የሚመጣውን ኹሉ ጥፈው ትተውልን ሂደዋልና። (ዐደራ)።*

### መወድስ።

**ጃንሆይ መጻሕፍትን ስለ ማሳተማቸውና በየቀኑ ለድኾች ምሳ ስለ ማብላታቸው።**

*አካዝያስ ኮነ ጽልመተ መጽሐፍ፤*

*ወነዌ መሠረተ ሥሥዐተ ይሰመይ።*

*ኀይለ ሥላሴሰ ካህን ገባሬ ሠናይ፤*

*ማኀቶት ለመጻሕፍት፤*

*ወጽፃብ እንበለ አድልዎ ለኵሉ ነዳይ።*

*ናፖሊዮንዚ ንጉሠ ኀይል፤*

*ዕበየ ኀይሉ ያጠይቅ ዲበ ዘመንግሥቱ ንዋይ፤*

*ይብል ተለቂሖ ወርቀ ቃለ ዳዊት ነቢይ፤*

*በምድር ናፖሊዮን ወእግዚአብሔር በሰማይ።*

ባሕቱ ኀሊፎ ወሰነ ዘናፖሊዮን ቀላይ፤

ኀይለ ሥላሴ በዲበ ምድር ወኀይለ ሥላሴ በሰማይ ላይ

ለዓለመ ዓለም ይነግሥ እምቅድመ ካሌብ ፀሓይ።

(ኀይለ ሥላሴ በዲበ ምድር ወኀይለ ሥላሴ በሰማይ ላይ)

<><><><><>

ያማርኛ መወድስ - ልዑል ራስ መኰንን ትግሬ ሳሉ ከየሩሳሌም በኪዳነ ወልድ እጅ ተጥፎ ባባ ወልደ ገብሬል እጅ ወዳዲ ከተማ የተላከ።

ፈረስኽ በእግር የዳመጠውን

እየነደፍክለትን በቀስት ያመለምላል ጐራዴኽ።

ራስ መኰንን ገደል ሰው የማይደፍርኽ

ምኒልክ አዳምን በገነት ሰልፍ

ይቀድመዋልና ፊያታይ እግርኽ።

በሚያበዩትም ጠላትችኽ

ያዘንምባቸዋል እሳት ኤልያስ ሰናድርኽ።

ጣሊያንንሂ የማሽላ እሸት እንድታበላው ጠብሰኽ

ምኒልክ ያ ደገኛ ይመጣልና ወደ ቤትኽ።

አምጥተኽ ቈየው በፊት ራስ ራሱን ቈርጠኽ።

አገዳውንስ ይመጡታል እየሰባበሩ አሽከሮችኽ።

“ወኵሎ ዘተብህለ በእንተ አብ ርቱዕ ያምጽኡ ኀበ ወልድ እስመ ዘይገብር አብ ወልድኒ ኪያሁ ይገብር በአምሳሉ ወዘየዐቢ ግብረ ሀለዎ ያርኢ ለኵሉ በጽንዐ ኀይሉ»።

ዓዲ መወድስ ካልእ በእንተ መቅበርቱ ወተዝካረ ሞቱ ለዝንቱ ልዑል እምልዑላን ወርእሰ ዘቡሩክ ዝክሩ እምንእሱ ወቡርክ ዘርዑ ወፍሬ ከርሥ።

ሚካኤል ቤትከ ቤተ አብርሃም

እስመ እምትካት ውእቱ ማኀደረ ፈላሲ ወነግድ።

ወድንግለ ሙሴ ፍቅርከ እመ ወልደ አምላክ ዋሕድ

ኦመ ዕለተ ሞት ወሊዶታ

ጥብሉለ እስመ ኦስከበቶ ውስተ ዝ ዐጸድ።

ሕገ ሰብእናሁ ከመ ታግህድ

ለተክለ ሃይማኖት ዮሴፍ አበ ብዙኃን ውሉድ።

እግረ ፀርሂ መቃብሪሁ ከመ ኢይኪድ

መብረቅ እምየማንከ ወእምፀጋምከ ነጐድጓድ።


ወኅይለ ሥላሴ ዐይንከ ዐይነ ርግበ ሰማይ ውዱድ

ለምድረ አሕዛብ ይኄጽራ ወይሬስያ ከመ ትርዐድ።

፲፱፻፷፮ ዓ.ም ግንቦት ፲፪።

ኪ.ወ.ከ።

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY



# ስለደራሲው በጥቂቱ

አለቃ ደስታ ተክለወልድ የኢትዮጵያ ዕውቅ የቤተ ክርስቲያን ሊቅ፣ የመዝገበ ቃላት አዘጋጅና ደራሲ ነበሩ።

ሐምሌ 19 ቀን 1893 ዓ.ም. በሸዋ ጠቅላይ ግዛት በተጉለትና ቡልጋ አውራጃ ላይ ወግዳ ጎሸ ውኃ ቀበሌ የተወለዱት አለቃ ደስታ፣ ያረፉት ጳጉሜን 2 ቀን 1977 ዓ.ም. ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትምህርትን ከአጥቢያቸው ዝምሮ እስከ ደብረ ሊባኖስ የቅኔና የዜማ ትምህርታቸውን አጠናቀዋል፡፡

ቀለምን ፈጥኖ በመቀበልና በማስተዋል ችሎታቸው የተመሰከረላቸው አለቃ ደስታ የመጻሕፍት አንድምታ ትርጓሜን አደላድለዋል፡፡ በብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት ቅዱሳት መጻሕፍትን በማረምና በማስተካከል ከ1916 እስከ 1920 ዓ.ም. ድረስ የሠሩ ሲሆን፣ በእርሳቸው አረጋጋጭነት በርካታ መጻሕፍት ለሕትመት በቅተዋል፡፡

በሀገረ ጀርመን በታተመው ኢንሳይክሎፔዲያ ኢትዮፒካ እንደተዘገበው፣ ወደ ድሬዳዋ በመሄድ በአልዓዛር ማተሚያ ቤት ሥራቸውን የቀጠሉበት አጋጣሚ የተፈጠረው ከሊቁ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መተዋወቃቸው ነበር፡ ፡ ከ30 ዓመት በፊት በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ምን እየሠሩ ዐምድ አጋጣሚውን እንዲህ ያስታውሰዋል፡፡

«አለቃ ኪዳነ ወልድ ብርሃንና ሰላምን ሲጎበኙ ደስታ ተክለ ወልድ የግእዙን መጽሐፍ ከፍ ባለ ድምፅ ሲያነብቡና ሲያናብቡ ሰምተው ‘ከኔ ጋር ሥራ’ ብለው ጠይቀዋቸው ነው ይባላል፡፡ ከዚህም የተነሣ በድሬዳዋ አልአዛር ማተሚያ ቤት 16 ዓመት ያህል ሠርተዋል፡፡ እንደገና ከድሬዳዋ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት በብርሃንና ሰላምና በአርቲስቲክ ማተሚያ ቤቶች አገልግለዋል፡፡

«አስተማሪዬ መምህር ክፍለ ጊዮርጊስ የጀመሩትን ግእዝ ዐማርኛ ግስ እንድጨርስ አዘውኝ ነበር፡፡ እነሆ እስከ ዛሬ ደክሜበታለሁ፤ አልተጠናቀቀልኝምና አንተ ተረክበኸኝ ሥራውን ቀጥል፡፡ ዘርሁን፤ ዘር ይውጣልህ» ብለው አለቃ ኪዳነ ወልድ ለአለቃ ደስታ አደራ ሰጥተው ነበር፡፡ አለቃም አደራውን ጠብቀው በ1948 ዓ.ም. ከመደበኛ ሥራቸው ውጭ ሌት ከቀን በመሥራት «መጽሐፍ ሰዋሰው ወግስ፤ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ» የተባለውን የመጀመሪያ ታላቅ መዝገበ ቃላት አሳትመዋል፡፡

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህር የነበሩት የታሪክ ምሁሩ ነፍስ ኄር ዶ/ር ብርሃኑ አበበ ስለ አለቃ ክፍሌና ስለ አለቃ ኪዳነ ወልድ ለ«ምን እየሠሩ ነው?» አዘጋጅ ሲገልጹ እንዲህ ብለዋል፤ «አለቃ ክፍሌ በወቅቱ የአገሪቱ የቀለም ሰዎች ከተባሉት አንዱ ነበሩ፡፡ ዘመኑም የአፄ ዮሐንስ ነበር፡፡ የሃይማኖት ክርክሩ ቦሩ ሜዳ ላይ ተነሥቶ አለቃ ክፍሌ በኋላቀር ካህናት ከሃዲ መስለው በመታየታቸውና በዐፄ ዮሐንስ ዘንድ እጅግ ፊት በማጣታቸው የሸዋ ንጉሥ የነበሩት ምኒልክ አገር ጥለው እንዲሰደዱ ይመክሩዋቸዋል፡፡ ከዚያም በምድረ ሱዳን አድርገው ግብፅ ቀጥለውም ወደ ኢጣልያ ይሻገራሉ፡፡ እነ አግናጥዮስ ጉይዲንና ሌሎችንም ግእዝ ካማርኛ ያስተምራሉ፡፡ ቀጥሎም እርጅና ሲመጣባቸው ወደ ኢየሩሳሌም ጉዞ ያደርጋሉ፡፡ ከዚያም አለቃ ኪዳነ ወልድን ያገኛሉ፡፡ ያላቸውን ዕውቀት ከውድ መጻሕፍታቸው ጋር ለኪዳነ ወልድ ያስረክባሉ፡፡ በተለይም የግእዝና የአማርኛ መዝገበ ቃላት በውል ተሰናድቶ እንዲታተም ለኪዳነ ወልድ አደራ ይሰጣሉ፡፡ በአገሪቱ ዘመናዊ ማተሚያ ሲቋቋም አለቃ ኪዳነ ወልድ ለመጻሕፍት ትርጓሜ ሥራ ወደ አገራቸው ይጠራሉ፡፡ እሳቸው ከአለቃ ክፍሌ የተቀበሉትን አደራ ለአለቃ ደስታ ተክለ ወልድ ያስረክባሉ፡፡ የዚህ ዐቢይ መዝገበ ቃላት ሥራ መነሻው ይህ ነው፤» በማለት ስለሦስቱም ሊቃውንት ያላቸው ግምት ከፍተኛ መሆኑን አንፀባርቀዋል፡፡ ዶ/ር ብርሃኑ የሦስቱንም የቀለም ሰዎች ታሪክ በፈረንሣይኛ ቋንቋ አዘጋጅተው «ሃይማኖተ አበው ቀደምት ወዘደኃርት» ከተባለው የአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መጽሐፍ ጋር አዳብለው በ1978 ዓ.ም. በጀርመን ማሳተማቸው ይታወቃል፡፡

አለቃ ደስታ ለኢትዮጵያ ባህል፣ ቋንቋና ታሪክ ካበረከቷቸው ሥነ ጽሑፋዊ ትሩፋቶች መካከል የግእዝ መማርያ «ርባሐ ስም ወአንቀጽ» (1946 ዓ.ም.) እና «ገበታ ሐዋርያት» (1928 ዓ.ም.) ይገኙበታል፡፡

«አንባቢ ሆይ ያማርኛ ቋንቋ ይህ ብቻ እንዳይመስልህ ከዚህ የቀረውን የእንስሳትንና የአራዊትን የአዕዋፍን፣ የዓሣትን፣ የዕፅዋትን፣ ያገርንና የሰውን ስም አምልተን፣ አስፍተን፣ ከነትርጓሜው ለማሳየት ሐሳብ አለን፤ ለዚሁም ያምላካችን ፈቃዱ ይኹን፤» ብለው በመዝገበ ቃላቱ ላይ ጽፈው ነበር፡፡ ያልታተሙትን ሥራዎቻቸውን ኹለተኛውን እትም ያሳተሙት ልጆቻቸውና ወራሾቻቸው ለንባብ እንደሚያበቁት ይጠበቃል፡፡

## የደራሲው ሥራዎች

1. ገበታዋሪያ፥የንባብ፡መማሪያ።
2. ርባሐ፡ስም፡ወአንቀጽ።
3. ዐዲስ፡ያማርኛ፡መዝገበ፡ቃላት።እንቡጥ ጽጌረዳ(ልብወለድ)